ሥነ-ጥበባት

የተማሪ መጽሐፍ

8ኛ ክፍል

ሥነ-ጥበባት

የተማሪ መጽሐፍ

8ኛ ክፍል



በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ

ISBN ቁጥር -

ዋጋ ብር -

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ

የጥንቃቄ መልዕክት

ተማሪዎች!

ይህን የተማሪ መጽሐፍ በጥንቃቄ ያዙ!

ይህ መማሪያ መጽሐፍ በቀጣይ ዓመት የናንተ ወንድሞችና እህቶች የሚማሩበት የትምህርትቤታችሁ ንብረት ነው! መጽሐፉ እንዳይበላሽ ወይም እንዳይጠፋ በጣም መጠንቀቅ አለባችሁ። መጽሐፉን በጥንቃቄ ለመያዝ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መመሪያዎች ተግባራዊ አድርጉ፤

1. መጽሐፉን ከጉዳት ለመከላከል በላስቲክና በአሮጌ ጋዜጣ ወይም በካኪ ወረቀት ሸፍኑ፤
2. መጽሐፉን ሁልጊዜ ደረቅና ንጹህ በሆነ ቦታ አስቀምጡት፤
3. መጽሐፉን ለመጠቀም ስትዘጋጁ በቅድሚያ እጃችሁ እርጥበት የሌለውና ንጹህ መሆኑን አረጋግጡ፤
4. በመጽሐፉ ሽፋን ወይም የውስጥ ገጾች ላይ አትጻፉ፤
5. መጽሐፉን እያነበባችሁ እያላችሁ ንባባችሁን አቋርጣችሁ እንደገና ለማንበብ ስትፈልጉ ምልክት ማድረጊያ ብጣሽ ወረቀት ወይም ካርድ ተጠቀሙ፤
6. በመጽሐፉ ውስጥ ያሉ ስእሎችን ወይም ገጾችን አትቅደዱ፤
7. በመጽሐፉ ውስጥ የተቀደደ ወይም የተገነጠለ ገጽ ሲኖር በሙጫ ወይም በሌላ ንጹህ ማጣበቂያ ጠግኑት፤
8. መጽሐፉን ከቦርሳችሁ ስታስገቡ ወይም ስታወጡ ጥንቃቄ አድርጉ፤
9. መጽሐፉን ለሌላ ሰው ስታቀብሉም ሆነ ከሌላ ሰው ስትቀበሉ ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጉ። ደህንነቱን አረጋግጣችሁ ተቀበሉ።
10. መጽሐፉን ለመጀመሪያ ጊዜ ስትቀበሉ ሽፋኖቹና ገጾቹ እንዳይገነጣጠሉ መጽሐፉን በጀርባው ጋደም አድርጋችሁ አስቀምጡት፤ ከዚያም ጥቂት ገጾችን ቀስ እያላችሁ በየተራ ግለጡ፤ በግራና በቀኝ እጃችሁ የያዛችሁትን የመጽሐፉን ክፍል በኃይል አትጫኑት (አትመንጭቁት)።

ማሳሰቢያ፤ እነዚህ መመሪያዎች ሳይተገበሩ ቀርተው በመጽሐፉ ላይ አንዳች ጉዳት ከደረሰ በወጣው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ያደርጋል።

ሥነ-ጥበባት

የተማሪ መጽሐፍ

8ኛ ክፍል

አዘጋጆች

ሀብታሙ ግዛቸው

አግማሴ በሪሁን

አርታኢዎች

አሰፋ ሰማው

ጃምቡየ ሰርጡ

ቡድን መሪ

አሰፋ ሰማው

ዲዛይነር

አትርሳው ጥግይሁን

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በተመደበ በጀት በአብክመ ትምህርት ቢሮና በምሁራን መማክርት ጉባዔ ትብብር ነው።

የመጽሐፉ ሕጋዊ የቅጂ ባለቤት © 2015 ዓ.ም. አብክመ ትምህርት ቢሮ ነው።

ምሁራን መማክርት ጉባዔ

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ

ማውጫ

መግቢያ v

ምዕራፍ 1

ጥበብን መገንዘብ

1.1 በዕይታዊ ጥበባት አናስሮች እና የዲዛይን መርሆች ሥዕሎችን ማደራጀት 2

1.1.1 የዕይታዊ ጥበባት አናስሮች ሥዕልን ለማደራጀት ያላቸው ጠቀሜታ . 2

1.1.2 የዲዛይን መርሆች በሥዕል ስራ ውስጥ ያላቸው ጠቀሜታ 5

1.2 የኢትዮጵያ ባህላዊ ሙዚቃ፣ የሙዚቃ መሳሪያዎች፣ ቅኝቶች እና ባህላዊ ውዝዋዜ 12

1.2.1. የኢትዮጵያ ባህላዊ ሙዚቃ 12

1.2.2 የሙዚቃ መሳሪያዎች 14

1.2.3 የኢትዮጵያ ቅኝቶች 27

1.2.4. የኢትዮጵያ ባህላዊ ውዝዋዜ ምድቦች (Folk Dance) 36

1.3 የፊልም እና የቴያትር መሰረታዊ የአዘገጃጀት ደረጃዎች 39

1.3.1 የፊልም መሰረታዊ የአዘገጃጀት ደረጃዎች 39

1.3.2 የቴያትር መሰረታዊ የአዘገጃጀት ደረጃዎች..... 40

ምዕራፍ 2

ሥነ-ጥበባትን በፈጠራ መግለጽ

2.1 የሙዚቃ ንባብ..... 49

2.1.2 በአንችሆየ እና በአምባስል ቅኝት የተጻፉ ሙዚቃዎችን እያዩ ማንበብ 54

2.2 የባህላዊ ውዝዋዜ አተገባበር 56

2.3. ቴያትር እና ፊልምን መተግበር 58

2.3.1 የቴያትር የልምምድ ሂደት..... 58

2.4. በሻማ ማቅለም (Batik) 64

2.5 በሐር ጨርቅ ማተም (Silk screen printing) 66

2.6 ኪነ-ቅርፅ (Sculpture) 69

2.6.1 ካስቲንግ (Casting) 69

2.6.2 በሸክላ አፈር ቅርፅ መስራት..... 71

2.6.3 ወረቀትን በማቡካት ቅርፅ መስራት (ፔፐር ማሼ) 72

ምዕራፍ 3

ባህልና ታሪክ

3.1 የባህላዊ ሙዚቃ፣ የሙዚቃ መሳሪያዎች እና የውዝዋዜ ባህላዊ ምልከታ 80
3.1.1 የባህላዊ ሙዚቃ ባህላዊ እና ታሪካዊ ምልከታ 80
3.1.2 የሙዚቃ መሳሪያዎች ባህላዊ እና ታሪካዊ ምልከታ 83
3.1.3 የባህላዊ ውዝዋዜ ባህላዊ እና ታሪካዊ ምልከታ 85
3.2 የኢትዮጵያ ጥንታዊ ሀውልቶች እና የዕደ-ጥበብ ስራዎች 87
3.2.1 የኢትዮጵያ ጥንታዊ የሀውልት ስራዎች 87
3.2.2 የኢትዮጵያ ጥንታዊ የዕደ-ጥበብ ስራዎች 92
3.3 አካባቢያዊ ታሪኮች ለቴያትር እና ለፊልም ያላቸው አስተዋጽዖ 98

ምዕራፍ 4

ሥነ-ውበታዊ ጠቀሜታ

4.1 የክውን ጥበባት ጠቀሜታዎች 104
4.1.1 የክውን ጥበባት ሥነ-ውበታዊ ጠቀሜታ 105
4.1.2 የክውን ጥበባት ባህላዊ (ብሔራዊ) ጠቀሜታ 105
4.1.3 የክውን ጥበባት ሥነ-ልቦናዊ ጠቀሜታ 106
4.2 ዕይታዊ እና ክውን ጥበባትን ማወዳደር 108
4.3 የሀውልቶች እና የዕደ- ጥበብ መስሪያ መሳሪያዎች እና መልዕክቶቻቸው 109
4.3.1 የሀውልቶች መስሪያ መሳሪያዎች እና የሚያስተላልፉት መልዕክት ... 109
4.3.2 የዕደ-ጥበብ መስሪያ መሳሪያዎች እና የሚያስተላልፉት መልዕክት 113

ምዕራፍ 5

የሥነ-ጥበባት ትምህርት ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ያለው ዝምድና

5.1 የሥነ-ጥበባት ትምህርት ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ያለዉ ዝምድና 121
5.1.1. ክውን ጥበባት ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ያላቸው ዝምድና 122
5.1.2 የዕይታዊ ጥበባት ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ያላቸው ዝምድና .....
..... 127
5.2 ሥነ-ጥበባትን ከወቅታዊ ጉዳዮች ጋር ማስተሳሰር 134

መግቢያ

ሥርዓተ ትምህርቱን ማዘጋጀት ለምን አስፈለገ?

ከሥርዓተ-ትምህርቱ ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመፍታት የተለያዩ ጥናት እና ምርምሮች ተካሂደዋል። ከእነዚህም አንዱ በሀገር አቀፍ ደረጃ በስፋት የተካሄደው የትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ-ካርታ ጥናት ዋናው ነው። ይህ እና ሌሎችም ተመሳሳይ ርእሶች ዙሪያ የተካሄዱት ጥናትና ምርምሮች ሥርዓተ ትምህርቱ በይዘት የታጨቀ፣ በትምህርት አይነቶች ብዛት የተወጠረ፣ በአብዛኛው ይዘት ማስታዎስን ትኩረት ያደረገ፣ ከተማሪዎችና ከማህበረሰቡ ህይወትና ኑሮ፣ ምርታማነት እንዲሁም ከሀገር በቀል እውቀት ጋር ያልተቆራኘ፣ ተማሪዎች ተገቢውን ግብረገባዊ እውቀትና ክህሎት እንዲላበሱ ያላደረገ፣ በቴክኖሎጂ ያልተደገፈ እና ልዩ ፍላጎትና ልዩ ተሰጥኦ ያላቸውን ተማሪዎች በተገቢው መንገድ ከማስተናግድ አኳያ ክፍተት ያለበት መሆኑ ተመላክቷል። በተጨማሪም ስርዓተ ትምህርቱ የ21ኛው ክፍለ ዘመን የሚጠይቀውን እውቀትና ክህሎት ማለትም ለመማር መማርን፣ በጥልቀት ማሰብና ችግር ፈችነትን፣ የፈጠራ አስተሳሰብና አዳዲስ ግኝቶች ማፍለቅን፣ ተግባቦትን፣ ትብብርን፣ መሪነትና ውሳኔ ሰጭነትን፣ የቴክኖሎጂ እውቀትን እና የባህል ማንነትና አለማቀፋዊ ዜግነትን ማስጨበጥ የማይችል መሆኑን በማመላከት የሥርዓተ-ትምህርት መሻሻል እና ለውጥ እንዲካሄድ የሚያመላክቱ ምክረ-ሃሳቦችን ሰንዝረዋል።

ይህንን መነሻ በማድረግም ሰፊ የውይይት እና የምክክር መድረኮች ተዘጋጅተው ህብረተሰቡ እንዲወያይ በማድረግ የለውጥ መርሃ ግብሮች ተቀርፀው ወደ ትግበራ ተገብቷል። ከእነዚህ የለውጥ መርሃ ግብሮች ውስጥ አንዱ አዲስ የአጠቃላይ ትምህርት ሥርዓተ-ትምህርት መቅረጽ ሲሆን ቀደም ሲል የነበሩትን ችግሮች ለመቅረፍ በሚያስችል መልኩ የሥርዓተ-ትምህርት ለውጥ ዝግጅት ተድርጓል።

በዚህም መሠረት አዲሱን የአጠቃላይ ትምህርት ሥርዓተ-ትምህርት ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻል በመጀመሪያ ለመማሪያ ማስተማሪያ መጻሕፍት ዝግጅት የሚያግዙ ሰነዶች ማለትም የተማሪው የባህሪ ገጽታ፣ የሥርዓተ-ትምህርት ማዕቀፍ፣ የይዘት ፍሰት፣ ተፈላጊ የመማር ብቃት እና መርሃ-ትምህርቶች እንደ ሀገር ተዘጋጅተዋል። በእነዚህ ሰነዶች መነሻነትም በክልላችን የመጀመሪያ ደረጃ(ከ1ኛ-6ኛ) እና የመካከለኛ ደረጃ(7ኛና 8ኛ) ክፍሎች የየትምህርት አይነቶች የተማሪዎች መማሪያ እና የመምህራን ማስተማሪያ መጽሐፍት ተዘጋጅተዋል።

የመጻሕፍት አተገባበር

መጽሐፉ ተማሪዎች ከዚህ ቀደም ከሚያውቁትና ከአካባቢያቸው ይዘውት ከሚመጡት ተሞክሮና እውቀት በመነሳት ተግባር ተኮር እና አሳታፊ በሆነ መልኩ እንዲማሩ ሆኖ ስለተዘጋጀ ተማሪዎች ትምህርቱን በጥልቀት ይገነዘቡታል ወይም ይረዱታል ተብሎ ይታመናል። ተማሪዎችና መምህራን አካባቢያቸውን እና ያካበቱትን ዕውቀትና ተሞክሮ መሰረት በማድረግ በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ የተለያዩ ተግባራትን በአግባቡ በመተግበር ተማሪዎቻችን ይዘቶችን መማር ብቻ ሳይሆን የመማር ክህሎታቸውን እንዲያሳድጉ ይጠበቃል። በመሆኑም መምህራን ለይዘቱ ተስማሚ ተብለው የተጠቆሙ የማስተማሪያ እና መማሪያ ዘዴዎችን በአግባቡ በመተግበርና ሌሎች ተገቢ ዘዴዎችን ተጨባጭ ሁኔታንና የተማሪዎችን አቅምና ፍላጎት መሰረት አድርጎ በመምረጥ ተማሪተኮር /አሳታፊ አድርገው የመማር ማስተማሩን ተግባር መፈጸም የሚጠበቅባቸው ሲሆን ተማሪዎች ደግሞ በትምህርቱ ክፍለ ጊዜ መጽሐፍቱን ከእጃቸው ሳይለዩ ትምህርቱን መከታተል ይኖርባቸዋል።

ውድ ተማሪዎቻችን!

መጽሐፉን በጥንቃቄ በመያዝ በአግባቡ መጠቀም አለባችሁ። በማንኛውም አገርና ሁኔታ መማር የትውልድን የወደፊት ሁኔታ ይወስናል። መማር ለማንኛውም ማህበራዊ፣ ሰብዓዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት መሰረት ነው። በመጽሐፉ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ተግባራት፣ ይዘቶችና ጥያቄዎች በአግባቡ በመስራትና በማጥናት ጥልቀት ያለው ክህሎትን እና ግንዛቤን ማዳበር ይገባችኋል።

ውድ ወላጆች/ አሳዳጊዎች!

የተማሪዎችን መማር የተሳለጠ ለማድረግ የመማሪያ መጻሕፍት ያላቸው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው። ስለሆነም ተማሪዎች መጽሐፉን በጥንቃቄ ይዘው እንዲጠቀሙ ማድረግ ይኖርባችኋል። ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎች መጽሐፉን ት/ቤት ይዘው እንዲሄዱ ማበረታታት፣ ከመምህሮቻቸው የሚሰጡ ተግባራትን በትክክል እንዲፈጽሙና እንዲያጠኑ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣ ትምህርት ቤት በመሄድ ከመምህራን ጋር በመገናኘት ስለ ልጅዎ የመማር ዕውቀትና የባህሪ ለውጥ በመጠየቅ ክፍተቱን በመለየት ምክር በመሥጠት ማስተካከል ይጠበቅባችኋል። በመሆኑም ትምህርት የሁሉም ነገር መሰረት መሆኑን በመገንዘብ መማርን ከመንግስት ስራ መያዝ ጋር ብቻ ሳታቆራኙት/ሳያያይዙት ልጆችን ሁልጊዜ ወደትምህርት ቤት መላክ አለባችሁ።

ምዕራፍ 1

ጥበብን መገንዘብ

የምዕራፉ ዓላማዎች፦

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፦

- የዕይታዊ ጥበባት አናስሮች በሥነ- ጥበብ ስራ ያላቸውን ጠቀሜታ ትረዳላችሁ።
- የዲዛይን መርሆች በሥነ-ጥበብ ስራ ያላቸውን ጠቀሜታ ታውቃላችሁ።
- የዕይታዊ ጥበባት አናስሮችና የዲዛይን መርሆችን በመጠቀም ሥነ-ጥበባዊ ስራ ትሰራላችሁ።
- የሙዚቃ መሳሪያ ምድቦችን ታውቃላችሁ።
- የኢትዮጵያ ሙዚቃን አውዳዊ ምድቦች ትረዳላችሁ።
- የቴያትር እና የፊልም ጥበባት መሰረታዊ የአዘገጃጀት ደረጃዎች ታውቃላችሁ።
- የባህላዊ ውዝዋዜ ምድቦች ታውቃላችሁ።
- የኢትዮጵያ መሰረታዊ ቅኝቶች በመለየት በተለያዩ ቁልፎች መመስረት ትችላላችሁ።
- በኢትዮጵያ መሰረታዊ ቅኝቶች የተፃፉ ድምፆችን እና መዝሙሮችን ማንበብ ትችላላችሁ።
- ለሙዚቃ ጥበብ አድናቆት ትሰጣላችሁ።

መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ በዕይታዊ ጥበባት አናስሮች እና የዲዛይን መርሆች ሥዕሎችን ማደራጀት፣ የዕይታዊ ጥበባት አናስሮች ሥዕልን ለማደራጀት ያላቸው ጠቀሜታ፣ የዲዛይን መርሆች በሥዕል ስራ ውስጥ ያላቸው ጠቀሜታ፣ የኢትዮጵያ ዋና ዋና

ባህላዊ ሙዚቃዎች ምድቦች፣ የሙዚቃ መሳሪያዎች እና ውዝዋዜ ምድቦችን፣ የፊልም እና የቴያትር መሰረታዊ የአዘገጃጀት ደረጃዎችን በዝርዝር የምትማሩበት ምዕራፍ ነው።


1.1 በዕይታዊ ጥበባት አናስሮች እና የዲዛይን መርሆች ሥዕሎችን ማደራጀት

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጥሞና ካነበባችሁ በኋላ ተገቢውን ምላሽ ስጡ።

1. የዕይታዊ ጥበባት አናስሮችን በመዘርዘር ምንነታቸውን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራርታችሁ ተናገሩ።
2. የዕይታዊ ጥበባት አናስሮችን በአግባቡ በመጠቀም የተሳካ የዲዛይን ስራ ለመስራት የሚያስችሉን መርሆችን በመዘርዘር ምንነታቸዉን ለጓደኞቻችሁ አብራርታችሁ ተናገሩ።

1.1.1 የዕይታዊ ጥበባት አናስሮች ሥዕልን ለማደራጀት ያላቸው ጠቀሜታ



ሥዕል 1 የሠዓሊ አገኘሁ እንግዳ ፖርትሬት ቀለም ቅብ (ከኤልሳቤጥ ወ/ጊዮርጊስ ሞደርኒስት አርት ኢትዮጵያ የተወሰደ)


ተማሪዎች ከላይ በሥዕል 1 ላይ የሠዓሊ አገኘሁ እንግዳን የራስ ምስል ሥዕል በትኩረት ስንመለከት በሥዕሉ ውስጥ ቀለም፣ ቦታ፣ ቴክስቸር፣ ቅርፅ፣ መስመር እና ነገር ያላቸውን ጠቀሜታ በትክክል መገንዘብ እንችላለን።

በሥዕሉ ውስጥ ገፀባህሪውን በትክክል እንዲለይ እና የሰዓሊው ሀሳብ ጎልቶ እንዲቀመጥ የዕይታዊ ጥበባት አናስሮች ትልቅ ሚና አላቸው። ገጸባህሪው ምን አይነት መልክ አለው? ልብሱ፣ ገላው፣ ፀጉሩ ምን አይነት መልክ አለው? ምን አይነት እንቅስቃሴ እና ቅርፅ አለው? በምን አይነት ስሜት ውስጥ ነው ያለው? የሚሉትን መሰረታዊ ጥያቄዎች የሚመልሱልን የዕይታዊ ጥበባት አናስሮች ናቸው። ተማሪዎች ከዚህ በታች ያሉት ሥዕሎች የዕይታዊ ጥበባት አናስሮችን ምንነት በምሳሌ ለመረዳት የተቀመጡ ስለሆነ በሚገባ በመመልከት የሥነ- ጥበብ አናስሮችን ጠቀሜታ ትገነዘባላችሁ።






ሥዕል 2 በቀለም ቅብ ሥዕል ውስጥ የመስመር ምሳሌ



ሥዕል 3 ቀለም በቀለም ቅብ ሥዕል ውስጥ




ስዕል 4 ቴክስቸር በቀለም ቅብ ሥዕል ውስጥ



ሥዕል 5 ዝርግ ቅርፅ /shape/ በሥዕል ውስጥ



ሥዕል 6 ፎርም /form/ በሥዕል ውስጥ



ሥዕል 7 ቦታ /Negative and Positive Space/ በስዕል ውስጥ

አንድን የዕይታዊ ጥበባት ስራ በተሳካ ሁኔታ ለመስራት እነዚህ የዕይታዊ ጥበባት አናስሮች ትልቅ ሚና አላቸው። መስመር፣ ቀለም፣ ቅርፅ፣ ቦታ፣ ቴክስቸር እና ፎርም በዋናነት የሥዕል መሳሪያዎችን በመጠቀም ሥዕል በምንሰራበት ሰሌዳ ላይ በማሳረፍ ሀሳባችንን እና ስሜታችንን እውን የምናደርግባቸው፤ የተሳካ አረፍተ ነገር የምንመሰርትባቸው የሰዓሊያን ቃላት ናቸው። የዕይታዊ ጥበባት አናስሮችን ተጠቅመን ልዩ ልዩ ስሜቶቻችንን በሥዕል መግለጽ እንችላለን።

ተግባር 1.1

1. ተማሪዎች በጥንድ በመሆን በአካባቢያችሁ የምታገኙትን የሥዕል ስራ በምሳሌነት በመውሰድ በሥዕሉ ውስጥ ያሉ የዕይታዊ ጥበባት አናስሮችን ለይታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ።
2. ተማሪዎች በምሳሌነት ከወሰዳችሁት የሥዕል ስራ በመነሳት የዕይታዊ ጥበባት አናስሮችን ጠቀሜታ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በሚገባ አብራርታችሁ ተናገሩ።


1.1.2 የዲዛይን መርሆች በሥዕል ስራ ውስጥ ያላቸው ጠቀሜታ

የዲዛይን መርሆች ስንል የዕይታዊ ጥበባት አናስሮችን ለማሰናዳትና በአግባቡ ለመጠቀም ወይም ጥሩ ዲዛይን ለማዘጋጀት የሚያስችሉን መርሆች ናቸው። ይህም ማለት የተሳካ ጥሩ ሥዕል ለመስራት ቀለምን፣ መስመርን፣ ቴክስቸርን፣ ቅርፅን እና ቦታን እንዴት መተግበርና መጠቀም እንዳለብን የሚመሩን መርሆች ናቸው።

ለአንድ አረፍተ ነገር ሰዋሰዋዊ ስርዓት እንዳለው ሁሉ የዕይታዊ ጥበባት አናስሮችንም ተጠቅሞ ዲዛይን ለመስራት መርህ ወይም ህግ ያስፈልጋል። ለምሳሌ ቀለም ስላለን ብቻ የተሳካ ዲዛይን ሰራን ማለት አይደለም።

ቀለምን በምን አግባብ መጠቀምና ለስሜታችን ውክልና መስጠት ያስፈልገናል የሚለውን ጥያቄ መመለስ አለብን። ይህን ለመወሰን የሚያስችሉን መርሆች የዲዛይን መርሆች ይባላሉ። የዲዛይን መርሆች የምንላቸው ንጽጽር፣ ሚዛን፣ ማመጣጠን፣ ምትና ድግግሞሽ፣ እንቅስቃሴ፣ ቅለት፣ አፅንኦት፣ ውህደት እና አንድነት ናቸው።


ንጽጽር (contrast)፦ ንጽጽር አናስሮችን በወደረኝነት ለመጠቀም የሚያስችለን ህግ ነው።



ሥዕል 8 ንጽጽር /Contrast/ በሥዕል ውስጥ


ሚዛን (Balance)፦ በሥነ- ጥበባዊ ድርሰታችን ውስጥ እኩል የሆነ የዕይታ ሚዛናዊነት እንዲኖር የሚያስችለን መርህ ሲሆን የዕይታዊ ጥበባት አናስሮችን በእኩል የማስቀመጥ ሂደት ነው። ይህም በዲዛይናችን ውስጥ ያለውን የዕይታ ትኩረት ከአንድ ቦታና አቅጣጫ ወደሁሉም የድርሰቱ ክፍል እንድናሳርፍ የሚስችለን ነው።

የሚዛን አይነቶች




ሥዕል 9 የሚዛን አይነቶች

የሚዛን አይነቶች ሦስት ሲሆኑ የመጀመሪያው እኩል የሆነ ሚዛን ይባላል። ይህም እኩል የሆኑ ነገሮችን እኩል ዕይታ እንዲያገኙ ሚዛናዊ በሆነ መንገድ የማስቀመጥ ሂደት ነው።



ሥዕል 10 እኩል የሆነ ሚዛን ምሳሌዎች

ሁለተኛው እኩል ያልሆኑ ነገሮችን እኩል ዕይታ በሚያገኙበት መንገድ ሚዛናዊ አድርጎ የማስቀመጥ ሂደት ነው። የሥነ -ጥበብ አናስሮችን በሚዛናዊነት ስንጠቀም ድርሰታችንን ሚዛናዊ የምናደርግበት መንገድ በቀጥታ እኩልና አንድ አይነት አናስሮችን ስንጠቀም ሂደቱ ቀላል ይሆናል። ነገር ግን የምንጠቀማቸው አናስሮች እኩልና አንድ አይነት ካልሆኑ እኩልነቱን ለማምጣት ወይም ሚዛናዊ ለማድረግ የምንጠቀመው ሂደት ከባድ ይሆናል። ይህም እኩል ባልሆነ ሚዛን ድርሰታችን ውስጥ ሚዛናዊ የሆነ ዕይታን የምንፈጥርበት ሂደት ነው።




ሥዕል 11 እኩል ያልሆነ ሚዛን ምሳሌዎች

ሦስተኛው ራዲያል ሚዛን ይባላል። ይህም ሁሉም አናስሮች ከማዕከላዊው በመነሳት የሚኖራቸው እኩል የዕይታ ሚዛናዊነት ነው። ራዲያል ሚዛን ከመካከል የሚነሳ እና ሁሉም አናስሮች በእኩል መጠን የሚኖራቸው ሚዛናዊነት ነው።




ሥዕል 12 የራዲያል ሚዛን ምሳሌ

ማመጣጠን (Proportion)፦ በድርሰታችን ውስጥ ያለውን የነገሮች ተገቢነት እና መጣኝነት የሚያመላክት ነው። ማመጣጠን እኩል እና ሚዛናዊ ከማድረግ የሚለየው በተገቢነት የሚገለጽ መሆኑ ነው። ለምሳሌ አንድ ሰው እና አንድ ትልቅ ዋርካ ወይም አንድ ሰውና ሰውየው የሚኖርበት ቤት ሊኖራቸው የሚገባው መመጣጠን ነገሮቹን በምናስተውልበት ቦታ ቅርበትና ርቀት ተወስነን ተፈጥሯዊ ልዩነታቸውን ሳናዛባ ማስቀመጥ ማለት ነው።




ሥዕል 13 የማመጣጠን ምሳሌ


ምት እና ድግግሞሽ (Rhythm and Repetition)፦ በዲዛይናችን ውስጥ ተደጋግመው የሚቀመጡት አናስሮች ስርዓትና ስልታዊነት የሚፈጥረው ስሜት ነው። ይህም የተስተካከለ እና እኩል የሆነ የአናስሮች መደጋገም ወይም ድግግሞሽ የተሻለ ምት ወይም ወጥነት ይሰጠናል።



ሥዕል 14 የምትና ድግግሞሽ ምሳሌዎች

አጽንኦት (Emphasis)፦ ከአናስሮች መካከል የተወሰኑትን በማብዛት ወይም በማግዘፍ የድርሰታችንን ትኩረትና እይታን የምንጠቀምበት ሂደት ነው።






ሥዕል 15 አጽንኦት የመስጠት ምሳሌ ስዕሎች

እንቅስቃሴ (Movement)፦ የተመልካችን አይን ከአንዱ ክፍል ወደሌላው በመውሰድ በድርሰቱ ውስጥ የሚካሄደውን ድርጊትና ሁኔታ ወይም ሀሳብ የሚያመላክተን ነው።





ሥዕል 16 የእንቅስቃሴ ምሳሌዎች

ቅለት (Simplicity)፦ በዲዛይናችን ውስጥ ውስን የሆኑ የዕይታዊ ጥበባት አናስሮችን መጠቀም ማለት ነው።





ሥዕል 17 የቅለት ምሳሌዎች

አንድነት (Unity)፦ የአናስሮች ሁሳራና አጠቃላይ የሚፈጥሩት አንድነት ነው።





ሥዕል 18 ለአንድነት ምሳሌ የሚሆኑ ስዕሎች

ውህደት፦ የተለያዩ ቀለሞችን በማዋሃድ በዲዛይን ስራችን ላይ ለተመልካች አስማምተን የምንሰራበት መርህ ነው።



ሥዕል 19 የውህደት ምሳሌ በቀለም ቅብ (እጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ “እናት” የተሰኘ ሥዕል 1963ዓ.ም የተወሰደ)

ተግባር 1.2

1. ተማሪዎች ይህን ከላይ የተቀመጠውን ሥዕል ምሳሌ በማድረግ በሥዕሉ ውስጥ ካሉ የዕይታዊ ሥነ-ጥበብ አናስሮች መካከል ሰዓሊው የተጠቀማቸውን ቀለማት ለይታችሁ ለጓደኞቻችሁ አሳዩ።

2. ተማሪዎች ይህን ከላይ የተቀመጠውን ሥዕል ምሳሌ በማድረግ በሥዕሉ ውስጥ ካሉ የዕይታዊ ስነ ጥበብ አናስሮች መካከል በሥዕሉ ውስጥ ያሉ የሸካራነትና የልስላሴ ደረጃ በመለየት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ።

3. ተማሪዎች ይህን ከላይ የተቀመጠውን ሥዕል ምሳሌ በማድረግ በሥዕሉ ውስጥ ካሉ የዕይታዊ የዲዛይን አናስሮች መካከል የሥዕሉን ቦታ (negative and positive space) በሥዕል ደብተራችሁ ላይ በእርሳስ በመንደፍ ለመምህራችሁ አሳዩ።

4. ተማሪዎች ይህን ከላይ የተቀመጠውን ሥዕል ምሳሌ በማድረግ በሥዕሉ ውስጥ ካሉ የዕይታዊ የዲዛይን አናስሮች መካከል መስመርን በሥዕል ደብተራችሁ ላይ በእርሳስ በመንደፍ ለመምህራችሁ አሳዩ።

5. ተማሪዎች መሰረታዊ የዲዛይን መርሆችን በመጠቀም በሥዕል ደብተራችሁ ላይ ዲዛይን በመስራት ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ።

6. የዕይታዊ ጥበባት አናስሮችን ጠቀሜታ በአካባቢያችሁ ያሉ የሥነ-ጥበብ ባለሙያዎችን በመጠየቅ የዕይታዊ ጥበባት አናስሮች ምንነት አብራርታችሁ ተናገሩ።

1.2 የኢትዮጵያ ባህላዊ ሙዚቃ፣ የሙዚቃ መሳሪያዎች፣ ቅኝቶች እና ባህላዊ ውዝዋዜ

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጥሞና ካነበባችሁ በኋላ ተገቢውን ምላሽ ስጡ።

1. ስለ ቅኝት የምታውቁትን ተናገሩ።
2. ባህላዊ ሙዚቃዎች በአካባቢያችሁ በምን በምን ሁነቶች ይከወናሉ?
3. ሙዚቃ ስታዳምጡ ምን ይሰማችኋል? መልሳችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።
4. ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ለማህበረሰቡ የሚሰጡትን ጠቀሜታ ግለፁ።
5. ባህላዊ ውዝዋዜ ከአንድ አካባቢ ማህበረሰብ ባህል ጋር ያለውን ዝምድና ግለፁ።

1.2.1. የኢትዮጵያ ባህላዊ ሙዚቃ

የኢትዮጵያ ባህላዊ ሙዚቃዎች የማህበረሰቡ ነፀብራቆች ሲሆኑ የሚፈጠሩትም ማህበረሰቡ ውስጥ ባሉ የጥበብ ፈጠራ ችሎታ ባላቸው ሰዎች ነው። እነዚህ ባህላዊ ሙዚቃዎች በዘመን ሂደት ለውጥን እና መሻሻልን እያደረጉ በጊዜው ከሚፈጠሩ ሁኔታዎች ጋር እየተስማሙ ከማህበረሰቡ ጋር አብረው የሚኖሩ ናቸው።

ባህላዊ ሙዚቃዎች በማህበረሰቡ እምነቶች፣ ልማዶች፣ ኃይማኖታዊ ስርዓቶች፣ የስራ ባህል እና አጠቃላይ የማህበረሰቡ እንቅስቃሴዎች ላይ የተመሰረቱ ናቸው። እነዚህ መሰረታዊ የሆኑ እምነቶች፣ ልማዶች፣ ስርዓቶች እና መሰል ማህበራዊ ሁነቶች ከሰው ልጅ መንፈሳዊ እና ዓለማዊ ፍላጎት አንፃር የተለያዩ አውዶች አሏቸው።

ተግባር1.3

1. የኢትዮጵያ ባህላዊ ሙዚቃዎች ለዘመናዊ ሙዚቃ እድገት ያደረጉትን አስተዋፅኦ አብራሩ።
2. ባህላዊ ሙዚቃ ከማህበረሰቡ ባህል ጋር እንዴት አብሮ እያደገ እንደመጣ ማብራሪያ ስጡ።

የኢትዮጵያ ሙዚቃ የተለያየ ታሪካዊ እና ባህላዊ መሰረት ያለው መሆኑን የሙዚቃ ተመራማሪዎች ይናገራሉ። ከእነዚህ የሙዚቃ ተመራማሪዎች መካከል ዘነበ በቀለ የኢትዮጵያ ሙዚቃን የሚገልፁት ሃሳቦች እና የክዋኔ አውዶች መሰረት በማድረግ በአራት ዋና ዋና ምድቦች መድቧቸዋል። እነርሱም፦ ማህበራዊ፣ ኃይማኖታዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ምድብ ናቸው። ትኩረት የሚያደርጉትም እንደሚከተለው ነው።

ማህበራዊ ምድቡ በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች በሚፈጠሩ እንደ ልደት፣ ሰርግ፣ ሞት እና የመሳሰሉት ሁነቶች ጋር ተያይዞ የሚፈጠሩ በዜማ የሚገለፁ ሃሳቦችን የሚያካትት ነው።

ኃይማኖታዊ ምድቡ በተለያዩ ኃይማኖታዊ ሥርዓቶች ላይ የሚዜሙ ዝማሬዎችን እና በልማዳዊ አምልኮቶች ላይ የሚከወኑ የዛር ሙዚቃ (ዛር ጨቸት) ዘፈኖችን የሚያጠቃልል ነው።

ፖለቲካዊ ምድቡ የብሄራዊ መዝሙሮች በዚህ ውስጥ ይካተታሉ።

ኢኮኖሚያዊ ምድቡ ስራን ለማቅለል እና ኢኮኖሚን በማሳደግ ላይ ትኩረት የሚያደርጉ እንደ ዓሣ ማጥመድ፣ እንጨት መቁረጥ፣ ቡና ለቀማ እና ገቢን ለማሳደግ በሚደረጉ ስራዎች ላይ የሚዘፈኑ ዘፈኖችን የሚያካትት ነው።

ተግባር 1.4

1. በአካባቢያችሁ ለስራ፣ ለኃይማኖታዊ ሥርዓቶች፣ ለፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ጉዳዮች የሚዜሙ ሙዚቃዎችን በማሰባሰብ በግጥም እና በዜማ በማቅረብ የሚያስተላልፉትን መልዕክት ለመምህራችሁ ተናገሩ።
2. የባህላዊ ሙዚቃን ትርጉምና ለማህበረሰቡ የሚሰጠውን ጠቀሜታ አብራሩ።

1.2.2 የሙዚቃ መሳሪያዎች

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. በአካባቢያችሁ የሚገኙትን ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች በመዘርዘር ጥቅማቸውን ተናገሩ።
2. ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች እንዴት ይዘጋጃሉ?
3. የምታውቋቸዉን ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ለክፍል ጓደኞቻችሁ ዘርዝሩላቸዉ።

1.2.2.1 የኢትዮጵያ ዋና ዋና ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች

ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች በአካባቢያዊ ቁሳቁሶች በማህበረሰቡ እውቀት እና ክሂሎት የሚዘጋጁ ናቸው። እነዚህ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች እንደየማህበረሰቡ እውቀት እና ችሎታ የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ። ምክንያቱም ሳይንሳዊ ልኬቶችን መሰረት አድርገው የሚዘጋጁ ባለመሆናቸው እና ከቦታ ቦታ በተለያዩ ባለሙያዎች እውቀት የሚሰሩ በመሆናቸው በአንድ አይነት የሙዚቃ መሳሪያ ላይ የተለያየ ውፍረት እና ቅጥነት ያላቸው የድምፅ ባህሪያት ሊያወጡ ይችላሉ።

ለምሳሌ መሰንቆ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል የሚገኝ እና የሚዘጋጅ ሲሆን በተለያዩ ቦታዎች እና ባለሙያዎች በመሰራቱ ምክንያት የተለያየ መጠን እና ርዝመት ይኖረዋል፡፤ ይህ በመሆኑ የተለያየ የድምፅ ውፍረት እና ቅጥነት ሊያመጣ ይችላል።

ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች በማህበረሰቡ የሚከወኑ ባህላዊ ዜማዎችን በማጀብ፣ መሰረታዊ ስልተ ምቶችን በማጠናከር እና ድምቀት በመስጠት ከፍተኛ የሆነ ሙዚቃዊ ፋይዳ ያላቸው ከመሆኑም በተጨማሪ የአንድ ማህበረሰብ ቁሳዊ ባህል ሆነው ቁሶቹ የሚሰሩበትን እውቀት እና ትዕምርቶችን ጭምር የሚያሳዩ ናቸው።

በኢትዮጵያ የሚገኙ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ከሚሰሩበት ቁስ እና ለመጫወት ከሚያስችሉ ብልሃቶች አንፃር በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ይመደባሉ። እነርሱም፦

- የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች
- የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያዎች
- የክር የሙዚቃ መሳሪያዎች ናቸው።

በኢትዮጵያ የሚገኙ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት እና በስዕላዊ መግለጫ ትንታኔ ተሰጥቷቸው የተቀመጡት የክር፣ የትንፋሽ እና የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች እነዚህ ብቻ አለመሆናቸውን መረዳት ያስፈልጋል። ይሁን እንጅ በዋናነት በሀገራችን ደረጃ ጥቅም ላይ በመዋል ጎልተው የሚታወቁ እና ለዚህ ክፍል ደረጃ ይመጥናሉ ተብለው የታሰቡ መሆኑን ታሳቢ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

ባህላዊ የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች

የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች አንዱን አካል ከሌላኛው አካል ጋር በማጋጨት ድምጽ መፍጠር የሚችሉ ሲሆን የሙዚቃውን የጊዜ ሂደት የሚያስጠብቁ እና ሙዚቃውን የሚያደምቁ ናቸው። በመሆኑም ለማህበራዊ እና ኃይማኖታዊ ሥርዓቶች ተብለው በሚከወኑ የባህል ሙዚቃዎች ላይ የበለጠ ስሜት መስጠት የሚችሉ በርካታ ባህላዊ የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች በሀገራችን ይገኛሉ። ከነዚህም ውስጥ እንደ ከበሮ፣ አታሞ፣ ነጋሪት፣ ድቤ፣ ፀናፅል፣ ወዘተ የሚጠቀሱ ናቸው።

ከበሮ፦ ከምት የሙዚቃ መሳሪያዎች የሚመደብ ወፍራም እና ቀጭን ድምፅ ማውጣት የሚችል ሲሆን ለመንፈሳዊ ዝማሬ ማጀቢያነት የሚያገለግል ባህላዊ የምት የሙዚቃ መሳሪያ ነው። ከበሮ ረጅም እድሜ ያለው ሲሆን መላው የከበሮው አካል እና አጨዋወቱ ሁሉ ታሪክ ነጋሪ በመሆኑ ታሪክን ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚያስተላልፍ ብርቅየ የሀገራችን የሙዚቃ መሳሪያ ነው።



ከበሮ ከተቦረቦረ ትልቅ ግንድ፣ ከጠፍር እና ጨርቅ የሚዘጋጅ በተለያዩ ክብረ በዓላት እና የቀብር ስነ ስርዓት ጥቅም ላይ የሚውል የሙዚቃ መሳሪያ ነው።



አታሞ፦ በመላው ኢትዮጵያ የሚገኝ ሲሆን ባህላዊ ዘፈኖችን የሚያደምቅ ሀገራዊ የምት የሙዚቃ መሳሪያ ነው። አታሞ በተለይም በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ልጅአገረዶች ከቦታ ቦታ በመንቀሳቀስ እና አንድ ቦታ ላይ በመሰባሰብ በሶለል፣ ሻደይ፣ አሸንድየ እና አሸንዳ በተባሉ የልጅአገረዶች በዓል ጊዜ የጨዋታውን ስልተ ምት በመጠበቅ እና በማድመቅ ጥቅም ላይ ይውላል። አታሞ እንደየ አካባቢው በሚሰራበት ቁሳቁስ እና በመጠን ይለያያል።



ነጋሪት፦ በሀገራችን ቀደምት ታሪክ ካላቸው ባህላዊ የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች አንዱ ሲሆን በነገስታቱ ዘመን ለአዋጅ መንገሪያነት ሲያገለግል የቆየ ነው። ነጋሪት ከባህላዊ የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች በአካሉ ትልቅ እና በተለያየ መጠን የሚዘጋጅ ነው።

አጨዋወቱም በሁለት መምቻ ዱላዎች/ሪትም ስቲክ/ የተወጠረውን ቆዳ በመምታት የተለያዩ መንግስታዊ እና ኃይማኖታዊ መልዕክቶችን በማስተላለፍ ጥቅም ይሰጥ የነበረ የሙዚቃ መሳሪያ ነው።



ድቤ፦ ከባህላዊ የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች የሚመደብ ነዉ። በቅርፁ ነጋሪትን የሚመስል ሲሆን በአካሉ ከምት የሙዚቃ መሳሪያዎች ትንሹ ነው። ቀጭን ድምፅ የሚያወጣ ሲሆን በአረፋ፣ በመውሊድ እና ሌሎች በዓላት ወቅት ዜማዎችን በማጀብ አገልግሎት የሚሰጥ ነው።



ፀናፅል፦ ከባህላዊ የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች የሚመደብ እና መላው አካሉ ድምፅ የሚሰጥ የምት የሙዚቃ መሳሪያ ነው። ፀናፅል በጥምቀት፣ መስቀል፣ ገና እና የተለያዩ በዓላት ወቅት ዜማዎችን በማጀብ አገልግሎት የሚሰጥ የምት የሙዚቃ መሳሪያ ሲሆን ለመንፈሳዊ ዜማ አገልግሎት ይዉላል።

ተግባር 1.5

1. ከላይ ከተዘረዘሩት ባህላዊ የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች በተጨማሪ የምታውቋቸውን በመዘርዘር ስለአሰራራቸውና ጠቀሜታቸው ማብራሪያ ስጡ።
2. ባህላዊ የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች ለማህበረሰቡ የሚሰጡትን ጠቀሜታ ዘርዝሩ።
3. የአታሞ እና የድቤ አንድነት እና ልዩነትን አብራሩ።
4. የነጋሪት እና የከበሮ አንድነት እና ልዩነትን አብራሩ።
5. በአካባቢያችሁ ከምትጠቀሙባቸው ባህላዊ የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች አንዱን በመጥቀስ ስለ አዘገጃጀቱ እና ለምን አገልግሎት እንደምትጠቀሙበት ማብራሪያ ስጡ።

ባህላዊ የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያዎች

የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያዎች በትንፋሽ አማካኝነት ድምጽ መፍጠር የሚችሉ ሲሆን ከንፈርን በማጥበቅ ወይም በማላላት የተለያዩ ቀዳዳዎችን በመዝጋት እና መልሦ በመክፈት የተለያዩ የድምፅ ባህሪያትን ማውጣት የሚችሉ ናቸው። ዜማን በመከተል ሙዚቃውን ጥንካሬ ለመስጠት እና ይበልጥ ውበት እንዲኖረው የማጀብ ተግባርም አላቸው።

እነዚህ ባህላዊ የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያዎች ማህበራዊ በሆኑ ጉዳዮች በሚፈጠሩ ሁነቶች ላይ የሚከወኑ በሀዘን፣ በደስታ እና መሰል አጋጣሚዎች ላይ ለሚዜሙ ዜማዎች የሚያገለግሉ ሲሆን በዘመናዊ መንገድ የሚቀናበሩ ሙዚቃዎችን ለማጀብም ጥቅም ላይ ይውላሉ።

በሀገራችን የሚገኙ የትንፋሽ ሙዚቃ መሳሪያዎች እንደየአካባቢው የተለያዩ ባህሪያት ያሏቸው ናቸው። ምሳሌ እንደ ጥሩምባ፣ ሁራ፣ መለከት፣ ሁልዱድዋ የመሳሰሉት ሁለት እና ሦስት ድምፅ ብቻ ማውጣት የሚችሉ ሲሆኑ እንደ ፋንፋ፣ ዋሽንት እና የመሳሰሉት ደግሞ አምስት እና ከአምስት በላይ ድምፆችን ማውጣት የሚችሉ ናቸው።

ሀ) ድምፀ ውስን ባህላዊ የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያዎች



መለከት፦ አንድ ወይም ሁለት ድምፆችን ብቻ ማውጣት የሚችል እና ለተለያዩ መንግስታዊ የክተትአዋጆች፣ ቤተመንግስት አካባቢ ለሚደረጉ ሥርዓቶች እና ለኃይማኖታዊ ክብረ-በዓላት ማድመቂያ ሆኖ የሚያገለግል ነው።



ጥሩምባ፦ በሀገራችን በሚከበሩ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ መንፈሳዊ እና ኢኮኖሚያዊ ክዋኔዎች ላይ መልዕክት በመንገር፣ ድምቀት በመስጠት እና በተለያዩ ማህበረሰባዊ ክስተቶች ጥቅም ላይ የሚውል ከነሀስ የሚሰራ ሁለት ድምፅ ብቻ ማውጣት የሚችል ባህላዊ የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያ ነው።



ዙምባራ፦ በቤንሻንጉል ክልል የሚገኝ ድምጸ ውስን የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያ ሲሆን በተለያዩ የክብረ በዓላት ስርዓቶች ላይ ጥቅም የሚሰጥ ነው። በስዕሉ ላይ እንደሚታየው ረጅም ሲሆን የሚያወጣውም ድምፅ ወፍራም ነው። ዙምባራ ከቀርቅሃ እና ከቅል አንገት የሚሰራ ባህላዊ የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያ ነው።

ለ) አምስት እና ከአምስት ድምፅ በላይ የሚያወጡ ባህላዊ የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያዎች

ፋንፋ፦ በሀገራችን የደቡባዊ ክፍል በሆነው ኮንሶ አካባቢ የሚገኝ የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያ ሲሆን በሙዚቃ ሳይንስ መሰረታዊ የሚባሉት ሰባት ድምፆች ማውጣት የሚችል ነው።



ፋንፋ የተለያየ መጠን እና ርዝመት ካላቸው ሸንበቆዎች የሚዘጋጅ ሲሆን የድርድር ስርዓቱ እንዳይፈርስ እና ቅደምተከተሉን የጠበቀ ድምፅ ማውጣት እንዲችል ሸንበቆዎቹ እንዲጣበቁ እና እንዲታሰሩ ይደረጋል።



ዋሽንት፦ የተለያየ የአንገ መጠን ካለው ሸንበቆ የሚዘጋጅ እና አራት የድምፅ ቀዳዳዎች ያሉት የሙዚቃ መሳሪያ ነው። በሀገራችን ለመንፈሳዊ ዜማዎች እና ዓለማዊ የሙዚቃ ስራዎች አገልግሎት የሚሰጥ ለስላሳ እና አሳዛኝ ድምፆችን እያወጣን ዜማ ለመጫወት እና ለተለያዩ የሙዚቃ መሳሪያዎች ቅኝት ለመስጠትም የሚያገለግለን የሙዚቃ መሳሪያ ነው።

ተግባር 1.6

1. ከላይ ከተዘረዘሩት ባህላዊ የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያዎች በተጨማሪ የምታውቋቸውን በመዘርዘር ስለአሰራራቸውና ጠቀሜታቸው ማብራሪያ ስጡ።
2. ባህላዊ የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያዎች ከባህላዊ የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች የሚያመሳስላቸውን እና ልዩነታቸውን ማብራሪያ ስጡ።
3. የፋንፋ እና የዋሽንት አንድነት እና ልዩነትን አብራሩ።
4. ጥሩምባ በአካባቢያችሁ ለምን ለምን አገልግሎት እንደምትጠቀሙበት ማብራሪያ ስጡ።
5. መለከት እንዴት ማዘጋጀት እንደምንችል ማብራሪያ ስጡ።
6. በአካባቢያችሁ ከሚዘወተሩ ባህላዊ የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያዎች መካከል አንዱን መርጣችሁ በማዘጋጀት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ።


ባህላዊ የክር የሙዚቃ መሳሪያዎች

የክር የሙዚቃ መሳሪያዎች በተወጠሩ የክር ንዝረት ወይም ደግሞ እርግብግቦሽ አማካኝነት ድምጽ መፍጠር የሚችሉ ሲሆን ክሮቹን በመግረፊያ በመግረፍ ወይም በመደርደር እና በመገዝገዝ የተለያዩ የድምፅ ባህሪያትን ማውጣት የሚችሉ ናቸው። ዜማን በመከተል ሙዚቃውን ጥንካሬ ለመስጠት እና ይበልጥ ሙዚቃው ውበት እንዲኖረው የማጀብ ተግባርም አላቸው።

እነዚህ የክር ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ማህበራዊ በሆኑ ጉዳዮች በሚፈጠሩ ሁነቶች ላይ የሚከወኑ እና በሀዘን፣ በደስታ እና መሰል አጋጣሚዎች ላይ ለሚዜሙ ዜማዎች ማጀቢያነት የሚያገለግሉ ሲሆን በዘመናዊ መንገድ የሚቀናበሩ ሙዚቃዎችን ለማጀብም ጥቅም ላይ ይውላሉ።

በሀገራችን የሚገኙ የክር የሙዚቃ መሳሪያዎች ማህበረሰቡ ጀግንነቱን፣ ኃይማኖታዊ ሥርዓቱን፣ ዓለማዊ ፍላጎቱን እና መሰል ማህበራዊ ተግባራቱን በዜማ፣ በፉከራ እና በሽለላ እንዲሁም በቀረርቶ በሚገልፅበት ወቅት ስሜትን የሚቀሰቅሱ እና ደስታን ወይም ሀዘንን በጋለ ስሜት ማጣጣም እንዲችል የሚረዱት ሲሆን ማህበራዊ ደህንነትን ለማስጠበቅ የምንጠቀምባቸው መሳሪያዎች ናቸው።

የክር የሙዚቃ መሳሪያዎች በመጠን፣ በክር ብዛታቸው እና በቅርፃቸው የተለያዩ ሲሆኑ በአጨዋወት ብልሃታቸውም ይለያያሉ። ለምሳሌ ክራር በግርፍ ወይም ድርድር ብልሃት የምንጫወተው ሲሆን መሰንቆ ደግሞ በመገዝገዣ (ቦው) በሚባለው የመሰንቆ አካል የተወጠረውን የክር ጥቅል በመገዝገዝ የምንጫወተው መሳሪያ ነው። እነዚህ የክር የሙዚቃ መሳሪያዎች በሀገራችን በተለያዩ ክፍሎች የሚገኙ ሲሆን እንደ ክራር፣ በገና፣ መሰንቆ፣ ዲታ እና ዱል የመሳሰሉት የሚጠቀሱ ናቸው።



ክራር፦ ስድስት ወይም አምስት ክሮች ያሉት ባህላዊ የክር የሙዚቃ መሳሪያ ሲሆን በአይነቱ፣ በመጠኑ፣ በአጨዋወት ስልቱ እና በዜማ ውስጥ በሚኖረው ተግባር የተለያየ ነው። ለምሳሌ በደቡብ አካባቢ ዲታ፣ በጋምቤላ ዱል እና በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ደግሞ ክራር በመባል የሚታወቅ የሙዚቃ መሳሪያ ነው። ክራር ዓለማዊ እና መንፈሳዊ ዜማዎችን (ዝማሬዎችን) ለማጀብ የሚያገለግል ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ ነው።



መሰንቆ፦ በሀገራችን የሚገኝ ረጅም ታሪክ ያለው እና በሀገራችን የሙዚቃ እድገት ውስጥ ከፍተኛ ሚና የነበረው ሲሆን አሁንም ጥቅም ላይ እየዋለ ያለ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ ነው። መሰንቆ ከ80 እስከ 140 በሚደርሱ የፈረስ ጭራዎች አንድ ላይ ተደርገው በሚፈጥሩት ጥቅል (ክር) ላይ ሰባቱንም መሰረታዊ የሙዚቃ ድምፆች ማውጣት የሚችል ጥንታዊ የኢትዮጵያ የክር የሙዚቃ መሳሪያ ነው።

መሰንቆ በከፍተኛ ደረጃ ጥቅም ይሰጥ የነበረው ለመንፈሳዊ ዝማሬዎች ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ ግን በተለያዩ የባህላዊ እና ዘመናዊ ሙዚቃዎችን በማጀብ የዜማ ውበት መፍጠር የሚችል ሆኖ በኢትዮጵያ ሙዚቃ ውስጥ እያገለገለ ይገኛል።



በገና፦ በኢትዮጵያ ከሚገኙ እድሜ ጠገብ የዜማ መሳሪያዎች ውስጥ በታሪካዊነቱ እና በአገልግሎቱ ታዋቂ ነው። በገና አስር ክሮች (አውታር) ያለው ሲሆን በአስሩም ክሮች ወይም አውታሮች ላይ የሚቃኙት ድምፆች ግን አምስት ብቻ ሲሆኑ ሌሎች አምስቱ አውታሮች የጣት ማረፊያ ናቸው። ማረፊያ የሆኑት አምስቱ አውታሮች አጠገባቸው ካሉት የሚደረደሩት አውታሮች ጋር በተመሳሳይ ድምጽ ይቃኛሉ።

በገና ለሀይማኖታዊ (ለመንፈሳዊ ዜማዎች) አገልግሎት እየዋለ ያለ ሲሆን ከክር የሙዚቃ መሳሪያዎች ውስጥ በአካሉ ትልቁ እና ወፍራም ድምፅ ማውጣት የሚችል ነው።

ተግባር 1.7

1. አንድ የክር የሙዚቃ መሳሪያ በመምረጥ በአካባቢያችሁ በሚገኝ ቁሳቁስ ተጠቅማችሁ የመሳሪያውን የአሰራር ቅደምተከተል በመጠበቅ ሰርታችሁ አምጡ።
2. የግርፍና የድርድር የአጨዋወት ዘዴን ልዩነት አብራሩ።
3. የክራር እና የበገናን አንድነት እና ልዩነት አብራርታችሁ ጻፉ።
4. በክራር እና በመሰንቆ በምትፈልጉት ቅኝት አንድ ዜማ ተጫወታችሁ አሳዩ።
5. ከላይ የተዘረዘሩትን ባህላዊ የክር የሙዚቃ መሳሪያዎች የአካል ክፍሎች በመዘርዘር ስለእያንዳንዱ ጠቀሜታ ማብራሪያ ስጡ።
6. በሀገራችን ተጨማሪ የምታውቋቸውን ባህላዊ የክር የሙዚቃ መሳሪያዎች በመዘርዘር ስለአሰራራቸው እና ጠቀሜታቸው ማብራሪያ ስጡ።

1.2.2.2 ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች

ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች የሚባሉት ቴክኖሎጂያዊ አሰራርን በመከተል የተሰሩ፣ ልኬታቸው የሚታወቅና በአካባቢያችን በምናገኛቸው ቁሳቁሶች በቀላሉ

ልናዘጋጃቸዉ (ልንሰራቸዉ) የማንችላቸዉ ናቸዉ። ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን በአራት ዋና ዋና ምድቦች እንመድባቸዋለን። እነሱም፡-

- ☞ የክር ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች(string modern Instrument)
- ☞ የምት ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች(Percussion modern Instrument)
- ☞ የትንፋሽ ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች(Wind modern Instrument)
- ☞ የቁልፍ ዘመናዊ ሙዚቃ መሳሪያዎች(Keboard moderrn Instrument)

የክር ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች

የክር ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች የምንላቸዉ ለዘመናዊ ሙዚቃ ማጀቢያነት የምንጠቀማቸዉ እና በመገዝገዝ ወይም ክሮችን በመቦጨቅ ድምፅ ሊሰጡ የሚችሉ የሙዚቃ መሳሪያ ናቸዉ። ለምሳሌ የሚከተሉትን እንመልከት፡-



ቫዮሊን፡- የሙዚቃ ደራሲያን ረቂቅ ሙዚቃዎችን ለማጀብ የሚጠቀሙበት እና በመገዝገዝ ብልሃት መጫወት የሚያስችል ዘመናዊ የክር የሙዚቃ መሳሪያ ሲሆን ቀጭን የሴቶችን ድምጽ (ሶፕራኖ) ማዉጣት የሚችል ነዉ።

ቪዮላ፡- እንደ ቫዮሊን በመገዝገዝ የምንጫወተዉ ሆኖ ከቫዮሊን የሚለየዉ የአራቱ ክሮች የዉፍረትና ቅጥነት መጠን እና ስም መለያየት ነዉ። ቪዮላ የሴት ወፍራም ድምጽ (አልቶ) ማዉጣት የሚችል እና በመጠኑ ከቫዮሊን የሚበልጥ የሙዚቃ መሳሪያ ነዉ።



ጊታር፡- በዓለም ላይ የተለያዩ የጊታር አይነቶች ያሉ ሲሆን እነሱም ሊድ ጊታ፤ ቤዝ ጊታር እና ቦክስ ጊታር ናቸዉ። የአጨዋወት ብልሃታቸውም ክሮችን በመቦጨቅ ነው። ሊድ እና ቦክስ ጊታር 6 ክሮች ሲኖራቸዉ ቤዝ ጊታር 4 ክሮች አሉት።

		
ቤዝ ጊታር	ሊድ ጊታር	ቦክስ ጊታር

የትንፋሽ ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች

በትንፋሽ ሀይል ከንፈርን በማጥበቅ እና በማላላት ስንጫወታቸዉ ድምፅ ሊሰጡ የሚችሉ ናቸዉ። የትንፋሽ ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን በአሰራራቸዉ በሁለት እንመድባቸዋለን። እነሱም፡-

- ከነሀስ የሚሰሩ (ትራምፔት፣ትሮምቦን፣ቱባ፣ ኮርኔት)
- ከእንጨት የሚሰሩ (ፍሉት፣ሳክስፎን፣ ክላርኔት) ለምሳሌ የሚከተሉትን እንመልከት፡-



ትራምፔት፡- ነሀስ የሚሰራ ዘመናዊ የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያ ሲሆን ከወፍራም ድምፅ እስከ መጨረሻዉ ቀጭን ድምፅ ማዉጣት የሚችል ነዉ።



ክላርኔት፡- ከእንጨት የሚሰራ እና ባለ አንድ ሪድ(ድምፅ መፍጠሪያ) ያለዉ ዘመናዊ የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያ ነዉ። ክላርኔትን በሀገራችን በኢትዮጵያ በአብዛኛዉ በሚሊታሪ ባንድ ዉስጥ የምንጠቀምበት የሙዚቃ መሳሪያ ነዉ።

ሳክስፎን፡- ከእንጨት የሚሰራ ዘመናዊ የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያ ሲሆን አራት አይነት ሳክስፎን አሉ። እነዚህም ቴነር ሳክስፎን ፣ አልቶ ሳክስፎን፣ ባሪቶን ሳክስፎን እና ሶፕራኖ ሳክስፎን ናቸዉ።


	
አልቶ ሳክስፎን	ሶፕራኖ ሳክስፎን
	
ቴነር ሳክስፎን	ባሪቶን ሳክስፎን

የምት ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች

ዘመናዊ የምት ሙዚቃ መሳሪያዎች አንድን አካል ከሌላ አካል ጋር በማጋጨት ወይም በመምታት ድምፅ ሊሰጡ የሚችል ሆነዉ በአብዛኛዉ ለዘመናዊ ሙዚቃ ማጀቢያነት የምንጠቀማቸዉ ናቸዉ። ለምሳሌ የሚከተሉትን እንመልከት፡-



ዛይላፎን፡- የሚቃኝ ዘመናዊ የምት የሙዚቃ መሳሪያ ሲሆን የሚሰራዉም ከጠንካራ እንጨቶች ነዉ። ዛይላፎን ሰባቱን የሙዚቃ ድምፅ ማዉጣት የሚችል የሙዚቃ መሳሪያ ነዉ።



ሲምበል፡- የሚቃኝ የምት የሙዚቃ መሳሪያ ሲሆን የሚሰራዉም ከነሀስ ነዉ። በአብዛኛዉ በሚሊታሪ ባንድ እንጠቀምበታለን።

የቁልፍ የሙዚቃ መሳሪያዎች

የቁልፍ ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች የሚባሉት ቁልፎችን በጣት በምንነካካበት ወይም በምንጫወትበት ጊዜ ከተወጠሩ ክሮች እና ቁልፎች ጋር የተያያዙ መዶሻ መሰል ነገሮች ክሮችን ሲመቷቸዉ ድምፅ መፍጠር የሚችሉ ናቸዉ። ለምሳሌ የሚከተሉትን እንመልከት፡-



ፒያኖ፡- ከቁልፍ የሙዚቃ መሳሪያዎች ዉስጥ የሚመደብ እና በጣም ታዋቂ የዘመናዊ ሙዚቃ ማጀቢያ መሳሪያ ነዉ።



ኦርጋን፡- ከሌሎች የቁልፍ የሙዚቃ መሳሪያዎች ቀደምት ወይም ጥንታዊ የሆነ የሙዚቃ መሳሪያ ነዉ።

1.2.3 የኢትዮጵያ ቅኝቶች

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. ስለ ቅኝት ትርጉም እና ጠቀሜታ የምታውቁትን ለመምህራችሁ ተናገሩ።
2. የምታውቋቸውን የኢትዮጵያ ቅኝቶች ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።
3. ዜማን ለመፍጠር ቅኝት ያለውን ጠቀሜታ ተወያዩ እና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ።

አንድን ዜማ ዜማ ሆኖ ከመፈጠሩ በፊት ዜማን መፍጠር የሚያስችሉ ቃና የተባሉ የድምፅ መዋቅራዊ ስብስቦች ያስፈልጉታል። እነዚህ ድምፅ ወይም የቃናዎች አደራደር ህጎችን መሰረት አድርገው ሲደራጁ የተለያዩ ዜማዎችን መፍጠር የሚያስችሉ ቃናዊ ስብስቦች ቅኝትን ይመሰርታሉ።

በሀገራችን በተለያዩ ቃናዊ አወቃቀር የሚመሰረቱ በርካታ የቅኝት አይነቶች ቢኖሩም ዋና ዋናዎቹ ትዝታ፣ ባቲ፣ አንችሆየ እና አምባሰል ናቸዉ። በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች መማሪያ መጽሐፍት ላይ የተቀመጡ መዝሙሮች በእነዚሁ መሰረታዊ ቅኝቶች ተመስርተው እንደዘመራችሁ ማወቅ ይገባችኋል። በኢትዮጵያ ሙዚቃ ላይ ጥናት እና ምርምር የሚያካሂዱ የሙዚቃ ባለሙያዎች በርካታ ናቸው።

በቅኝቶች የድምፅ አወቃቀር ሁኔታ ላይ በኢትዮጵያ ሙዚቃ የተለያዩ ቅኝቶች እንዳሉ ተመራማሪ ዶ/ር እዝራ አባተ በሚከተለው አካባቢ ሁኔታ እንደሚታዩ በጥናቱ አረጋግጧል።

- የሰሜን እና የመካከለኛው ኢትዮጵያ (ትግራይ፣ አማራ እና ሸዋ)
- የምስራቁ (ሐረር፣ ድሬድዋ እና ሶማሌ)

➢የደቡብ እና የምዕራቡ (ደቡብ ኢትዮጵያ፣ ጋምቤላ እና ቤንሻንጉል)

ቅኝቶችን መመስረት የሚያስችሉ የድምፅ ርቀቶች (Intervals)

የድምፅ ርቀት (ኢንተርቫል) በሁለት ድምፆች መካከል የሚኖር የርግብግቦሽ መጠን ልዩነት ሲሆን የተለያዩ ቅኝቶችን መመስረቻ ህግ ሆኖ ያገለግላል። ቅኝቶችን ለመመስረት የሚያስችሉ አምስት የኢንተርቫል አይነቶች አሉ። እነሱም፦ ሜጀር፣ ፐርፌክት፣ ማይነር፣ አግመንትድ እና ዲሚኒሽድ ናቸው።

ለምሳሌ፦ ከC እስከ D ወይም በ220Hz እና 240Hz ያለውን የድምፅ ርቀት የርግብግቦሽ መጠን ልዩነት ለማወቅ 240Hz — 220Hz = 20Hz ሲሆን በሁለቱ ድምፆች መካከል ያለ ርቀት ተደርጎ ይወሰዳል። ስለዚህ የማንኛውም ቅኝት ሲመሰረት በነዚህ የድምፅ ርቀቶች የሚወሰን ሲሆን የመነሻ ድምፁን በመሰረታዊነት እንደመነሻ በመቁጠር እንደየ ቅኝቱ የድምፅ ብዛት መሰረት የድምፅ ርቀት ህግ ይኖረዋል። ከዚህ በታች የሚቀርቡት የኢትዮጵያ ቅኝቶች አመሰራረትን መመልከት ይቻላል።

1.2.3.1 ትዝታ ቅኝት


የትዝታ ቅኝት በሀገራችን የሚዜሙ በርካታ መዚቃዎችን መጫወት የሚያስችል እና በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በሚገኙ ማህበረሰቦች የሙዚቃ ባህል ውስጥ የሚታወቅ ነው። እንደ መዚቃው ስልተ ምት ፍጥነት እና ቀስታ (ቴምፖ) አማካኝነት የተለያዩ አእምሯዊ እና አካላዊ እንቅስቃሴዎችን መፍጠር የሚያስችሉ ዜማዎች እንዲገነቡ ያደርጋል።

ትዝታ ቅኝት ያለፈ ታሪክን፣ ፍቅርን፣ መተሳሰብን፣ ተስፋን እና መሰል ሃሳቦችን መግለፅ የሚችሉ ዘፈኖችን ማደራጀት እና ማቀናበር የሚያስችለን በአምስት ድምፆች የሚመሰረት ቅኝት ነው። ትዝታ ቅኝት ዓብይ (Major) ትዝታ እና ንዑስ (minor) ትዝታ ቅኝት ተብለው በሁለት ይከፈላሉ።

ዓብይ ትዝታ ቅኝት/Tezeta Major/

የዓብይ ትዝታ ቅኝት ከባለሰባቱ የሙዚቃ ድምፆች ላይ አራተኛውን እና ሰባተኛውን የድምፅ ደረጃዎችን በማስወጣት ይመሰረታል።


በተፈጥሮ ሲ መነሻ ድምፅ የዓብይ ትዝታ ቅኝት አመሰራረት እንመልከት፡-



ዓብይ ትዝታ ቅኝት የድምፅ ርቀቶች (intervals)

- C ----C ፐርፌክት አንደኛ
- C ----D ዓብይ ሁለተኛ
- C---- E ዓብይ ሦስተኛ
- C ----- G ፐርፌክት አምስተኛ
- C --- A ዓብይ ስድስተኛ
- C --- ኦክታቭ C ፐርፌክት ስምንተኛ (ፐርፌክት ኦክታቭ)

ምሳሌ፦ C ዓብይ ትዝታ ቅኝት




ተግባር 1.8

1. E ድምጽን መነሻ በማድረግ በኤፍ ቁልፍ በሙሉ ኖታ የዓብይ ትዝታ ድምጾችን በመደርደር በተግባር በድምፅ ዘምራችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሰሙ።
2. በዓብይ ትዝታ ቅኝት የተዜሙ ዜማዎችን ዘርዝሩ።
3. የድምፅ ርቀት ምንነትን በምሳሌ በማስደገፍ ማብራሪያ ስጡ።
4. በተለያዩ መነሻ ድምፆች የዓብይ ትዝታ ቅኝትን የድምጽ ርቀቶች ሰርታችሁ አሳዩ።
5. በዓብይ ትዝታ ቅኝት በመሰንቆ አንድ ዜማ በተግባር ተጫውታችሁ አሳዩ።

ንዑስ ትዝታ ቅኝት/Tezeta minor/


የንዑስ ትዝታ ቅኝት ከባለሰባቱ የሙዚቃ ድምፆች ላይ አራተኛውን እና ሰባተኛውን የድምፅ ደረጃዎችን በማስወጣት እንዲሁም ሦስተኛውን እና ስድስተኛውን የሙዚቃ ድምፅ በግማሽ ድምፅ ዝቅ በማድረግ ይመሰረታል። ምሳሌ በC መነሻ ድምጽ እንመልከት፡-



የንዑስ ትዝታ ቅኝት የድምፅ ርቀቶች (intervals)

- C ----C ፐርፌክት አንደኛ
- C ----D ዓብይ ሁለተኛ
- C---- Eb ንዑስ ሦስተኛ
- C ----- G ፐርፌክት አምስተኛ
- C --- Ab ንዑስ ስድስተኛ
- C --- ኦክታቭ C ፐርፌክት ስምንተኛ(ፐርፌክት ኦክታቭ)

ምሳሌ፦ C ንዑስ ትዝታ ቅኝት



ተግባር 1.9

1. G እና F ድምፆችን መነሻ አድርጋችሁ በጅ ቁልፍ ላይ የንዑስ ትዝታ ቅኝት ድምፆችን በግማሽ ኖታ በመደርደር የድምጽ ርቀቶችን ሰርታችሁ አሳዩ።
2. በዓብይ ትዝታ እና በንዑስ ትዝታ ቅኝት መካከል ምን መሰረታዊ ልዩነት እንዳለ ማብራሪያ ስጡ።


1.2.3.2 ባቲ ቅኝት

ባቲ ቅኝት በሀገራችን ታዋቂ እና በሙዚቃ ስራ ውስጥ የተለያዩ ዜማዎችን መመስረት የሚያስችል የድምፅ መዋቅር ነው። እንደ ሙዚቃው ስልተ ምት ፍጥነት እና ቀስታ (ቴምፖ) አማካኝነት የተለያዩ ስሜቶችን እና አካላዊ እንቅስቃሴዎችን መፍጠር የሚያስችሉ ዜማዎች እንዲገነቡ ያደርጋል። ባቲ ቅኝት ጀግንነትን፣ ያለፈ ታሪክን፣ ፍቅርን፣ መተሳሰብን፣ ተስፋ እና መሰል ሃሳቦችን መግለፅ የሚችሉ ዘፈኖችን ማደራጀት እና ማቀናበር የሚያስችል በአምስት ድምፆች የሚዋቀር ቅኝት ነው።

ባቲ ቅኝት ዓብይ (Major) ባቲ እና ንዑስ (minor) ባቲ ቅኝት ተብሎ በሁለት ይከፈላል።

ዓብይ ባቲ ቅኝት/Bati Major/


የዓብይ ባቲ ቅኝት ከባለሰባቱ የሙዚቃ ድምጾች ላይ ሁለተኛውን እና ስድስተኛውን የድምፅ ደረጃዎችን በማስወጣት ይመሰረታል። ለምሳሌ C መነሻ ድምጽ በማድረግ እንመልከት፡-



የዓብይ ባቲ ቅኝት የድምፅ ርቀቶች (intervals)


- C ----C ፐርፌክት አንደኛ
- C ----E ዓብይ ሦስተኛ
- C---- F ፐርፌክት አራተኛ
- C ----- G ፐርፌክት አምስተኛ
- C --- B ዓብይ ሰባተኛ
- C --- C ፐርፌክት ስምንተኛ

C ባቲ ዓብይ ቅኝት በጅ ቁልፍ ሲቀመጥ



ንዑስ ባቲ ቅኝት/Bati Minor/

የንዑስ ባቲ ቅኝት ከባለሰባቱ የሙዚቃ ድምፆች ላይ ሁለተኛውን እና ስድስተኛውን የድምፅ ደረጃዎችን በማስወጣት እንዲሁም ሦስተኛውን እና ሰባተኛውን የሙዚቃ ድምፅ በግማሽ ዝቅ በማድረግ ይመሰረታል። ለምሳሌ C መነሻ ድምጽን መነሻ በማድረግ እንመልከት፡-




የንዑስ ባቲ ቅኝት የድምፅ ርቀቶች (intervals)

- C ----C ፐርፌክት አንደኛ
- C ---Eb ንዑስ ሦስተኛ
- C---- F ፐርፌክት አራተኛ

- C ----- G ፐርፌክት አምስተኛ
- C --- B b ንዑስ ሰባተኛ
- C --- አክታቭ C ፐርፌክት ስምንተኛ

ምሳሌ፦ C ባቲ ንዑስ ቅኝት በጅ ቁልፍ ሲቀመጥ




ተግባር 1.10

1. D ድምፅን መነሻ በማድረግ በኤፍ ቁልፍ ዓብይ ባቲ ቅኝትን በግማሽ ኖታ በመደርደር የድምጽ ርቀቶችን ሰርታችሁ አሳዩ።
2. B ፍላት ድምፅን መነሻ በማድረግ በጅ ቁልፍ ንዑስ ባቲ ቅኝትን በሙሉ ኖታ ደርድራችሁ አሳዩ።
3. የዓብይ ባቲ እና ንዑስ ባቲ ቅኝት መሰረታዊ ልዩነታቸውን ምሳሌ በመስጠት አብራሩ።
4. ከምታውቋቸው ዜማዎች መካከል በባቲ ቅኝት የሚዜሙትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ዘርዝሩላቸው።
5. በዓብይ ባቲ ቅኝት በክራር አንድ ዜማ በተግባር ተጫውታችሁ አሳዩ።

1.2.3.3 አንችሆየ ቅኝት

አንችሆየ ቅኝት በሀገራችን ውስጥ ከሚገኙ ቅኝቶች ውስጥ አንዱ ሲሆን ከሰባቱ የድምፅ ደረጃዎች መካከል ከመነሻው ሦስተኛውን እና ሰባተኛውን የድምፅ ደረጃዎች በማውጣት እና ሁለተኛውን እና አምስተኛውን የድምጽ ደረጃዎች በግማሽ ድምፅ ዝቅ በማድረግ የሚመሰረት ቅኝት ነው።

የአንችሆየ ቅኝት አመሰራረት ስርዓት ድምፆች ከባለሰባቱ ዓብይ ቅኝት(Major scale) ላይ በመነሳት በሚከተለው መንገድ መመስረት ይቻላል። ምሳሌ፦ C መነሻ ድምጽን መነሻ በማድረግ፡-




የአንችሆየ ቅኝት የድምፅ ርቀቶች

- C ----C ፐርፌክት አንደኛ
- C ----Db ንዑስ ሁለተኛ
- C---- F ፐርፌክት አራተኛ
- C ----- Gb ዲሚኒሽድ አምስተኛ
- C ---A ዓብይ ስድስተኛ
- C --- ኦክታቭ C ፐርፌክት ስምንተኛ (ፐርፌክት ኦክታቭ)

በጅ ቁልፍ ላይ የአንችሆየ ቅኝት አቀማመጥ

ምሳሌ፦ C አንችሆየ ቅኝት



በሙዚቃ መፃፊያ ሰሌዳው ላይ እንደተመላከተዉ የአንችሆየ ቅኝት ከባለሰባቱ ዓብይ ቅኝት ላይ ሦስተኛውን እና ሰባተኛውን የድምፅ ደረጃዎች በመተው እንዲሁም ሁለተኛውን እና አምስተኛውን የድምፅ ደረጃዎች በግማሽ የድምፅ ደረጃ ዝቅ በማድረግ በአምስት ድምፆች ብቻ የሚመሰረት የኢትዮጵያ ቅኝት ነው።


ተግባር 1.11

1. G ድምፅን መነሻ በማድረግ በጅ ቁልፍ በግማሽ ኖታ የአንችሆየ ቅኝትን ድምጾች ደርድራችሁ አሳዩ።
2. B ፍላት ድምፅን መነሻ በማድረግ በኤፍ ቁልፍ በሙሉ ኖታ የአንችሆየ ቅኝት ድምጾች ደርድሩ።
3. በአካባቢያችሁ ከምታዳምጧቸው ዜማዎች መካከል በአንችሆየ ቅኝት የሚዜሙ የምትሏቸውን ዜማዎች ዘርዝሩ።
4. በአንችሆየ ቅኝት በበገና አንድ ዜማ በተግባር ተጫዉታችሁ አሳዩ።

1.2.3.4 አምባሰል ቅኝት

ቅኝቶች የሚመሰረቱት በተለያየ የርግብግቦሽ መጠን ባላቸው ቃናዎች መሆኑን በአንችሆየ የቅኝት አመሰራረት ስትማሩ አውቃችኋል። በአምባሰል የቅኝት አመሰራረት ሂደትም ተመሳሳይ የአደራደር ስርዓት አላቸው።

የአምባሰል ቅኝት አመሰራረት ስርዓት ከሰባቱ የድምፅ ደረጃዎች በመነሳት ሦስተኛውን እና ሰባተኛውን የሙዚቃ ድምፆች በማስወጣት እንዲሁም ሁለተኛውን እና ስድስተኛውን ድምፅ በግማሽ ድምፅ ዝቅ በማድረግ የሚመሰረት የሀገራችን ቅኝት ነው። የድምፅ ርቀቶችን ከባለሰባቱ ዓብይ (ሜጀር ስኬል) ቅኝት ላይ በመነሳት በሚከተለው መንገድ መመስረት ይቻላል። ምሳሌ፦ C መነሻ ድምጽን መነሻ በማድረግ-




የአምባሰል ቅኝት የድምፅ ርቀቶች (intervals)

- C ----C ፕርፌክት አንደኛ
- C ----Db ንዑስ ሁለተኛ
- C---- F ፕርፌክት አራተኛ

- C -----G ፐርፌክት አምስተኛ
- C --- Ab ንዑስ ስድስተኛ
- C --- ኦክታቭ C ፐርፌክት ስምንተኛ(ፐርፌክት ኦክታቭ)

በጅ ቁልፍ ላይ የአምባሰል ቅኝት አመሰራረት

ምሳሌ፦ C አምባሰል ቅኝት



ተግባር 1.12

1. D ድምፅን መነሻ በማድረግ አምባሰል ቅኝትን በጅ ቁልፍ በሙሉ ኖታ ገንብታችሁ አሳዩ።
2. በአምባሰል ቅኝት የሚዜሙ ዜማዎችን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ዘርዝሩ።
3. በምትፈልጉት የሙዚቃ ድምፅ በመነሳት የአምባሰል ቅኝት የኢንተርቫል ርቀት ህጎች ትክክል መሆናቸውን አረጋግጡ።

1.2.4. የኢትዮጵያ ባህላዊ ውዝዋዜ ምድቦች (Folk Dance)

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. ባህላዊ ውዝዋዜ በምን ሁነቶች ላይ ይተገበራል?
2. በተለያዩ አካባቢዎች የሚተገበሩ ውዝዋዜዎችን ልዩነት ተናገሩ።
3. በአካባቢያችሁ የሚከወኑ ውዝዋዜዎች ጥቅምን አስረዱ።
4. በሀገራችን ከሚታወቁ ባህላዊ ውዝዋዜዎች መካከል የምታውቋቸውን የባህላዊ ውዝዋዜ ስያሜዎች ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

ዓመታት እያለፉ ሲሄዱ የሰው ልጅ ባህሎች እና እምነቶች ቀስ በቀስ ወደ ወግነት ይለወጣሉ። ባህላዊ ውዝዋዜዎች(ጭፈራዎች) የሀገሮችን እና የአካባቢዎችን ወጎች

ለሕዝብ ማሳየት ከሚቻልባቸው ጠንካራ መንገዶች ዉስጥ ዋነኞቹ ናቸዉ። ምንም እንኳ ብዙዎቹ ባህላዊ ጭፈራዎች የጎሳ ውዝዋዜ ስም ቢኖራቸውም ሁሉም ባህላዊ ውዝዋዜ ሆነው አይቀጥሉም። ይሁን እንጂ ሁሉም የጭፈራውን ባህላዊ አመጣጥ ይጠቁማሉ።

አብዛኛውን ጊዜ ባህላዊ ጭፈራዎች የሚጨፈሩት በማኅበራዊ ግብዣዎች ላይ (በድንገተኛ ወይም በየዓመቱ በሚከበሩ ክብረ በዓላት ላይ) ነው። እነዚህ ጭፈራዎች አንድ ዓይነት የውዝዋዜ መድረክ ቢኖራቸውም እንኳ ምቹ ሁኔታን አይጠይቁም። በመሆኑም አዳዲስ ተወዛዋዦችን እና አጫዋቾችን ከሌላ ሰው ጋር ማሳተፍ አይችልም። እንዲህ ዓይነቶቹ ጭፈራዎች የባህላዊ ጭፈራዎችን እድገት የሚቆጣጠር የአስተዳደር አካል የላቸውም ለማለት ያስደፍራል። ከዚህ ይልቅ በሀገራችን እና በአካባቢያችን የሚጨፈሩት ባህላዊ ጭፈራዎች በአካባቢው ባህል ላይ በሚከናወነው ለውጥ ሳቢያ በድንገት ይጨፈራሉ። እንዲሁም ብዙውን ጊዜ "የጎዳና ውዝዋዜ" ተብለው ይጠራሉ።

በሀገራችን ከሚታወቁ ባህላዊ ውዝዋዜዎች መካከል የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል። በተንቤን አካባቢ አውርስ፣ በጎጃም አካባቢ ዝናብ እንቅጥቅጥ፣ በራያ ቆቦ አካባቢ እረገጣ፣ በኦሮሚያ አካባቢ ፎሌ እና በአካባቢያቸው ስም የሚጠሩ እንደ የጉራጌ ጭፈራ፣ የትግራይ ጭፈራ፣ የምንጃር ጭፈራ ወዘተ የሚሉት ይገኙበታል። ከላይ ከተዘረዘሩት ባህላዊ ዉዝዋዜዎች (ጭፈራዎች) በተጨማሪ በሀገራችን በተለያዩ አካባቢዎች በርካታ የባህላዊ ውዝዋዜ አይነቶች ይገኛሉ። እነዚህ የውዝዋዜ አይነቶች የአካባቢውን ወግ፣ ልማድ፣ የማህበረሰቡን መንፈሳዊ እና ቁሳዊ ባህሎችን እንዲሁም የተለያዩ ማህበራዊ አውዶችን መሰረት አድርገው ይተገበራሉ።

ባህላዊ ውዝዋዜዎች በአጨዋወት ብልሀታቸው ተመሳሳይ እና ተወራራሽ ቢሆኑም በሚኖራቸው አውዳዊ ልዩነት እና ውዝዋዜዎቹ ከሚፈጥሩት የመነሳሳት እና ደስታን ከመፍጠር አንፃር መለየት እና መመደብ ይቻላል። ምሳሌ

- በክብረ-በዓላት ላይ የሚከወኑ ውዝዋዜዎች
- ጀግንነትን በሚገልፁ የፉከራ፣ ሽለላ እና ቀረርቶ ላይ የሚደረጉ ውዝዋዜዎች
- በሰርግ እና መሰል ማህበራዊ ክዋኔዎች የሚዘወተሩ ውዝዋዜዎች
- በስራ ወቅት የሚከወኑ ውዝዋዜዎች ወዘተ

በተጨማሪም ውዝዋዜዎች ከሚከውኑት ሰዎች ከእድሜ ልዩነት፣ ከፆታ እና ከማህበራዊ ደረጃ አንፃር ሊመደቡ ይችላሉ። ምሳሌ፦

- በፆታ ልዩነት የተመሰረቱ በቡድን የሚከወኑ
- በጥንድ የሚከወኑ
- በህብረት የሚከወኑ





ሥዕል 20 በሴቶች የሚከወን ባህላዊ ውዝዋዜ ሥዕል 21 በቡድን የሚከወን ባህላዊ ውዝዋዜ



ሥዕል 22 በጥንድ የሚደረግ ባህላዊ ውዝዋዜ

ስዕሎች እንደሚያመላክቱት የኢትዮጵያ ባህላዊ ውዝዋዜ ክዋኔዎች ከግል ችሎታ ይልቅ ማህበራዊ ጥበብን (ማህበራዊ ልማድ) የሚጠይቁ እና ዘፋኝ፣ ተወዣዋዥ፣ የሙዚቃ መሳሪያ ተጫዋች፣ ተመልካች እና በውስጡ የሚገለፀው የቋንቋ ውበትን፣ ቁሳዊ ሀብትን፣ ቃል አልባ ተግባቦትን እና መሰል ማህበራዊ ዳራዎችን የሚያካትቱ ናቸው።

ተግባር 1.13

1. በጥንድ እና በህብረት በሚደረግ ባህላዊ ውዝዋዜ መካከል ያለውን አንድነት እና ልዩነት ማብራሪያ ስጡ።
2. በአካባቢችሁ አብዛኛውን ጊዜ በተለያዩ ሁነቶች የምትተገብሩትን የባህላዊ ውዝዋዜ ምድብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።
3. በጥንድ እና በህብረት በመሆን አንድ በአካባቢያችሁ የሚዜም ዜማ በመምረጥ ባህላዊ ውዝዋዜውን በተግባር ሰርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።
4. ባህላዊ ውዝዋዜዎች ሊመደቡ የሚችሉበትን ምክንያቶች ተናገሩ።

1.3 የፊልም እና የቴያትር መሰረታዊ የአዘገጃጀት ደረጃዎች

1.3.1 የፊልም መሰረታዊ የአዘገጃጀት ደረጃዎች

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. በአካባቢያችሁ ፊልም አይታችሁ ታውቃላችሁ? ያያችሁትን ፊልም ርዕስ ለመምህራችሁ ተናገሩ።
2. ፊልም ለአንድ አካባቢ ማህበረሰብ ምን ጠቀሜታ ይኖረዋል? ተወያዩ እና መልሳችሁን ለክፍል መምህራችሁ ተናገሩ።
3. ፊልም ለማዘጋጀት ምን ምን ነገሮች ያስፈልጋሉ?

የፊልም ጥበብ ከ9ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኋላ የፎቶ ግራፍ፣ የድምጽ እና የዕይታዊ ፈጠራዎች ማደግና መዘመንን ተከትሎ የድራማ እና የቴያትርን ቦታ፣ የጊዜ እና የተደራሽነት ውስንነቶችን በመሻገር የምስል እና ድምጽ ቴክኖሎጅን በመጠቀም መሰራት የጀመረ ጥበብ መሆኑን በ6ኛ እና 7ኛ ክፍል ተምራችኋል።

በዚህ የክፍል ደረጃ ደግሞ ፊልምን ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉ መሰረታዊ የአዘገጃጀት ደረጃዎችን ትማራላችሁ።

የፊልም መሰረታዊ የአዘገጃጀት ደረጃዎች

- ጽሁፍ መጻፍ፦ የፊልሙን ሀሳብ ደራሲው የሚያስቀምጥበት ክፍል ነው።
- ቅድመ ዝግጅት፦ ይህ ክፍል ደራሲው በጀት የሚያቅድበት እና የመስሪያ የጊዜ ሰሌዳ የሚያወጣበትን ያጠቃልላል። እንዲሁም ተዋናይ የሚመረጥበት ክፍል ነው።
- የትግበራ ወቅት፦ በታቀደው እቅድ መሰረት ወደ ስራ የሚገባበትን ክፍል ይይዛል።
- ፎቶግራፍ፦ በዚህ ክፍል የፎቶ ግራፍ አነሳስ ሀሳችን ያጠቃልላል።
- ድምጽን መቅዳት፦ ሁሉም ነገሮች ከተስተካከሉ በኋላ የተዋናይን ድምጽ የምንቀዳበት ነው።
- ድህረ ዝግጅት፦ በዚህ ክፍል ውስጥ የተሰራውን ፊልም የምንገመግምበት ክፍል ነው።
- ማሰራጨት (ማሳየት)፦ በዚህ ክፍል ፊልሙን ከገመገምን በኋላ ትክክለኛ ከሆነ በተለያዩ ሚዲያዎች የምናሳይበት ክፍል ነው።

1.3.2 የቴያትር መሰረታዊ የአዘገጃጀት ደረጃዎች

ቴያትር ደረጃውን ጠብቆ ለማዘጋጀት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የቴያትር መሰረታዊ ጉዳዮች መገንዘብ ያስፈልጋል።

- ተመልካች
- የተዋናዮች የትወና አቅም ወይም ችሎታ
- የመራሔ-ተውኔቱ ቴያትሩን መምራት እና ማደራጀት
- የቴያትሩ ዓላማ እና የሚፈጥሩት ሰዎች የሚቀበሉት አመለካከት
- የደራሲው አስገራሚ መዋቅር እና ገጸ-ባህሪያትን በመፍጠር ላይ ያከናወናቸው ስራዎች
- በሰፊ ወይም ጠባብ አካባቢ በአልባሳት፣ በመብራት እና በመልክዓ ምድሮች ከሚፈጠሩት የዕይታ ውጤቶች እንዲሁም የድምፅ አከዋወን

በ6ኛ እና በ7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፋችሁ ስለ ቴያትር ትርጉም እና የቴያትር አላባዉያን ተምራችኋል። በዚህ የክፍል ደረጃ ደግሞ ቴያትርን ለማዘጋጀት

የሚያስፈልጉ ቁልፍ ደረጃዎች እንመልከት፡-

- **የቴያትሩን ጽሁፍ መፃፍ፦** በዚህ ውስጥ ደራሲው የቴያትሩን አጠቃላይ ሀሳብ የሚያሰፍርበት ክፍል ነው።
- **አቅጣጫን ማስቀመጥ፦** ከዝግጅት እስከ ስዕላዊ መግለጫ፣ አልባሳት፣ ጌጣጌጦች፣ መዋቢያዎች፣ ሙዚቃዎች፣ ድምፆች እና መብራቶች ወዘተ ያሉ ውክልናዎችን የምናካትትበት እና በጀትን የምናስቀምጥበት ክፍል ነው።
- **ተዋናይን መምረጥ፦** በዚህ ክፍል ውስጥ ገፀ ባህሪያትን ተላብሰው የሚጫወቱ ተዋናዮችን መምረጥ፣ የመድረክ አዘጋጆችን መምረጥ እና የመብራት ሁኔታን የሚያመቻቹ ሰዎችን የምንመርጥበት ክፍል ነው።
- **መለማመጃ ክፍሎች፦** በዚህ ክፍል ውስጥ ለቴያትሩ የሚያስፈልጉ አልባሳትን የምንመርጥበት፣ ጽሁፉን በንባብ የምንለማመድበት፣ ንግግሩን የምንላበስበት እና ድርጊቱን /እንቅስቃሴውን/ እንድንለማመድበት የሚደረግበት ክፍል ነው።
- **የማስተዋወቅ ስራ፦** በዚህ ክፍል የተሰራውን የቴያትር ስራ በተለያዩ መገናኛ ሚዲያዎች ማለትም በቴሌቪዥን፣ በበራሪ ወረቀቶች ወዘተ ስራውን ለተደራሲው የምናደርስበት ክፍል ነው።

ተግባር 1.14

1. የፊልም መሰረታዊ የአዘገጃጀት ደረጃዎች ከቴያትር መሰረታዊ የአዘገጃጀት ደረጃዎች በምን በምን ይለያሉ?
2. የቴያትር መሰረታዊ የአዘገጃጀት ደረጃዎችን ማወቅ ምን ጠቀሜታ አለው?
3. በፊልም እና በቴያትር መካከል ያለውን ልዩነት እና ተመሳሳይነት ማብራሪያ ስጡ።

የምዕራፉ ማጠቃለያ

የዕይታዊ ጥበባት አናስሮች እና የዲዛይን መርሆች መሰረታዊ የሥዕል ቋንቋ ተደርገው የሚወሰዱ ናቸው። ሥዕልን ለመረዳት፣ ለማድነቅ፣ ለመገምገም፣ እና ለመተርጎም እነዚህን ቋንቋዎች ማወቅ የግድ አስፈላጊ ነው። የዕይታዊ ጥበባት አናስሮች የምንላቸው ቀለም፣ መስመር፣ ቴክስቸር፣ ዝርግ፣ ቅርፅ፣ ቦታ እና ፎርም ሲሆኑ የዲዛይን መርሆች የምንላቸዉ እንቅስቃሴ፣ ምት፣ ድግግሞሽ፣ ንፅፅር፣ ዉህደት፣ አፅንኦት እና አንድነት ናቸው።

በዲዛይን ስራ ውስጥ አናስሮችን በምን መንገድ መጠቀም እንዳለብን እና ዲዛይኑን በምንሰራበት ወቅት የዲዛይን አናስሮችን ሳይዘበራረቁ ቅደም ተከተላቸውን ለመጠበቅ እና በቦታቸው ለማስቀመጥ የሚመሩን የዲዛይን መርሆች ይባላሉ።

የኢትዮጵያ ሙዚቃ የራሱ የሆነ የዜማ ማሳመሪያ ዘዴ (ቅላፄ) ያለው ፣ ከማህበረሰቡ ባህል ጋር የተዋሃደ ነዉ።

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሙዚቃ በኢትዮጵያዊ ቅኝቶች ላይ የሚመሰረት የማህበረሰቡን ፍልስፍና፣ ባህል፣ ትምህርት፣ ፖለቲካ፣ ኃይማኖት ወዘተ በዜማ እና ግጥም ቅንብር እና በባህላዊ ውዝዋዜዎች የሚገለፅ ነው።

ባህላዊ ሙዚቃዎች መሰረታቸው በማህበረሰቡ እምነቶች፣ ልማዶች፣ ኃይማኖታዊ ሥርዓቶች፣ የስራ ባህል እና በአጠቃላይ በማህበረሰቡ የእለት ከዕለት ተግባሩ የተመሰረቱ ናቸው። የሙዚቃ ተመራማሪ የሆነው ዘነበ በቀለ የሀገራችንን ሙዚቃ ከማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኃይማኖታዊ አውዳቸው አንፃር በአራት መድቧቸዋል።

የባህል ሙዚቃ መሳሪያዎች በባህላዊ መንገድ፣ አካባቢያዊ ቁሳቁሶችን በመጠቀም የሚዘጋጁ እና ባህላዊ ዘፈኖችን ለማድመቅ የሚያገለግሉ ናቸው። የሙዚቃ መሳሪያዎች ከማህበረሰብ ማህበረሰብ በተለያየ ቅርፅ እና መጠን የሚዘጋጁ በመሆናቸው የተለያዩ የድምፅ ባህሪያትን ማውጣት የሚችሉ ሲሆኑ የማህበረሰቡ እውቀት እና ክሂሎት አሻራ ያረፈባቸው ቁሳዊ ቅርስ ናቸው።

ባህላዊ ውዝዋዜ በአካል እንቅስቃሴ የሚገለጽ የሙዚቃ ዋነኛ መገለጫ ሲሆን እንደየ አካባቢው ባህል የማህበረሰቡ የውዝዋዜ ስልቶች የተለያዩ እና በጋራ፣ በተናጠል እና በጥንድ በመሆን ሊከናወኑ የሚችሉ ናቸው።

ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ባህላዊ ዜማዎችን ለማጀብ፣ ለሙዚቃው ድምቀት እንዲኖረው በማድረግ እና ማህበራዊ ደህንነት በማጎልበት፣ አካላዊ ደህንነትን በመጠበቅ፣ ቃል አልባ መግባቢያ በመሆን እና ሥነ-ልቦናዊ ደህንነትን በማጠንከር ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ሲሆን የክር፣ የምት እና የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያዎች ተብለው ይመደባሉ።

ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ቴክኖሎጅያዊ አሰራርን በመከተል የተሰሩ፣ ልኬታቸዉ የሚታወቅ እና በቀላሉ ከአካባቢያችን በምናገኛቸዉ ቁሳቁሶች ልናዘጋጃቸዉ የማንችላቸዉ ሲሆኑ እነዚህም የክር፣ የምት፣የትንፋሽ እና የቁልፍ ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ተብለዉ በአራት ይመደባሉ።

ባህላዊ ውዝዋዜዎች የአካባቢን ማህበራዊ፣ ኃይማኖታዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን የሚገልፁ በመሆናቸው ማህበረሰቡ የራሱን ባህል እንዲወድ፣ እንዲያደንቅ፣ እንዲያከብረው፣ ከሌሎች አካባቢዎች ጋር የባህል ልውውጥ እንዲያደርግ እና መልካም ግንኙነቱን እንዲያጎለብት የሚረዱ ናቸው።

ቴያትር እና ፊልም የጥበብ ዘርፎች ሲሆኑ ሕይወትን ያንጸባርቃሉ። ከሰው ልጆች አጠቃላይ እንቅስቃሴ ውስጥ በከፊል መርጦ ጥበባዊ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ተመራጭ የቴያትር እና ፊልም ቁልፍ መርህ ነው። በመሆኑም የቴያትር ርዕሰ ጉዳይ ምንጊዜም የሰው ልጆች ናቸው።

ፊልምን ለማዘጋጀት አዘጋጆች ሊያደርጉት የሚገባው መሰረታዊ ሂደቶች የሚባሉት ፅሁፎችን ማዘጋጀት፣ የትግበራ ቅድመ ዝግጅት፣ ፎቶግራፍ የማንሳት፣ የድምፅ መቅዳት ሂደት፣ የድህረ ዝግጅት እና የተሰራውን የፊልም ስራ ለተመልካች የማሳየት እና የማቅረብ ሂደት ነው።

በተመሳሳይ ቴያትር ለተመልካች ከመቅረቡ በፊት ቴያትሩን መስራት የሚያስችሉ ቅድመ ሁኔታዎች አሉ። እነሱም የቴያትሩን ፅሁፍ መፃፍ፣ አቅጣጫን ማስቀመጥ፣ ተዋኞችን መምረጥ፣ የመለማመጃ ስፍራዎችን ማዘጋጀት እና ቴያትሩ ከተዘጋጀ በኋላ የማስተዋወቅ ስራ መስራት ናቸው።

የምዕራፉ ቼክሊስቶች

ተማሪዎች በዚህ ምዕራፍ የተማራችኋቸውን ዋና ዋና ነጥቦች ማወቃችሁን አረጋግጡ

ተ.ቁ	ይዘት	አሳክቻለሁ	አላሳካሁም
1	የኢትዮጵያ ሙዚቃ መሰረታዊ ምድቦችን አውቂያለሁ።		
2	ባህላዊ በሆነ መንገድ የሚፈጠሩ በማህበረሰቡ የሚከወኑ ሙዚቃዎች መኖራቸውን ተረድቻለሁ።		
3	የኢትዮጵያ ሙዚቃ በተለያዩ ምክንያቶች መንፈሳዊ እና ዓለማዊ፣ ዘመናዊ እና ባህላዊ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኃይማኖታዊ እና ማህበራዊ ተብለው ሊከፈሉ እንደሚችሉ ተገንዝቢያለሁ።		
4	የባህላዊ እና ዘመናዊ ሙዚቃ አቀራረብ ባህሪያትን ለይቼ አውቂያሉ።		
5	የሙዚቃ መሳሪያዎችን ዋና ዋና ምድቦችን ለይቼ አውቂያለሁ።		
6	በኢትዮጵያ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች በአካባቢያዊ ቁሳቁሶች የሚዘጋጁ እና የማህበረሱ ቁሳዊ ባህል መሆናቸውን ተረድቻለሁ።		
7	የኢትዮጵያ ዋናዋና ቅኝቶች መሰረታዊ የአመሰራረት ፅንሰ ሃሳቦችን አውቂያለሁ።		
8	የድምፅ ርቀት ምንነትን እና በቅኝት አመሰራረት ያለውን ፋይዳ ተረድቻለው።		
9	ባህላዊ ውዝዋዜዎች የሚከወኑበትን አውዶች ለይቻለሁ።		
10	የፊልም እና ቴያትር መሰረታዊ የአዘገጃጀት ሂደቶችን አውቂያለሁ።		
11	የዕይታዊ ጥበባት አናስሮች እና የዲዛይን መርሆችን በመጠቀም ሥዕሎችን ማደራጀት ችያለሁ።		
12	የዕይታዊ ጥበባት አናስሮችን ለይቸ አዉቂያለሁ።		
13	የዕይታዊ ጥበባት አናስሮች እና መርሆችን በመጠቀም ሥነ-ጥበባዊ ስራ መስራት ችያለሁ።		

የማጠቃለያ መልመጃዎች

ትዕዛዝ አንድ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ።

1. ከሚከተሉት ውስጥ የዲዛይን መርህ የሆነው የትኛው ነው?

   ሀ) ቀለም ለ) ሚዛን ሐ) መስመር መ) ቅርፅ

2. ከሚከተሉት ውስጥ ከባህላዊ የክር የሙዚቃ መሳሪያዎች የሚካተት የቱ ነው?

   ሀ) ጊታር ለ) አታሞ ሐ) ፀናፅል መ) ክራር

3. ከሚከተሉት ዉስጥ ድምፀ-ውስን ባህላዊ የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያ የሆነዉ የቱ ነው?

   ሀ) ዋሽንት ለ) ፋንፋ ሐ) መለከት መ) ትራምፔት

4. ከሚከተሉት ባህላዊ የክር የሙዚቃ መሳሪያዎች ውስጥ በመገዝገዝ የምንጫወተው የትኛውን ነው?

   ሀ) በገና ለ) ክራር ሐ) መሰንቆ መ) ቪዮላ

5. ትዝታ ቅኝት ለመመስረት ከሰባቱ ድምፆች ውስጥ የማንጠቀማቸው ድምፆች የትኞችን ነው?

   ሀ) ሁለተኛው እና ስድስተኛው ለ) ሶስተኛው እና ሰባተኛው
   ሐ) አራተኛው እና ሰባተኛው መ) ሶስተኛው እና ስድስተኛው

6. የኢትዮጵያ መሰረታዊ ቅኝቶች የሚመሰረቱት በስንት ድምፆች ነው

   ሀ) ስድስት ለ) አምስት ሐ) ሰባት መ)አራት

7. ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ከአጨዋወታቸው አንፃር በስንት ምድብ ይመደባሉ?

   ሀ) 2 ለ) 3 ሐ) 4 መ) 5

ትዕዛዝ ሁለት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጥሞና በማንበብ ማብራሪያ ስጡ።

8. የአንድ አካባቢ ባህላዊ ውዝዋዜ ከሌላው አካባቢ ባህላዊ ዉዝዋዜ በምን ሊለያይ እንደሚችል ማብራሪያ ስጡ።

9. የድርድር እና የግርፍ የክራር አጨዋወት ልዩነትን አብራሩ።

10. የድምፅ ርቀት እና የቅኝት ግንኙነትን ማብራሪያ ስጡ።

11. በክብረ በዓላት የሚደረጉ ባህላዊ ውዝዋዜዎች በሰርግ ጊዜ ከሚደረጉ ባህላዊ ውዝዋዜዎች በምን እንደሚለዩ ማብራሪያ ስጡ።

12. ባህላዊ ውዝዋዜ ለአንድ ማህበረሰብ የሚሰጠውን ማህበራዊ እና ሥነ- ልቦናዊ ጠቀሜታ ዘርዝሩ።

13. ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን ለምን ከአካባቢ ቁሳቁስ እናዘጋጃቸዋለን ምክንያታችሁን አብራሩ።

14. የኢትዮጵያ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ ምድቦችን በመዘርዘር የተመደቡበትን ምክንያት አስረዱ።

15. ከምታውቁት ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ አንዱን መርጣችሁ ስለ አዘገጃጀቱ ቅደም ተከተል ማብራሪያ ስጡ።


16. የቴያትር ፋይዳን ዘርዝሩ።

17. የዲዛይን አናስሮችን በመዘርዘር ለአንድ የሥዕል ስራ ያላቸዉን ጠቀሜታ ግለጹ።

18. የሚዛን አይነቶችን በመዘርዘር ግልጽ የሆነ ማብራሪያ ስጡ።

19. ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ከባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ጋር ያላቸዉን ልዩነት አብራሩ።

20. ለሚከተሉት የሙዚቃ ድምጾች ትክክለኛ የድምጽ ርቀታቸውን አስቀምጡ።



ትዕዛዝ ሦስት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በተግባር ስሩ።

21. የዲዛይን አናስሮችና መርሆችን በመጠቀም አንድ የስዕል ድርሰት ሰርታችሁ አሳዩ።

22. በአካባቢያችሁ አብዛኛውን ጊዜ የምትጠቀሙበትን ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ በተግባር ሰርታችሁ አሳዩ።

ምዕራፍ 2

ሥነ-ጥበባትን በፈጠራ መግለጽ

የምዕራፉ ዓላማዎች፦

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፦

- በሙዚቃ መጻፊያ ሰሌዳ ላይ የተጻፉ ዜማዎችን እና ኖታዎችን ታነባላችሁ።
- ባህላዊ ውዝዋዜን በተግባር ሰርታችሁ ታሳያላችሁ።
- ሀሳብ እና ስሜታቸውን በተውኔት ትገልፃላችሁ።
- የሻማ ማቅለም የአሰራር ብልሃቶችን ታውቃላችሁ።
- የኪነ-ቅርፅ አሰራርን እና የመስሪያ ቁሳቁሶችን ታውቃላችሁ።
- ማህበራዊ የሆኑ የክውን እና እይታዊ ጥበቦችን ታደንቃላችሁ።
- የሐር ጨርቅ ህትመትን በተግባር ሰርታችሁ ታሳያላችሁ።
- የተለያየ የኪነ-ቅርፅ አይነቶችን በተግባር ሰርታችሁ ታሳያላችሁ።
- በሻማ የማቅለም ተግባርን ሰርታችሁ ታሳያላችሁ።

መግቢያ

በምዕራፍ አንድ የዕይታዊ ጥበባት አናስሮች እና በዲዛይን መርሆች ሥዕልን ማደራጀት፣ የዕይታዊ ጥበባት አናስሮች ሥዕልን ለማደራጀት ያላቸዉ ጠቀሜታ፣ የዲዛይን መርሆች በሥዕል ስራ ዉስጥ ያላቸዉ ጠቀሜታ፣ የኢትዮጵያ የሙዚቃ መሳሪያ ምድቦች፣ የመሰረታዊ የሀገራችን ቅኝቶች አመሰራረት፣ የባህላዊ ውዝዋዜ ምድቦች፣ ስለባህላዊ ሙዚቃ ምድቦች፣ የፊልም እና የቴያትር መሰረታዊ የአዘገጃጀት ደረጃዎች ተምራችኋል።

ይህ ምዕራፍ የፈጠራ ችሎታን የሚያሳድጉ ተጨማሪ ጽንሰ-ሃሳቦችን እና በተግባር የተደገፉ ፈጠራዊ ትምህርቶችን የምትማሩበት ሲሆን በውስጡም በሻማ ማቅለም፣ የሐር ጨርቅ ህትመት፣ ፔፐር ማሼ፣ ኪነ- ቅርፅን መስራት መቻልን፣ በሸክላ አፈር ቅርፅ መስራት፣ ሙዚቃን ማንበብ እና መፃፍ፣ የሙዚቃ ድምፅ ቃናዎችን በሀገራዊ ቅኝቶች መዘመር መቻል፣ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች የተፃፉ ተውኔቶችን በቴያትር እና በፊልም መከወን እና የመድረክ አጠቃቀም እና የባህላዊ ውዝዋዜ አተገባበርን አካቶ የያዘ ምዕራፍ ነው።

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. ሙዚቃን ማንበብ እና መፃፍ ይቻላል? ምክንያታችሁን አስረዱ።
2. ሥነ-ጥበባትን በመጠቀም እንዴት ፈጠራዊ ችሎታን መግለፅ እንደሚቻል ማብራሪያ ስጡ።
3. የቴያትር እና የፊልም መሰረታዊ ልዩነቶችን አስረዱ።
4. የሻማ ማቅለም መሰረታዊ የአሰራር ቴክኒኮችን ዘርዝሩ።
5. የኪነ-ቅርፅ አሰራር ቴክኒኮችን እና ግብዓቶችን ተናገሩ።
6. የሐር ጨርቅ ህትመት የአሰራር ዘዴን ዘርዝሩ።
7. የካስቲንግን ትርጉም ተናገሩ።

2.1 የሙዚቃ ንባብ

ቋንቋዎች በንግግር እና በጽሁፍ የሚገለፁ ናቸው። ቋንቋዎች ድምፅን ሊወክሉ የሚችሉ ምልክቶች እና የአፃፃፍ ስርዓትን ለማስጠበቅ የሚረዱ ምልክቶችም አሏቸው። በተመሳሳይ ሙዚቃ እንደማንኛውም ቋንቋ ሁሉ ዜማዎችን በጽሁፍ ማስቀመጥ የሚያስችሉ እና ድምፆችን የሚወክሉ ዓለም አቀፋዊ ምልክቶች አሉት።

ሙዚቃን ለማንበብ ከሚያስችሉ መሰረታዊ ምልክቶች ውስጥ የሙዚቃ መፃፊያ ሰሌዳ፣ ኖታዎች እና የረፍት ምልክቶቻቸው፣ የመዝጊያ እና የመድገም ምልክቶች እንዲሁም ለዜማዎች አገላለፅ ውበት ለማስጠበቅ ትዕዛዝ የሚሰጡ ምልክቶች(የድምፅ ከፍታ እና ዝቅታ የሚነግሩ፣ የምት ሂደት ፍጥነት እና ዝግታ የሚገልፁ፣ የድምፆችን ርዝማኔ የሚናገሩ ወዘተ ጥቂቶቹ ናቸው።

2.1.1 ሙዚቃን አዳምጦ መፃፍ እና እያዩ ማንበብ (Solfegio)

ሀ) አዳምጦ መፃፍ

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. ሙዚቃን አዳምጦ መፃፍ ምን ማለት ነው?
2. ሙዚቃን አዳምጠን የምንፅፈው መቸ እና እንዴት ነው?
3. ሙዚቃን አዳምጠን መፃፍ ምን ጠቀሜታ አለው?

ዜማዎች የሚዋቀሩት በተለያዩ የድምፅ ቃናዎች በመሆኑ የሰማናቸውን ቃናዎች በሙዚቃ መፃፊያ ሰሌዳ ላይ ኖታዎች እና እረፍት ምልክቶችን ስንፅፋቸው አዳምጦ መፃፍ ይባላል። ተማሪዎች እናንተም መምህራችሁ የሚያሰሟችሁን የሙዚቃ ድምፆች በማዳመጥ በሙዚቃ መፃፊያ ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ልምምድ ታደርጋላችሁ።

ምትን አዳምጦ መፃፍ

በሙዚቃ የዜማ አወቃቀር ሂደት ዜማው እንዲፈጠር ምት መሰረታዊ ግብዓት ነው። ምት ማለት የሙዚቃውን ሂደት የሚወስን እና የሚቆጣጠር ዋና የድምፅ እና የዝምታ ቆይታዎችን መለኪያ ነው። በመሆኑም ዜማን መፍጠር የሚችሉት ቃናዎች እያንዳንዳቸው በምን ያህል ጊዜ መርዘም እና ማጠር እንዳለባቸው የሚወስን በመሆኑ በዜማው ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ ድምፆችን እና እረፍቶችን በጊዜ ገደብ እንድንጫወተው የሚረዳ ነው።

ተግባር 2.1.

1. የሙዚቃ ምልክቶችን አዳምጦ መፃፍ ምን ጥቅም አለው በምሳሌ በማስደገፍ ማብራሪያ ስጡ።
2. መምህራችሁ የሚያሰሟችሁን የድምፅ እና የዝምታ ጊዜ ቆይታዎች አዳምጣችሁ ፃፉ።
3. አዳምጣችሁ የፃፋችሁትን የድምፅ እና የዝምታ ጊዜ ቆይታዎችን በጊዜ አመልካች ምልክት በምድብ ከፋፍላችሁ ፃፉ።

ድምፅን አዳምጦ መፃፍ

በዜማ ቅንብር ውስጥ አንዱ መሰረታዊ አላባዉያን ድምፅ ነው። በጊዜ ተገድበው በኖታዎች የሚቀመጡ የተለያዩ የድምፅ ቃናዎችን በርግብግቦሽ መጠናቸው መሰረት ሰምተን በመለየት በሙዚቃ መፃፊያ ሰሌዳ ላይ ወደ ፅሁፍ ስናሰፍር ድምፅን አዳምጦ መፃፍ ይባላል።

ተግባር 2.2

1. የሙዚቃ ድምፆችን አዳምጦ መፃፍ ምን ጠቀሜታ አለው? ተወያዩ እና በምሳሌ በማስደገፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩ።
2. መምህራችሁ የሚያሰሟችሁን ድምፆች (ዜማ) አዳምጣችሁ ፃፉ።
3. አዳምጣችሁ የፃፋችሁትን ድምፅ (ዜማ) በጊዜ አመልካች ምልክት በምድብ ከፋፍላችሁ ፃፉ።
4. ምትን አዳምጦ መጻፍ እና ድምጽን አዳምጦ መጻፍ ያላቸው ልዩነትን አብራሩ።

ለ) የዕይታ ንባብ

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. የሙዚቃ የዕይታ ንባብ ምን ማለት ነው።
2. የዕይታ ንባብ ምን ጠቀሜታ አለው።
3. የዕይታ ንባብ እና አዳምጦ መፃፍ ልዩነታቸውን አብራሩ።

የዕይታ ንባብ ማለት በጆሯችን የምንሰማቸውን የተለያዩ ዜማዎች በሙዚቃ መፃፊያ ሰሌዳ ላይ በኖታዎች፣ በእረፍት ምልክቶች እና በተለያዩ ምልክቶች ተቀናብረው የተቀመጡትን እያየን በትክክለኛ የጊዜ ቆይታቸው እና የዜማ አካሄዳቸው ስንጫወታቸው (ሲነበቡ) እያዩ ማንበብ ይባላል። ተማሪዎች እናንተም መምህራችሁ የሚሰጧችሁን የተፃፉ ምቶች እና ድምፆች እየተመለከታችሁ ታነባላችሁ።


ምትን እያዩ ማንበብ

ምት ተለዋዋጭ እና ቋሚ (Rhythm and beat) ተብሎ የሚታወቅ ሲሆን ድምፆችን እና ዝምታዎችን በጊዜ የሚቆጣጠር የድምፆች እና ዝምታዎች መለኪያ ነው። በሙዚቃ ስራ ውስጥ የተደራጁ እና ተለክተው የሚቀመጡ ዝምታዎች እና ድምፆች ለዜማ መፈጠር መሰረታዊ ግብዓቶች ናቸው። እነዚሁ ዝምታዎች እና ድምፆች በእረፍት ምልክቶች እና ኖታዎች አማካኝነት በሙዚቃ መፃፊ ሰሌዳ፣ ወረቀት እና ጥቁር(ነጭ) ሰሌዳ ላይ በጊዜ ዋጋቸው መሰረት ይቀመጣሉ። እነዚህ የተፃፉ ኖታዎች እና የእረፍት ምልክቶች ዋጋቸውን (የጊዜ መጠናቸውን) ጠብቀ እየተመለከቱ በአንድ ድምፅ ላይ ብቻ ተመስርቶ መከወን ምትን እያዩ ማንበብ ይባላል።


ተግባር 2.3

የሚከተሉትን ኖታዎች እና እረፍት ምልክቶችን እያያችሁ የጊዜ ቆይታቸውን ጠብቃችሁ አንብቡ።


1. ሁለት በሁለት የተፃፉ ድምፅ እና ዝምታን የሚወክሉ ምልክቶችን ማንበብ



2. በሁለት በአራት የተፃፉ ድምፅ እና ዝምታን የሚወክሉ ምልክቶችን ማንበብ



3. ስድስት በስምንት የተፃፉ ድምፅ እና ዝምታን የሚወክሉ ምልክቶችን ማንበብ




ድምፅን እያዩ ማንበብ

በሙዚቃ ስራ ውስጥ የተደራጁ እና ተለክተው የሚቀመጡ ዝምታዎች እና ድምፆች ለዜማ መፈጠር መሰረታዊ ግብዓቶች መሆናቸውን ተመልክታችኋል። እነዚሁ ዝምታዎች እና ድምፆች በእረፍት ምልክቶች እና ኖታዎች አማካኝነት በሙዚቃ መፃፊ ሰሌዳ፣ ወረቀት እና ሰሌዳ ላይ በጊዜ ዋጋቸው መሰረት ይቀመጣሉ።

እነዚህ ድምፅን እና ዝምታን ወክለው የተቀመጡ ኖታዎች እና እረፍት ምልክቶች እያንዳንዱ የድምፅ ዋጋ እና የርግብግቦሽ መጠናቸውን ጠብቆ የሙዚቃ ፅሁፉን እየተመለከትን መከወን ድምፅን (ዜማን) እያዩ ማንበብ ይባላል።

ተግባር 2.4

1. የሚከተሉትን በሙዚቃ መፃፊያ ሰሌዳ ላይ በኖታዎችን እና በእረፍት ምልክቶች የተፃፉ ዜማዎችን በድምፅ ዜማቸውን እያያችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ።




2. ምትን እያዩ ማንበብ እና ድምጽን እያዩ ማንበብ ያላቸውን ዝምድና አብራሩ።


2.1.2 በአንችሆየ እና በአምባስል ቅኝት የተጻፉ መዚቃዎችን እያዩ ማንበብ

ሀ) በአንችሆየ ቅኝት የተጻፉ መዚቃዎችን ማንበብ (መዘመር)

ተግባር 2.5

1. የሚከተሉትን በስታፍ ላይ የተጻፉ አንችሆየ ቅኝት እና ዜማዎች በድምጽ ዘምሯቸው







ለ) በአምባሰል ቅኝት የተጻፉ ዜማዎችን ማንበብ (መዘመር)

ተግባር 2.6

1. የሚከተሉትን በስታፍ ላይ የተጻፉ አምባሰል ቅኝት እና ዜማዎች በድምጽ ዘምሯቸው







በአምባሰል ቅኝት የተሰራ መዝሙር

የመዝሙሩ ርዕስ፦ ስራ

እስቲ እንስራ በስራ እንክበር፤
መሰረት ነው ለሁሉም ነገር፤
አዝማች
ትንሽ ትልቅ ሳንል ስራን አንናቀው፤
ትንሽ ሲጀመር ነው ትልቅ የሚሆነው፤(2)
ስንፍናን ከለመድን እናንቀላፋለን፤
ከሱ ኋላ ቀርተን እንጎተታለን፤
ረሃብ ያጠቃናል እንጠወልጋለን፤
ሁል ጊዜ ተመጽዋች ለማኝ እንሆናለን።





2.2 የባህላዊ ውዝዋዜ አተገባበር

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. በአካባቢያችሁ ባህላዊ ውዝዋዜን ለመስራት የምትጠቀሙባቸውን ቁሳቁሶች በመዘርዘር እንዴት እና ለምን አገልግሎት እንደምትጠቀሙባቸው አብራሩ።
2. በአካባቢያችሁ ባህላዊ ውዝዋዜን ለመተግበር የምታደርጓቸውን ቅደም ተከተሎች በዝርዝር ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

ባህላዊ ውዝዋዜ የማንነት መገለጫ ስለሆነ ውዝዋዜውን ስናከናውን የአለባበስ

ሁኔታን፣ ስልተ ምቱን፣ ጥቅም ላይ የሚውሉ ቁሳቁሶችን እና ኬሮግራፊውን የአካባቢውን ባህል በትክክል የሚገልጹ መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው።

ባህላዊ ውዝዋዜ እንደየአካባቢው ባህል እና የውዝዋዜ ስልት ልዩነት አለው። ለምሳሌ በጎጃም አካባቢ የሚዘወተረው ባህላዊ ውዝዋዜ በእጅ እና መላው የሰውነት ክፍል እንቅስቃሴ ላይ ሲሆን የወሎ አካባቢ ውዝዋዜ ስልት ትኩረት የሚያደርገው ደግሞ ከትከሻ እና ከአንገት እንቅስቃሴ ጋር የተዛመደ ሆኖ የአካል እንቅስቃሴው የተረጋጋ እና ሀይል የሚፈልግ ነው።

በአጠቃላይ የአንድን አካባቢ ባህላዊ ውዝዋዜን ለመተግበር በመጀመሪያ ደረጃ የአካባቢውን አጠቃላይ ባህል ማወቅ ያስፈልጋል። ለምሳሌ፦

ከአለባበስ፦ በሰርግ፣ በባዓላት፤ ወንዶች፣ ሴቶች ባህላዊ ውዝዋዜን ሲከውኑ የሚለብሱትን መለየት

ከውዝዋዜ ስልት፦ በምን? በህብረት፣ በጥንድ፣ በቡድን እንዲሁም የእጅ እንቅስቃሴ፣ የትከሻ፣ የእግር፣ የመሳሰሉትን በግልጽ ማወቅ ያስፈልጋል። ከዚህ በታች እንደ ምሳሌነት የተቀመጡትን የውዝዋዜ አተገባበር ቅደም ተከተሎች መሰረት በማድረግ ትክክለኛ የአካባቢውን ባህል በመጠበቅ በተግባር ተግብራችሁ ታሳያላችሁ፦

ሀ) የወሎ ውዝዋዜ ለመተግበር ቅደም ተከተል

- በመጀመሪያ ደረጃ የአካባቢውን ባህላዊ አልባሳት መልበስ
- ለትንሽ ደቂቃ መሮጥ እና ሰውነትን ማፍታታት
- ትከሻን፣ አንገትን እና ወገብን ማነቃቃት
- በእጃችን ወገብን ያዝ ማድረግ
- ትከሻን ወደ ላይ እና ወደታች ማንቀሳቀስ
- ትከሻን ከምት ጋር ወደላይ እና ወደታች በፍጥነት ማንቀሳቀስ
- ትከሻን በመድገም ወደ ላይ ማንቀሳቀስ
- በመጨረሻም ትከሻን በፍጥነት ወደ ላይ እና ወደታች እንዲሁም ወደ ግራ እና ወደ ቀኝ ከስልተ ምቱ ጋር በፍጥነት ማንቀሳቀስ

ለ) የጎጃም ዝናብ እንቅጥቅጥን ለመስራት

- የአካባቢውን ባህላዊ አልባሳት መልበስ
- ለትንሽ ደቂቃ መሮጥ እና ሰውነትን ማፍታታት
- ሁሉንም የሰውነት ክፍል በደንብ ማንቀሳቀስ
- ትክሻን ወደፊት ወደ ኋላ ማንቀሳቀስ
- ከደረት ጋር ትክሻን ወደ ላይ እና ወደ ታች እንዲንቀሳቀስ ማድረግ
- ከስልተ ምቱ ጋር ደረትን እና ትክሻን በፍጥነት ማንቀሳቀስ እና መንቀጥቀጥ

ተግባር 2.7

1. የአንድ አካባቢ ባህላዊ ውዝዋዜ ስልት በመምረጥ እንዴት እንደሚተገበር የአሰራር ቅደም ተከተሉን ማብራሪያ ስጡ።
2. አንድ ባህላዊ ውዝዋዜ ለመተግበር የአተገባበር ቅደም ተከተሉን ጠብቆ መከወን ምን ጠቀሜታ አለው ትላላችሁ? ተወያዩ እና ለክፍል መምህራችሁ ተናገሩ።
3. በሀገራችን እና በክልላችን ከሚታወቁ ባህላዊ ውዝዋዜ ስልቶች መካከል አንዱን በመምረጥ በተግባር የአሰራር ቅደም ተከተሉን በማሳየት ከውናችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ እና ለመምህራችሁ አሳዩ።

2.3. ቴያትር እና ፊልምን መተግበር

2.3.1 የቴያትር የልምምድ ሂደት

የቴያትር ዝግጅት ራሱን የቻለ የልምምድ ሂደት አሉት።

- **የመጀመሪያ ንባብ፦** ተዋናኞቹ ጽሑፉን (ድርሰቱን) ቀደም ብሎ ቢደርሳቸውም ከተውኔቱ ጋር የሚተዋወቁበት፣ ምን እንደሚናገሩ እና ከማን ጋር እንደሚነጋገሩ የሚገነዘቡበት ጊዜ ነው።

አንድ ተዋናኝ በመጀመሪያው የንባብ ወቅት እንዴት መባል እንዳለባቸው የማያውቃቸውን አዳዲስ ቃላት፣ ትርጉማቸው ግልጽ ያልሆኑ ዓረፍተ ነገሮች ቢገጥሙት ሊጨነቅ የማይገባበት ጊዜ ነው። ምክንያቱም ከመጀመሪያው ንባብ በኋላ እና በቀሪዎቹ የልምምድ ጊዜያት በመወያየት እና ደጋግሞ በመሞከር ግልጽ

እየሆነለት ስለሚመጣ ነው። ስለዚህ ተዋናዮቹ በመጀመሪያው ንባብ ትናንሽ፣ ቀላል እና ሊያስወግዷቸው ከማይችሏቸው ጥቂት የተለመዱ አገላለጾች በስተቀር ልክ እንደ ትወና ተመስጦ እና ስሜት ውስጥ በመግባት ማንበብ አስፈላጊ ያልሆነበት የልምምድ ጊዜ ነው።

- **ተቀምጦ የሚደረግ የንባብ ልምምድ፦** ከመጀመሪያው የንባብ ልምምድ ቀጥሎ አዘጋጁ ተዋናዮቹን ጽሑፉን (ድርሰቱን) ይዘው በጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠው የንባብ ልምምድ እንዲያደርጉ የሚደረግበት የልምምድ ጊዜ ነው።

በዚህ የልምምድ ወቅት ከእያንዳንዱ ተዋናኝ መድረክ ላይ ከመቆመ በፊት የሚጠበቁ

- ጽሑፉን (ድርሰቱን) መርምሮ ለመርዳት እድል ማግኘት
- ቃለ ተውኔቱን ከሚመላለሰው ተዋናይ ጋር መተዋወቅ
- የሚወክለውን ገጸባህሪ አላማ በትክክል መረዳት
- የአዲስ ቃላትን አባባል (የስሞችን አጠራር ማጥናት)
- በየትዕይንቱ መቼ እንደሚገባ፣ ከየት እንደሚመጣ፣ መድረኩንም እንዴት እንደሚያልቅ እና ወዴት እንደሚሄድ እርግጠኛ መሆን።

በአጠቃላይ በዚህ የንባብ ልምምድ ወቅት ስለ ሚወክለው ገጸባህሪ ማንነት፣ በተውኔቱ ውስጥ ስላለው ሚና፣ ስለቀደምት ማንነቱ እና ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮችን ከአዘጋጁ ጋር በመወያየት እውቀቱን የሚያዳብርበት የልምምድ ወቅት ነው።

- **የመድረክ እንቅስቃሴ፦** ይህ ሰዓት ተውኔቱን መድረክ ላይ በእግሩ ለማቀም የሚደረግ የእንቅስቃሴ ሂደት ነው። ተዋናያን በአዘጋጁ በሚሰጣቸው መመሪያ መሰረት ድራማዊ ድርጊቱን የሚገልጹበት፣ ውበት እና ትርጉም ያላቸውን እንቅስቃሴዎች የሚከውኑበት የልምምድ ወቅት ነው።



ሥዕል 23 የቴያትር የመድረክ እንቅስቃሴን እና ልምምድን የሚያሳይ

የቴያትር የልምምድ አይነቶች

- **የቃል ጥናት፦** ተዋናያን ጽሑፉን ጥለው በቃል ልምምድ አድርገው የሚጨርሱበት ጊዜ ነው።
- **የሙከራ ልምምድ፦** ተዋናንያን የቃል ጥናታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ አዘጋጁ ነጻ ሆኖ ገቢሮችን፣ ትዕይንቶችን እና የተዋንያንን ስሜት ለመለካት ደግሞ ደጋግሞ የሚሞክርበት ጊዜ ነው።

በዚህ ልምምድ ወቅት አዘጋጁ የራሱን እና ከተዋንያኑ ያገኘውን ገንቢ ሀሳብ አቀናጅቶ የተሻለውን ለተውኔቱ የሚያቀርብበት የልምምድ ወቅት ነው።

- **ድንገቴ ፈጠራ፦** በልምምድ ወቅት የሚሰሩ ድንገቴ ፈጠራዎች ናቸው።
- **ያለማቋረጥ ትርዒቱን ሙሉውን መወጣት፦** በአዘጋጁ የታቀደውን እና የተመረጠውን የተውኔት ሀሳብ በመድረክ ላይ ሳያቋርጡ መከወን ነው። በዚህ ወቅት ቁሳቁስ ብንረሳ፣ ቃላት ብንዘነጋ እና የመሳሰሉት ችግሮች ቢያጋጥሙን የምንጠቀመውን ተጠቅመን መቀጠል ነው ያለብን።
- **አልባሳትን መለካት፦** በዚህ የልምምድ ወቅት ከገጸ-ባህሪው ጋር ተስማሚ የሚሆን ልብስ የሚመረጥበት ሂደት ነው።
- **የአልባሳት ትርኢት፦** ከመጀመሪያ የቴክኒክ ልምምድ በፊት ዲዛይነሮች፣ ልብስ ሰፊው፣ የጸጉር ባለሞያው፣ የመድረክ አስተባባሪው እና አዘጋጁ በተገኙበት በሙሉ የመድረክ መብራት እያንዳንዱ ተዋናይ ተራ በተራ በለበሰው ልብስ ምን እንደሚመስል የሚገመገምበት ነው።

- **የቴክኒክ ልምምድ፦ በዚህ ወቅት አዘጋጁ ከቴክኒክ ሰዎች ጋር ቴክኒካል በሆኑ ጉዳዮች ጋር በመወያየት መድረክ ላይ በተዋንያን ዘንድ ምን እንደሚመስል የሚያረጋግጥበት ወቅት ነው።**

በዚህ ቴክኒክ ልምምድ ወቅት ምን ሰዓት መጋረጃ እንደሚከፈት፣ ሙዚቃ መቼ እንደሚገባ፣ ስልክ መቼ እንደሚጮህ፣ ትይንት መቼ እንደሚለወጥ እና በር መቼ እንደሚከፈት በነዚህ ጉዳዮች ላይ ከተዋንያን የሚገመገምበት ነው።

- **የፍጻሜ ልምምድ፦ በዚህ ወቅት ሁሉም ተዋናይ ያለማቋረጥ ቴያትሩን በሙሉ ብቃት የሚተውኑበት ወቅት ነው።**

የስንብት ልምምድ፦ ይህ ወቅት ደግሞ የቴያትሩ መጨረሻ የሚያመለክት ሲሆን ተዋናዮቹ እጅ ነስተው ወደ መጋረጃ የሚገቡበት ወቅት ነው። ከላይ በተሰጠው የቴያትር ልምምድ ገለፃ መሰረት ከዚህ በታች የተቀመጠውን የቴያትር መነሻ ድርሰት ቃለ ተውኔቱን መምህራችሁ በሚነግሯችሁ አቅጣጫ መሰረት በተግባር ሰርታችሁ ታሳያላችሁ።

የቴያትሩ ርዕስ፦ ሰላም

ገጸ ባህሪያት

አቶ አበበ፦ የአርባ ሁለት አመት ወጣት ነጋዴ

ያለምወርቅ፦ የሀያ አምስት አመት ወጣት ስራ አስኪያጅ

ተዋበች፦ የሀያ አመት ልጅ፤ የአቶ አበበ ልጅ

አቶ ባለው፦ የአምሳ አመት አባውራ ነጋዴ

የተውኔቱ ታሪክ

አቶ አበበ እና አቶ ባለው አንድነት ተብሎ በሚጠራ ቀበሌ የሚኖሩ በንግድ ስራ የሚተዳደሩ ነዋሪዎች ናቸው። አቶ አበበ ከትዳር አጋራቸው የወለዷቸው ሁለት ልጆች ያሏቸው ሲሆን አቶ ባለውም እንዲሁ ከትዳር አጋራቸው የወለዷቸው አራት ልጆች አሏቸው። ወ/ሮ ያለምወርቅ፣ አቶ አበበ እና አቶ ባለው በሚኖሩበት የአንድነት ቀበሌ ስራ አስኪያጅ ሲሆኑ እንዲሁም በቀበሌው ሰላምን ለማረጋገጥ እና የአካባቢው ኗሪዎች በሰላም በመከባበር እንዲኖሩ የሚያደርግ እና ህግ የሚያስከብር ሳጅን አጥናፍ ደግሞ የቀበሌው ፖሊስ ነው። ከእለታት በአንድ ቀን ስለ አካባቢያቸው

ሰላም ደህንነት ጉዳይ ሲወያዩ ያደረጉት የውይይት ሃሳብ በሚከተለው መንገድ ቀርቧል። ይህንን ተግባር በቡድን በቡድን ሆናችሁ መምህራችሁ በሚነግሯችሁ አቅጣጫ መሰረት ቃለ ተውኔቱን በቴያትር ተውናችሁ በማሳየት ጥሩ የተወነውን ቡድን ለዩ።

ቃለ ተውኔት

አቶ አበበ፦ ከሱቁ በር ላይ (በትካዜ ነገሩን እያሰላሰለ) ቁሟል።

አቶ ባለው፦ እንዴት አደራችሁ? (ከአንገቱ ዝቅ በማለት) ምነው? ነገር የገባህ ትመስላለህ።

አቶ አበበ፦ እንዴት አደራችሁ? ወቸው ጉድ ምን እማያሳስብ ነገር አለ ብለኽ ነው የኑሮ ውድነቱ ሊያሰድደን አይደለም እንዴ አቶ ባለው።

አቶ ባለው፦ አይ አቶ አበበ ምን እሱማ ምኑ ይነገራል ባይሆን በሰላም የመኖሩ ጉዳይ ይቀድማል ብለን ነው እንጅ።

አቶ አበበ፦ እረ ተው ይሄ ነገር መቅደም ያለበት መጀመሪያ በልቶ ማደር ነው የሚሻለው ሰው ካልበላ እና ሆዱ ካልሞላ ሰላም መሆን ምን ያደርጋል።

አቶ ባለው፦ ምነው አቶ አበበ እንዴት ሰው በሰላም ወጥቶ አምርቶ እና ነግዶ በሰላም ካልገባ እንዴት ሆዱን መሙላት ይቻላዋል ተው እንጅ ወዳጄ

አቶ አበበ፦ እኔ ሰላም ሀገር የሚባለው ነገር አይገባኝ የምን ሰላም እና ሀገር ነው ወድያ በልልኝ። (እያለ ሲናገር ልጁ ተዋበች በድንገት ትሰማዋለች)

ተዋበች፦ ደህና አደራችሁ በጥዋት እንዴት ተገናኛችሁ? (ባባቷ ንግግር እየተበሳጨች)

አቶ አበበ፦ ተዋብየ መጣሽ እንዴ? (በአክብሮት ስሜት)

ተዋበች፦ አዎ አባቴ

አቶ ባለው፦ እየውልሽ ልጄ በጠዋቱ አባትሽ ክርክር ገጥሞኛል።

ተዋበች፦ በምን ጉዳይ እየተከራከራችሁ ነው (ነገሩን አንዳልሰማች በማስመሰል)

አቶ ባለው፦ ለሰው ልጅ በሕይወት ለመኖር ዋስትና ስለሆነው ሰላም እና ስለሆድ ሞልቶ ማደር ነው ልጄ

ተዋበች፦ ይሄማ በጣም ጥሩ ነገር ነው ሰላም ከሌለማ ወጥቶ መግባት እንኳን ይቸግራል እኮ እንኳንስ ሰርቶ እና በልቶ ለማደር ዋናው ነገር ሰርቶ እና በልቶ ለማደር ሰላም ቁልፍ ነገር ነው።

አቶ አበበ፦ (በቁጣ) አንች ደግሞ ስለ ሰላም ምን ታውቂና ነው ሰርቼ የማበላሽ እኔ ምኑን ታውቂውና ደግሞ እኮ ታፈጥብኛለች

ተዋበች፦ አይ አባቴ እንደሱ አይደለም ሀገራችን፣ አካባቢያችን እና መንደራችን ሁሉ ሰላም ሲሆን ብቻ ነው ሌላው ነገር ሁሉ ሙሉ የሚሆነው እና ሰርተን መኖር የምንችለው። ስለዚህ ሰላም በጣም አስፈላጊ ነው።

አቶ ባለው፦ ተባረኪ ልጄ እንዲህ ነው እንጅ ልጅ ማለት

አቶ አበበ፦ አሃሃሃ እኔማ መች አውቄ ለካ ሰርቶ ለማደርም ወጥቶ ለመግባትም የሰላም ዋጋው ከፍ ያለ ነው

አቶ ባለው፦ ለነገሩ የቀበሌያችን ስራ አስኪያጅ ወ/ሮ ያለም ወርቅ ሰብስበው ስለሰላም ዋጋ ሲናገሩ አልነበርክም ለካ ለምን ትቀራለህ

አቶ አበበ፦ ልክ ብለሃል ምን የኔ ነገር ወደ ስራው ብቻ እየተሯሯጥኩኝ እኮ ነው እንግዲህማ በሀገሬ በሰላም ጉዳይ አልደራደርም

ተዋበች፦ አባቴ በጣም ደስ ብሎኛል እኔም ሀገሬ ሰላም ሆና እንድትኖር ዋጋ እከፍላለሁ። በማለት በአንድነት ሰላም ተባብለው ወደ ቤት ይሄዳሉ።

ተግባር 2.8

1. ከላይ ከቀረበው ተውኔት ምን እንደተገነዘባችሁ ለክፍል መምህራችሁ ተናገሩ።
2. አንድ ቴያትርን ለመከወን የሚያስፈልጉ መሰረታዊ ነገሮች ምን ምን ናቸው?
3. የአንድ ቴያትር ጭብጡ እና ሴራው ያለውን ልዩነት ማብራሪያ ስጡ።
4. ቴያትር ለህብረተሰቡ የሚሰጠውን ጠቀሜታ አብራሩ።

5 ከላይ ባያችሁት የቴያትር ድርሰት መሰረት አንድ በአካባቢያችሁ ከሚገኝ ታሪክ በመነሳት አጭር የቴያትር ድርሰት በመጻፍ በተግባር ከውናችሁ አሳዩ።

2.4. በሻማ ማቅለም (Batik)

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. የሻማ ማቅለም ምንነትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።
2. የአስሮ ማቅለም አሰራር አይነቶችን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።
3. የሻማን ባህሪ በማስታወስ እንዴት በማቅለም ልንሰራበት እንደምንችል ያላችሁን አስተያየት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

ህትመት በልዩ ልዩ መንገድ የሚሰራ ሥነ -ጥበባዊ ተግባር ነው። አንድን ምስል በማላተም ወይም ቀለም በማሳለፍ ምስሉን ሌላ አካል ላይ የማስቀረት ሂደት ነው። ካለፋችሁት የክፍል ደረጃ ስለ ቀጥታ ህትመት፣ ስለ ቀርፃ ማውጣት ህትመት እና የስቴንስል ህትመት አሰራርና ምንነት ተምራችኋል። በዚህ የክፍል ደረጃ ደግሞ በሻማ ማቅለም እና የሲልክ ስክሪን ህትመት ምንነትን እንማራለን።


በሻማ ማቅለም ማለት ሻማን እንደ ግብዓትነት በመጠቀም ጨርቅን የማቅለም ስራ ነው። ይህም ሻማን በማቅለጥ እንዲቀልም የተፈለገው ጨርቅ ላይ በማፍሰስ ረግቶ እንዲቀመጥ በማድረግ ጨርቁን የማቅለሚያ ፈሳሽ ቀለሙ እንዳያገኘው በማድረግ የሚሰራ ነው። ሻማ ከውሃ ጋር ስለማይዋሀድ በቀለጠ ሻማ የተቀባው የጨርቁ ክፍል የማቅለሚያ ቀለሙ ሳያገኘው ይቀራል። ስለዚህ እንዲቀልም የማንፈልገው ቦታ በቀላሉ በሻማው ይሸፈንልናል። በመቀጠልም ሻማውን በካውያ በመተኮስ ከጨርቁ ላይ ማጽዳት እንችላለን። ይህም የተለየ ጨርቅን የማቅለም ሂደት ለማግኘት ያስችለናል።

አስፈላጊ መሳሪያዎችና የአሰራር ቅደም ተከተል

- የሚቀልም ጨርቅ፣ የማቅለሚያ ቀለም፣ ጋዜጣ፣ ካውያ፣ የቀለጠ ፈሳሽ ሻማ፣ ጠረጴዛ ወይም ጠፍጣፋ ወለል

የአሰራር ቅደም ተከተል

- የሚቀልመውን ጨርቅ ጠፍጣፋ ወለል ላይ ወይም ጠረጴዛ ላይ መዘርጋት፤
- ጨርቁ የሚቀልምበትን ክፍል መለየትና የቀለጠውን ሻማ ጨርቁ ላይ ማፍሰስ፤
- ጋዜጣውን በቀለጠው ሻማ ክፍል ላይ በማልበስ በካውያ ጨርቁን መተኮስ፤
- ከጨርቁ ላይ ሻማው እስኪጠፋ ድረስ በጋዜጣው ላይ ደጋግሞ መተኮስ፤
- ባልቀለመው ቦታ ድጋሜ የቀለጠውን ሻማ በማፍሰስ በሚፈለገው ዲዛይን መሰረት ጨርቁን ማቅለም እና በካውያ እየተኮሱ ከጨርቁ ላይ ሻማውን ማስወገድ፤



ሥዕል 24 የሻማ ማቅለም አሰራር ቅደም ተከተል

ተግባር 2.9

1. ተማሪዎች በቡድን በመሆን ከላይ የቀረበውን በሻማ ማቅለም አሰራርና ቅደም ተከተል መሰረት በማድረግ በሻማ የጨርቅ ማቅለም ስራ ሰርታችሁ ለጓደኞቻችሁ እና ለመምህራችሁ አሳዩ።
2. የሻማ ማቅለም አሰራር ከአስሮ ማቅለም አሰራር በምን ይለያል?

2.5 በሐር ጨርቅ ማተም (Silk screen printing)

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. ተማሪዎች የተለያዩ ልብሶች ላይ የምታዮቸው ጽሁፎችና ሥዕሎች እንዴት እንደታተሙ ጠይቃችሁ ታውቃላችሁ? እስኪ ለጓደኞቻችሁ ስለ አልባሳት ህትመት ምንነት የምታውቁትን ተናገሩ።
2. የሐር ጨርቅ ለልዩ ልዩ የህትመት ስራ ተመራጭ የሆነው ለምን ይመስላችኋል?

የሐር ጨርቅ ህትመት ከስቴንስል የህትመት አሰራር አይነቶች አንዱ ሲሆን ከወረቀት ስቴንስል ህትመት የሚለየው የሀር ጨርቅ ላይ ያሉ ቀዳዳዎችን እንዲታተም ከተፈለገው ነገር በተቃራኒ በመድፈን የሚሰራ በመሆኑ ነው።

የሐር ጨርቅ በጣም ጥቃቅን ቀዳዳዎች አሉት። እነዚህ ቀዳዳዎች ቀለም ለማሳለፍ የተመቹ ናቸው። የሐር ጨርቅ በሚገባ ከተወጠረ በኋላ እንዲታተም ከተፈለገው ነገር በተቃራኒ ያሉትን የጨርቁን ቀዳዳዎች በመድፈን እና ክፍት በሆነው ደግሞ ቀለም በማሳለፍ ህትመት መስራት ይቻላል። ይህ ዘዴ የሐር ጨርቅ ህትመት ይባላል። የሐር ጨርቅ ህትመት አንድን ነገር በአንድ ቀለም እና በባለ ብዙ ቀለም ህትመት ለመስራት የተመቸ ሲሆን ከወረቀት ስቴንስል ህትመት የተሻለ አንድ ጊዜ በርካታ ቁጥር ያላቸው ህትመቶችን ለማዘጋጀት ያስችለናል።


የሐር ጨርቅ ህትመት ለመስራት የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች እና የአሰራር ቅደም ተከተል

የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች

- በእንጨት ፍሬም የተወጠረ የሐር ጨርቅ
- እንዲታተም የተፈለገው ነገር ወይም ምስል
- ሴንቲሳይዘር፣ የከሰል ፍም መቀት ወይም የኤሌክትሪክ ምድጃ
- ብርሃን አስተላላፊ ፕላስቲክ ወረቀት
- የህትመት ቀለም ጥቁር፣ ቢጫ፣ ሲያን እና ማጀንታ ለህትመት የተዘጋጁ
- የቀለም መቀቢያ የእንጨት መግፊያ
- ውሃ እና የጨለማ ክፍል
- የብርሃን ሳጥን በመብራት የሚሰራ
- ወፍራም ልብስ

የአሰራር ቅደም ተከተል

- እንዲታተም የተፈለገውን ነገር በብርሃን አስተላላፊ ወረቀት ላይ ማዘጋጀት፤
- የሐር ጨርቁን በጨለማ ክፍል ውስጥ ሴንቲሳይዘር መቀባት እና ማድረቅ፤
- በብርሃን አስተላላፊ ወረቀት ላይ ያለውን ሴንቲሳይዘር ተቀብቶ ወደ ደረቀው የሐር ጨርቅ ለማስተላለፍ የብርሃን ሳጥኑ ላይ ደፍቶ በማስቀመጥ ወፍራም ልብስ መሸፈን እና ከፍተኛ ብርሃን አብርቶ ለተወሰነ ደቂቃ እንዲቃጠል ማድረግ፤
- በመቀጠል የሐር ጨርቁን ውሃ እየረጩ ማጠብ ይህ በሚሆንበት ጊዜ እንዲታተም የተፈለገው ነገር ብርሃን ያልነካው ይሆን እና ብርሃኑ ያቃጠለው ቀሪው ክፍል የሐር ጨርቁን ይደፍነዋል ይህም የሚታተመው ክፍል ቀዳዳ ሆኖ እንዲቀር ያደርገዋል፤
- በመቀጠል የሐር ጨርቁ ላይ የህትመት ቀለም በማፍሰስ እና በቀለም መግፊያው በመቀባት የሚፈለገው ቦታ ላይ ደግሞ ደጋግሞ ማተም ይቻላል።



ሥዕል 25 የሐር ጨርቅ ህትመት ስራ

ተግባር 2.10

1. ተማሪዎች የሐር ጨርቅ ህትመት ስራ ለመስራት አስፈላጊ የሆኑ መሳሪያዎችን እና የአሰራር ቅደም ተከተሎችን በማስታወስ ስለ ሐር ጨርቅ ህትመት ምንነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ገለጻ አድርጉ።

2. ተማሪዎች በቡድን በመሆን በአካባቢያችሁ የምታገኙትን የሐር ጨርቅ በአራት መዓዘን እንጨት ላይ በመወጠር የእጅ አሻራችሁን ወፍራም ወረቀት ላይ ቀርጻችሁ በሴንቲ ሳይዘሩ ፋንታ የተቀረጸውን ወፍራም ወረቀት በእንጨት የተወጠረው የሐር ጨርቅ ላይ በመለጠፍ የግድግዳ ቀለምን ተጠቅማችሁ የእጅ አሻራችሁን በማተም ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ።

2.6 ኪነ-ቅርፅ (Sculpture)

2.6.1 ካስቲንግ (Casting)

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. ተማሪዎች በቤታችሁ ያሉ የፕላስቲክ እቃዎች የቅርፅ መመሳሰልን አስተውላችሁ ታውቃላችሁ? የውሃ ጀግ፣ ባልዲ፣ ኩባያ የመሳሰሉት እንዴት ተደጋግመው በተመሳሳይ መጠንና ቅርፅ ሊሰሩ እንደቻሉ የምትገምቱትን ለጓደኞቻችሁ አብራሩላቸው።

የኪነ-ቅርፅ ስራዎች በቁስ እና በአሰራር የተለዩ ቢሆኑም በመሰረታዊነት በእነዚህ በአራቱ የአሰራር ስልቶች የሚካተቱ ናቸው። ኪነ-ቅርፅ ከሥነ-ጥበብ ዘርፎች መካከል አንዱ ሲሆን በመጨመር ወይም በመቀነስ ሞዴሊንግ (Modeling)፣ ወደ ውስጥ በመፋቅ ወይም መቅረጽ (Carving)፣ በማያያዝና መገጣጠም (Assembling) እና ካስቲንግ (Casting) ባለ ሁለት እና ባለ ሶስት አውታረ መጠን ምስል የምናዘጋጅበት ዘርፍ ነው።

ካስቲንግ ወይም ኪነ-ቅርፅን ማራባት (Casting) በአብዛኛው ከፈሳሽ ወደ ጥጥር ከጥጥር ወደ ፈሳሽ መለወጥ የሚችሉ ቀላጭ ቁሳቁሶችን ሞልድ ላይ በማፍሰስ ኪነ-ቅርፅን የማራባት ወይም ከአንድ ቁስ የተሰራን ቅርፅ ወደ ሌላ ቁስ የመቀየር ዘዴ ነው። በቀላሉ ከቤታችን ያለን ሻማ ስኒ ላይ ብናቀልጥና እንዲረጋ ብናደርገው የረጋው ሻማ የስኒውን ቅርፅ ይዞ ይወጣል። ይህን ቀላል አሰራር ውስብስብ ለሆኑ የቅርፅ ስራዎችም በመተግበር አንድን የጭቃ ቅርፅ ወደ ጂፕሰም፣ ወደ ሲሚንቶ ወደ ነሀስ እና ሌሎች ቁሶች መለወጥ ይቻላል። ወይም ደግሞ አንድ ቅርፅ በብዙ ቁጥር ደጋግሞ ለማምረት ይቻላል።

በጀሶ ካስቲንግ ለመስራት የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች እና የአሰራር ቅደም ተከተል

- በጭቃ የተሰራ ቅርፅ ወይም ለካስቲንግ የተዘጋጀ ቅርፅ፤
- ጀሶ፣ ውሃ፣ ባልዲ፣ የጆንያ ቁርጥራጭ ወይም ጨርቅ፤
- ፈሳሽ ሳሙና ወይም ቫዝሊን የመሳሰሉት ያስፈልጋሉ፤

የአሰራር ዘዴ

- ካስት የሚደረገውን ቅርፅ ለማውጣት በሚመች መልኩ መከፋፈልና ዝግጁ ማድረግ፤
- በመጀመሪያ በባልዲው ላይ ውሃ በማድረግ ጄሶውን በቀጭኑ መበጥበጥ፤
- የተበጠበጠውን ጄሶ ለካስቲንግ በተዘጋጀው ቅርፅ ላይ መርጨት፤
- በድጋሜ ከመጀመሪያው ወፈር በማድረግ ጄሶ መበጥበጥና ቅርጹ ላይ መርጨት፤
- ሁለት ሶስቱ ደጋግሞ ጄሶውን በመርጨት ቁርጥራጭ ጆንያ መለጠፍ፤
- ከ15 ደቂቃ በኋላ በቅደም ተከተል የደረቀውን ጄሶ ከቅርጹ ላይ ማንሳት፤
- ጄሶው የቅርጹን ኔጋቲቭ ምስል ይዞ ይወጣል ይህም ሞልድ ይባላል፤
- በመቀጠል ሞልዱን ፈሳሽ ሳሙና ወይም ቫዝሊን መቀባት፤
- ከዚያ ጄሶ በቀጭኑ በመበጥበጥ ሞልዱ ላይ ማፍሰስ፤
- በድጋሜ በወፍራሙ በመበጥበጥ ጄሶውን ሞልዱ ላይ ማፍሰስ፤
- በመጨረሻም ከ15 ደቂቃ በኋላ ከሞልዱ ላይ ፖዝቲቭ የጄሶ ቅርጹን ለይቶ ማንሳት።።



ሥዕል 26 በጭቃ የተሰራ የሞዴሊንግ ቅርፅ



ሥዕል 27 ለካስቲንግ የተዘጋጀ የጭቃ ቅርፅ ጄሶ ሲቀባ ወይም ሲረጭበት





ሥዕል 28 ካስት የሆነው የጭቃ ቅርፅ እና ኔጋቲቭ ምስል ወይም ሞልድ

ተግባር 2.11

1. የካስቲንግ የቅርፅ አሰራር ጠቀሜታን አብራሩ።
2. ተማሪዎች ከአማረኛ ፊደላት መካከል ደስ የሚላችሁን በመምረጥ በጭቃ ቅርፅ ሰርታችሁ ወደ መማሪያ ክፍላችሁ አምጡ።
3. ያመጣችሁን የአማረኛ ፊደል የጭቃ ቅርፅ ከመምህራችሁ ጋር በመሆን በክፍል ውስጥ የጀሶ ካስቲንግ የአሰራር ቅደም ተከተልን በመጠቀም የጭቃ ቅርጹን ወደ ጀሶ ካስት በማድረግ ለጓደኞቻችሁ አሳዩ።
4. የሰራችሁትን የጀሶ ሞልድ ቫዝሊን ወይም ፈሳሽ ሳሙና በመቀባት እና መልሳችሁ በሞልዱ ላይ ጀሶ በማፍሰስ በጭቃ የሰራችሁትን የአማረኛ ፊደል ቅርፅ ወደ ጀሶ ቀይራችሁ ለመምህራችሁ እና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ።
5. በመጨረሻም ስለሰራችሁት የጀሶ የአማረኛ ፊደል ቅርፅ አሰራር ሁኔታ ለጓደኞቻችሁ ዘገባ አቅርቡ።

2.6.2 በሸክላ አፈር ቅርፅ መስራት

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. ተማሪዎች በአካባቢያችሁ ከሸክላ አፈር የተሰሩ ቁሳቁሶችን ተመልክታችሁ ታውቃላችሁ? እስኪ የምታስታውሱትን ለጓደኞቻችሁ ዘርዝሩላቸው።

ተማሪዎች በአካባቢያችን ከሸክላ አፈር የተሰሩ በርካታ የመገልገያ ቁሳቁሶችን እናገኛለን። የሸክላ አፈር ከሌላው የአፈር አይነት በተለየ ስለሚቦካ እና በነፋስ ቶሎ ስለማይሰነጣጠቅ ቅርፅ ለመስራት የተመቸ ነው። በቤታችን ውስጥ የምናገኛቸው ጀበና፣ ድስት፣ እንስራ፣ ጋን፣ እና ምጣድ የመሳሰሉት ቁሶች በቀላሉ ከሸክላ አፈር የተሰሩ ሲሆን ረጅም እድሜ እንዲቆዩ እና ደረቅ እንዲሆኑ በእሳት ይቃጠላሉ። የሸክላ አፈር ከጥንት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የሰው ልጅ ጠቃሚ የሆኑ የመገልገያ ቁሳቁሶችን ለመስራት የምንጠቀምበት አስፈላጊ የአፈር አይነት ነው።

ተግባር 2.12

1. ተማሪዎች በቡድን ሆናችሁ በአካባቢያችሁ ካሉ የሸክላ ስራዎችን ከሚሰሩ ጠቢባን ጋር በመሄድ ወይም የሚያውቁ ሰዎችን በመጠየቅ ለሸክላ ቅርፅ አሰራር አስፈላጊ የሆኑ መሳሪያዎችን እና የአሰራር ቅደም ተከተል ዘገባ አዘጋጅታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ እና ለመምህራችሁ ገለጻ አድርጉ።
2. በአካባቢያችሁ የሸክላ አፈር የሚገኝ ከሆነ የሸክላ አፈር በመጠቀም ከቤት ውስጥ ቁሳቁሶች መካከል ደስ የሚላችሁን ቅርፅ በመስራት ለጓደኞቻችሁ እና ለመምህራችሁ አሳዩ።

2.6.3 ወረቀትን በማቡካት ቅርፅ መስራት (ፔፐር ማሼ)

ወረቀትን በማቡካት ቅርፅ መስራት (ፔፐር ማሼ) ማለት የተለያዩ ወረቀቶችን በመቆራረጥ እና በማቡካት ልዩ ልዩ ቅርጾችን የመስራት ዘዴ ነው። ይህም በአካባቢያችን ያሉ የወዳደቁ ወረቀቶችን ቆራርጦ በውሃ በማራስ እና በመዘፍዘፍ ወረቀቱን እንደ ጭቃ በመጠቀም ቅርፅ መስራት ማለት ነው። አካባቢያችንን ከሚያቆሽሹ ነገሮች መካከል አንዱ አላግባብ የሚወዳድቁ ወረቀቶች ናቸው። እነዚህን ወረቀቶች መልሶ በመጠቀም እና የቅርፅ ስራዎችን በማዘጋጀት የአካባቢያችንን ንጽህና መጠበቅ እና የፈጠራ ስራችንን ማሳደግ እንችላለን።

ፔፐር ማሼ በሁለት አይነት የአሰራር ዘዴዎች መስራት ይቻላል። ወረቀቶቹን አድቅቆ በማቡካት እና እንደ ጭቃ ሞዴሊግ ልዩ ልዩ ቁሶችን መስራት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ወረቀቶችን በማጣበቂያ እያራሱ በመለጠፍ ቅርፅ የመስራት ዘዴ ነው። የፔፐር ማሼ ስራ ተሰርቶ ካለቀ በኋላ ስራውን የበለጠ ለማሳመር በቀለም ማስጌጥ ይቻላል። ይህም ስራውን የበለጠ የሚያምር ያደርገዋል።

አስፈላጊ መሳሪያዎችና የአሰራር ቅደም ተከተል

አስፈላጊ መሳሪያዎች

- ቁርጥራጭ ወረቀቶች፣ ውሃ፣ እና ባልዲ
- ስኳር ያለው የስንዴ ሙቅ በስሉ የቀዘቀዘ

የአሰራር ቅደም ተከተል

- የተቆራረጠውን ወረቀት ለ24 ሰዓት ያህል ውሃ ውስጥ ዘፍዝፎ ማቆየት፤
- በውሃ የራሰውን ወረቀት ደጋግሞ ማሸት እና እንዲቦካ ማድረግ፤
- ከስንዴ ወይ ከጤፍ ዱቄት ስኳር በመጨመር ሙቅ ማዘጋጀት፤
- የቦካውን ወረቀት ከሙቁ ጋር በማቀላቀል ማሸት፤
- በመጨረሻም እንዲሰራ የተፈለገው ነገር ላይ ወስዶ መለጠፍ ወይም ወረቀቱን እያያያዙ እንደጭቃ በመጠቀም ተፈላጊውን ቅርፅ መስራት።



ሥዕል 29 ወረቀትን በማቡካት እና ከሙቅ ጋር በመደባለቅ የተሰራ ፔፐር ማሼ ስራ





ሥዕል 30 ወረቀትን በመለጠፍ የተሰራ ፔፐር ማሼ

ተግባር 2.13

1. ተማሪዎች በቡድን በመሆን በትምህርት ቤታችሁ ግቢ ውስጥ የወዳደቁ ቁርጥራጭ ወረቀቶችን ሰብስባችሁ ከላይ በተቀመጠው የፔፐር ማሼ አሰራር መሰረት የፕላስቲክ ባልዲን ቅርፅ በማውጣት በየክፍሉ የሚቀመጥ የቆሻሻ ቅርጫት ፔፐር ማሼ ሰርታችሁ ለመምህራችሁ አስረክቡ።

2. የፔፐር ማሼ የአሰራር ዓይነቶችን በመዘርዘር ስለአሰራራቸው ማብራሪያ ስጡ።

የምዕራፉ ማጠቃለያ

ሙዚቃ እንደ ማንኛውም ቋንቋ ሊፃፍ እና ሊነበብ የሚችል የጥበብ እና ሳይንስ ትምህርት መስክ ነው። ሙዚቃን መፃፍ እንድንችል የሚያደርጉ ድምፅን የሚወክሉ ኖታ (የሙዚቃ ምልክት) ያሉት እና ድምፆችን በተወከሉት የኖታ ምልክት መሰረት ማንበብ የሚያስችሉ እንደ የሙዚቃ መፃፊያ ሰሌዳ (ስታፍ)፣ ቁልፎች (ክሌፍ) ያሉት ሲሆን የሙዚቃዎችን ስልተ ምቶችን መወሰን የሚያስችሉ የጊዜ አመልካች ምልክቶችን እና የተለያዩ የሙዚቃውን ውበት እና ጥራት የሚጨምሩ ምልክቶች አሉት። በሙዚቃ ንባብ (ሶልፌጆ) ትግበራ ወቅት የማንበብ እና የመፃፍ እንዲሁም በጆሮ የሚሰሙ የዜማ ድምፆችን እና ዝምታዎችን ማዳመጥ እና መፃፍ የሚያካትት ነው።

በኢትዮጵያ የሚገኙ ውዝዋዜዎች በተለያዩ የአጨዋወት ብልሃቶችን፣ አካባቢያዊ ምልክቶችን እና ቁሳቁሶችን የሚጠቀሙ ሲሆን በአካባቢው ባህላዊ እውቀቶች ላይ የተመሰረቱ ናቸው። በመሆኑም በየአካባቢው የተለያዩ ብልሃትን በመጠቀም የሚተገበሩ ሲሆን ለምሳሌ የጎንደር፣ የጎጃም፣ የወሎ እና የሸዋ የውዝዋዜ አጨዋወት ብልሃቶች ይገኛሉ።

የቴያትር ዝግጅት ራሱን የቻለ የልምምድ ሂደቶች አሉት። እነዚህም የመጀመሪያ ንባብ፣ ተቀምጦ የሚደረግ የንባብ ልምምድ እና የመድረክ እንቅስቃሴ ናቸው። በመጀመሪያ የንባብ ወቅት ተዋናዮቹ ከተውኔቱ ጋር የሚተዋወቁበትጊዜ ሲሆን ተቀምጦ የሚደረግ ንባብ ተዋናዮቹ ቁጭ ብለው በማስተዋል የተውኔቱን ፍሬ ሀሳብ ከአዘጋጁ ጋር የሚወያዩበት ነው። የመድረክ እንቅስቃሴ ተዋናዮቹ በአዘጋጁ

በሚሰጣቸው መመሪያ መሰረት ድራማዊ ድርጊቱን ለማሳየት የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ነው።

በሐር ጨርቅ ማተም የጨርቁ ቀዳዳዎች ቀለም ለማሳለፍ የተመቹ ናቸው። የሐር ጨርቅ በሚገባ ከተወጠረ በኋላ እንዲታተም ከተፈለገው ነገር በተቃራኒ ያሉትን የሐር ቀዳዳዎች በመድፈን እና ክፍት በሆነው ደግሞ ቀለም በማሳለፍ ህትመት መስራት ይቻላል። በሻማ ማቅለም (ባቲክ) የጥንቱ ህብረተሰብ ለልብስ ዲዛይን መስሪያ የሚጠቀምበት ዘዴ ሲሆን አሁንም በጥንቱ ዘዴ በምሥራቅ አገሮች እየተሰራበት ይገኛል።

ካስቲንግ ከቅርፅ መስሪያ ስልቶች መካካል አንዱ ሲሆን በዋናነት አንድን በጭቃ ተሰርቶ ያለቀን ቅርፅ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከዋናው ቅርፅ ላይ ሞልድ በማዘጋጀት ከሞልዱ ውስጥ ፈሳሽ ነገሮችን እንደ ሲሚንቶ፣ ጀሶ እና ዋክስ የመሣሰሉትን በመጠቀም በተዘጋጀው ሞልድ ላይ በመሙላት ከዋናው ቅርፅ ላይ ሌላ ተመሳሳይ ይዘት እና መጠን ያለው ቅርፅ የማግኘት ወይም ቅርፅን የማባዛት ጥበብ ነው። የወረቀት ቅርፅ (ፔፐር ማሼን) በሁለት አይነት የአሰራር ዘዴዎች መስራት ይቻላል። አንደኛው ዘዴ የቦካውን ወረቀት በተለያዩ ቁሳቁሶች በውጨኛው አካላቸው ላይ እንደ ጭቃ ቦክቶ የተዘጋጀውን ወረቀት ካስት በማድረግ የሚሰራ ነው። ሁለተኛው መጀመሪያ የነገሩን ቅርፅ በሸቦ እና በእጨት በማውጣት የቦካውን ወረቀት በመለጣጠፍ እንደ ጭቃ ሞዴሊንግ የአሰራር ዘዴ በመጠቀም ተፈላጊውን ምስል መፍጠር ነው።

የምዕራፉ ቼክሊስቶች

ተማሪዎች በዚህ ምዕራፍ የተማራችኋቸውን ዋና ዋና ነጥቦች ማወቃችሁን አረጋግጡ።

ተ.ቁ	ይዘት	አሳክቻለሁ	አላሳካሁም
1	የሙዚቃ ጥበብ ሊፃፍ እና ሊነበብ መቻሉን ተገንዝቢያለሁ።		
2	በኢትዮጵያ ቅኝቶች የተፃፉ ዜማዎችን ማንበብ ችያለሁ።		
3	ምቶችን እያየሁ ማንበብ ችያለሁ።		
4	ሙዚቃን በመፃፍ እና በማንበብ ሂደት እያዩ ማንበብ እና አዳምጦ መፃፍ የሚባሉት ብልሃቶች ለይቻለሁ።		
5	ውዝዋዜዎችን የአጨዋወት ብልሃታቸውን ተጠቅሞ በተግባር መጫወት ችያለሁ።		
6	ቴያትርን መተወን እችላለሁ።		
7	የሐር ጨርቅ ህትመት አሰራርን መረዳት ችያለሁ።		
8	የካስቲንግን ምንነት ማብራራት ችያለሁ።		
9	የካስቲንግ ቅርፅ የአሰራር ቅደም ተከተሎችን በመለየት መስራት ችያለሁ።		
10	የፔፐር ማሼ አሰራርና መሳሪያዎችን መለየት ችያለሁ።		
11	የሻማ ማቅለም የአሰራር ቅደም ተከተልን በመለየት መስራት ችያለሁ።		


የማጠቃለያ መልመጃዎች


ትዕዛዝ አንድ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ስጡ።

1. ሙዚቃን መፃፍ እና ማንበብ ይቻላል? እንዴት? አብራሩት።
2. የዕይታ ንባብ እና አዳምጦ መፃፍ ማለት ምን ማለት ነው? አስረዱ።
3. በአካባቢያችሁ ያለ ውዝዋዜ ምረጡ እና ቅደምተከተሉን ጠብቃችሁ ሰርታችሁ አሳዩ።
4. ቴያትርን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል አጭር ታሪክ ፈልጋችሁ ሀሳቡን በቃለ ተውኔት ፃፉ።
5. የሀር ጨርቅ ህትመት አሰራር ከወረቀት ስቴንስል ህትመት በምን ይለያል?
6. በሻማ ማቅለም የአሰራር ቅደም ተከተሎችን አብራርታችሁ ጻፉ።
7. የፔፐር ማሼ ስራን ለመስራት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ዘርዝሩ።
8. የካስቲንግ ቅርፅ አሰራር ዘዴን ግለፁ።
9. የካስቲንግ ለመስራት የሚያስፈልጉን ቁሳቁሶችን ዘርዝሩ።


ትዕዛዝ ሁለት የተግባር ልምምድ መልመጃ።


1. በድምጻችሁ ዜማውን አሰሙ






2. ምቱን በእጃችሁ በማጨብጨብ በተግባር ተጫውታችሁ አሳዩ







ምዕራፍ 3

ባህልና ታሪክ

የምዕራፉ ዓላማዎች፦

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፦

- የባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን ባህላዊ እና ታሪካዊ አመጣጥን ታውቃላችሁ።
- የባህላዊ ውዝዋዜ ባህላዊ እና ታሪካዊ አመጣጥን ትረዳላችሁ።
- የባህላዊ ሙዚቃ ባህላዊ እና ታሪካዊ አመጣጥን ታዉቃላችሁ።
- የኢትዮጵያ ጥንታዊ የሀውልት ስራዎችን ታውቃላችሁ።
- የኢትዮጵያ ጥንታዊ የዕደ -ጥበብ ስራ ጥቅሞችን ትገነዘባላችሁ።
- ሀገር በቀል እውቀቶችን በቴያትርና በፊልም መግለፅ ትችላላችሁ።

መግቢያ

ተማሪዎች ይህ ምዕራፍ የክውን እና የዕይታዊ ጥበባትን የባህል እና ታሪካዊ ዳራቸውን የምታውቁበት ክፍል ነው። ትኩረት የሚደረግባቸው የትምህርት ይዘቶች የባህላዊ ሙዚቃ፣ የሙዚቃ መሳሪያዎች እና ውዝዋዜዎች ባህላዊ እና ታሪካዊ ዳራቸው ላይ ነዉ። በተጨማሪም የኢትዮጵያ ጥንታዊ ሀውልቶች፣ የ ኢትዮጵያ ጥንታዊ የዕደ- ጥበብ ስራ ውጤቶች፣ አካባቢያዊ ታሪኮች ለቴያትር እና ለፊልም ስራዎች ያላቸውን አስተዋፅኦ የምትገነዘቡበት ምዕራፍ ነው።

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. ባህላዊ ሙዚቃዎች ለማህበረሰቡ ጥቅም መስጠት የጀመሩበት ጊዜ ከመቼ ጀምሮ ይመስላችኋል?
2. የባህላዊ ሙዚቃ መሳሪያዎችን ማህበረሰቡ አዘጋጅቶ መጠቀም የጀመረው ከመቼ ጊዜ ጀምሮ እንደሆነ ተናገሩ?
3. ባህላዊ ሙዚቃዎች እና የሙዚቃ መሳሪያዎች ከማህበረሰቡ ጋር ምን ዝምድና አላቸው?
4. የምታውቁትን የኢትዮጵያ ጥንታዊ የዕደ-ጥበብ ስራዎችን ዘርዝሩ።
5. የምታውቁትን የኢትዮጵያ ጥንታዊ ሀውልቶች ስም ዘርዝሩ።

3.1 የባህላዊ ሙዚቃ፣ የሙዚቃ መሳሪያዎች እና የውዝዋዜ ባህላዊ ምልከታ

3.1.1 የባህላዊ ሙዚቃ ባህላዊ እና ታሪካዊ ምልከታ

ሙዚቃ አንድ ማህበረሰብ እንደ ማህበረሰብ እንዲቆም ከሚያደርጉት ማህበራዊ ተግባራቱ ውስጥ ዋነኛው ክፍል ነው። ባህል የማህበረሰብ አጠቃላይ መገለጫ ሲሆን ሙዚቃም የዚሁ ክፍል ነው። በማህበረሰቡ የሚዘወተሩትን እውቀቶች፣ ጥበብ፣ ኃይማኖትን፣ አስተዳደራዊ ህጎቹ እና ሌሎች ማህበራዊ ልማዶች በዜማ እና በግጥም የመግለፅ ሂደት የሚያሳየው ሙዚቃ ነው።

ፎክሎር ፎክ እና ሎር ከሚሉ ሁለት ቃላቶች የተመሰረተ ሲሆን ህዝብ እና እውቀት የሚሉ ትርጉሞችን የሚይዝ ነው። ፎክሎር የሚለው ቃል የሚሸከማቸው ባህላዊ ጥበባት የሚባሉት የማህበረሰቡ ቃላዊ፣ ቁሳዊ፣ ክውን ጥበባት እና ማህበራዊ ልማድ ናቸው።

ሙዚቃ የማህበረሰብን እውቀት፣ ልማድ፣ እምነት፣ ፖለቲካ ወዘተ በክዋኔ የሚገልፅ ማህበራዊ ጥበብ በመሆኑ በራሱ የባህሉ ዋና አካል ተደርጎ ይወሰዳል። በመሆኑም ዜማዎቹ የሚሰሩበት እውቀት እና የመተግበር ክሂሎቶች በማህበረሰቡ አባላቶች ሲሆን ባለቤትነታቸውም ራሱ ማህበረሰቡ ይሆናል።

ሙዚቃ ሰው ከተፈጠረበት ዘመን ጀምሮ የሚከወን ተግባር እንደሆነ ይታመናል። ለዚህ ማረጋገጫ ሆኖ የሚቀርበውም የሰው ልጅ ሲወለድ በአካባቢው ካሉ ነገሮች ጋር ሊግባባ የሚችለው ለቅሶ በሚመስል ድምፃዊ መዋቅር እንደሆነ ይታወቃል። በመሆኑም የሰው ልጅ ከቋንቋ በፊት ሙዚቃን እንደ መግባቢያ ይጠቀምበት እንደነበረ የሚያሳይ ነው።

በጥንቱ ዘመን የነበሩ ሰዎች ሙዚቃን ይጠቀሙበት እንደነበር የሚያሳዮ የዋሻ ላይ ስዕሎች በፈረንሳይ እና ሌሎች ጥንታዊ ሀገሮች ይገኛሉ። በተመሳሳይ በኢትዮጵያም በአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ የተነሳው ኢትዮጵያዊው የዜማ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ስራዎች የሙዚቃን ቀደምት ታሪክ ማረጋገጫዎች ናቸው።

በኢትዮጵያ በተለያዩ ክፍለ ሀገራት ሙዚቃ በዘፈን፣ በፉከራ፣ በሽለላ እና በቀረርቶ ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ የሚቀርብ ሲሆን በአሁናዊ (Contemporary) አቀራረቡ ደግሞ ከዘመናዊ ሙዚቃ መሳሪያዎች ጋር ተዋደው እና ተዋህደው ለንግድ በሚሰሩ ሙዚቀኞች (commercial Artists) እና ዘፋኞች በተለያየ መንገድ እሴት ተጨምሮባቸው ተከውነው እና ተቀርፀው ለማህበረሰቡ ይደርሳሉ።

ባህላዊ ሙዚቃን ማህበረሰቡ ከጥንት ዘመን ጀምሮ በተለያዩ ማህበራዊ ክዋኔዎች ሃሳቡን፣ ስሜቱን፣ ደስታውን ብሶቱን፣ የሀገር ፍቅር ስሜቱን፣ ሀዘኑን ለመግለፅ እንዲሁም ማህበራዊ ግንኙነቱን ለማጠናከር በግጥም እና በዜማ በከፍተኛ ደረጃ እየተጠቀመበት የመጣ የሙዚቃ አይነት ነው። ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን ማህበረሰቡ ሲጠቀምባቸዉ የቆዩ የባህላዊ ሙዚቃ ግጥሞች እንመልከት፦

የሽለላ ግጥም

ወንድ ልጅ ተወልዶ ካልተባለ አጅሬ
ስደዱት ተራራ ሳር ይብላ እንደበሬ።
ተው በሉት ያንን ሰው መካር የለውም ወይ
ምላጩን ከሳቡት እርሳስ አይደለም ወይ።
ተው በሉት ተው በሉት ያነን ሰው
ነገር እንደቁና የሚያመላልሰው።
አገራችን ታማ ተኝታ በአልጋ ላይ
ወዴት እንሔዳለን ሞት ሸረቷን ሳናይ።

በፉከራ ጊዜ ከምንጠቀማቸው ግጥሞች

መሄድ ያማረው መንገዝ ያማረው
የሀገሩ ጉዳይ እያሳሰበው።
ማረስ ነው እንጅ እጅ እስኪቆስል
ምንድን ነው ስርቆት ውሻ ይመስል።
እኔስ አርሳለው አልመረርም
ችጋር በወንጭፍ አይባረርም።

በበራይ /በውቂያ/ ጊዜ ከሚዜሙ ግጥሞች

እባክህ እንጀራ ለሁለት ትረፈው
ወንድሙን ወንድሙ እንዳይጠየፈው።
አንድ በሬ ነበረኝ የማልበው የማርሰው
ዕዳ መጣ ቢሉት ታሞ ተኛ እንደሰው።

በሙሾ ጊዜ ከምንጠቀምባቸው ግጥሞች

ክፉ አውሬ በሽታ ገብቶ ሀገራችን
ጥላት አለበሰው ድፍን ወገናችን።
የላይኛው መንደር ተራማጅ ነው አሉ
የመጣልን የለም ከሰደድነው ሁሉ።

ተግባር 3.1

1. ከላይ የቀረቡትን ማህበረሰቡ ሲጠቀምባቸው የመጡ ሀገራዊ ግጥሞችን በዜማ እና በእንቅስቃሴ በተግባር በመስራት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ።
2. በአካባቢያችሁ አብዛኛውን ጊዜ ስሜታችሁን፣ ደስታችሁን፣ ሀዘናችሁን እና የሀገር ፍቅር ስሜትን ለማንፀባርቅ የምትጠቀሙባቸውን ግጥሞች ፅፋችሁ በመምጣት በሽለላ፣ በቀራርቶ፣ በሙሾ፣ በዘፈን በተግባር በክፍል ውስጥ ከውናችሁ አሳዩ።

3.1.2 የመዚቃ መሳሪያዎች ባህላዊ እና ታሪካዊ ምልከታ

የሰው ልጅ ራሱን በዙሪያው ካሉት ተፈጥሯዊ እና ማህበራዊ ሁኔታዎች ጋር የሚስማሙትን እና በሕይወት ሲቆይ ስኬታማ የሚያደርጉትን ቁሳዊ ባህሎች ይሰራል።

እነዚህ ቁሳዊ ባህሎች እራሱን ከአደጋ ለመከላከል፣ አእምሯዊ ደህንነቱን ለመጠበቅ፣ ኢኮኖሚያዊ እደገቱን ለማረጋገጥ እና ሥነ-ልቦናዊ ጥንካሬውን ለማጎልበት ቁሳቁሶችን (ጎራዴ፣ ማጭድ፣ ማረሻ፣ የቤት ውስጥ እቃዎች፣ የአደን መሳሪያዎች፣ የመዚቃ መሳሪያዎች ወዘተ) ያዘጋጃል።

ቁሳዊ ባህሎች ከማህበረሰቡ ባህል፣ እውቀት፣ ልምድ፣ ችሎታ፣ እምነት እና ሥነ-ልቦናዊ ስሪት ጋር በእጅጉ የተቆራኙ ናቸው። ቁሳዊ ባህሎቹ ከማህበረሰቡ እውቀት፣ ልምድ እና ችሎታ አኳያ የሚዘጋጁ በመሆናቸው ከአካባቢ አካባቢ ይለያያሉ።

ባህላዊ የመዚቃ መሳሪያዎች ማህበረሰቡ ከጥንት ጊዜ ጀምሮ ለተለያዩ ክብረ-በዓላት፣ ለሰርግ ስርዓት፣ የሀገር ስሜትን ለመግለጽ፣ ማህበረሰብን ለማነቃቃት፣ ለገቢ ምንጭነት እና ራስን ለማዝናናት ሲጠቀምባቸው የመጡ የባህል ዋነኛ መገለጫዎች ናቸው።

ለምሳሌ የሚከተሉት የመዚቃ መሳሪያዎች ከባህል ጋር ያላቸውን ዝምድና ተመልከቱ





ሥዕል 31 የሙዚቃ መሳሪያዎች ባህላዊ ምልከታ

ተግባር 3.2

1. ከላይ በሥዕል 30 ከተመለከታችኋቸው ምስሎች ምን እንደተረዳችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ማብራሪያ ስጡ።
2. በሀገራችን ውስጥ ከሚገኙ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች መካካል የምታውቋቸውን በመዘርዘር ከአካባቢው ባህል ጋር ያላቸውን ግንኙነት እና በምን ሁነቶች ላይ እንደሚጠቀሙባቸው ማብራሪያ ስጡ።
3. ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ከአንድ አካባቢ ባህል ጋር ለምን ትስስር እንደሚኖራቸው ምክንያታዊ በመሆን ማብራሪያ ስጡ።

የሙዚቃ መሳሪያዎች የሰው ልጅ በሕይወት ልምምዱ ውስጥ ጥራታቸውን እና አጨዋወታቸውን እያሳደጋቸው የመጡ ናቸው። በቅድሚያ በሰው ልጅ ዘንድ ጥቅም ላይ የዋሉት የምት እና የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያዎች እንደሆኑ ጥንታዊ የሙዚቃ ታሪኮች ያስረዳሉ።

የሰው ልጅ የራሱን እጅ እና እግሮች ከመጠቀም ተነስቶ ቆዳዎችን በተቦረቦሩ እንጨቶች ላይ በመወጠር ድምፅ እንዲፈጥሩ በማድረግ፣ አፉን ተጠቅሞ ሩጫትን እንደ ሙዚቃ መሳሪያ ከመጠቀም ወደ ውስጣቸው የተቦረቦረ ሸንበቆዎች በማሳደግ የሙዚቃ መሳሪያዎችን አሁን ለደረሱበት እድገት አብቅቷቸዋል።

ጥንታዊነት ያላቸው የሙዚቃ መሳሪያዎች በእንስሳት ቅርፅ ወይም ደግሞ አካባቢው ውስጥ በሚገኙ ቁሳቁሶች (ቀንድ፣ አጥንት፣ እንጨት፣ ቅጠል ወዘተ) ይዘጋጁ ነበር። ለምሳሌ



ሥዕል32 ከአጥንት የተሰራ የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያ



ሥዕል 33 በእንስሳት ቅርፅ የተሰራ የሙዚቃ መሳሪያ

በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች የሚኖሩ ብሔር ብሔረሰቦች የራሳቸው የሆኑ ጥንታዊነት ያላቸው እና ከማህበረሰቡ ስነ-ልቦናዊ ውቅር እና ባህል ጋር የተሳሰሩ ብዙ ዘመናትን ያስቆጠሩ ሙዚቃ መሳሪያዎች ይገኛሉ። እንደ ከበሮ፣ በገና እና መሰንቆ የመሳሰሉት ሀይማኖታዊ ዳራ ያላቸው በመሆኑ የኢትዮጵያ የሙዚቃ መሳሪያዎችን ጥንታዊ መሆናቸውን የሚያመላክቱ ናቸው።

ከዚህ በላይ የተሰጡት ማብራሪያዎች በሀገራችን ኢትዮጵያ የሙዚቃ መሳሪያዎች ጥንታዊነት ያለቸው መሆኑን መገንዘብ ያስችላሉ።

3.1.3 የባህላዊ ውዝዋዜ ባህላዊ እና ታሪካዊ ምልከታ

ባህላዊ ውዝዋዜ የዕሁፍ ቋንቋዎች ከመፈጠራቸው ከክርስቶስ ልደት በፊት 3300 ዓ.ዓ ቃላትን እና አፈፃፀማቸውን እንዲሁም ታሪኮችን ከትውልድ ትውልድ ማስተላለፊያ ዘዴ ነበር።

በተለያዩ ክፍለ ዓለማት የሚኖሩ ማህበረሰቦች ለፈውስ እና ስሜቶችን ለመግለፅ (አሁን እየተደረገ እንዳለው) ይጠቀሙበትም ነበር።

በሀገራችን በተለያዩ አካባቢዎች በርካታ የባህላዊ ውዝዋዜ አይነቶች ይገኛሉ። እነዚህ የውዝዋዜ አይነቶች የአካባቢውን ወግ፣ ልማድ፣ የማህበረሰቡን መንፈሳዊ እና ቁሳዊ ባህሉች እንዲሁም ማህበራዊ አውዶችን መሰረት አድርገው ይተገበራሉ።

ባህላዊ ውዝዋዜዎች በአጨዋወት ብልሀታቸው ተወራራሽ ቢሆኑም በሚኖራቸው አውዳዊ ልዩነት እና ውዝዋዜዎቹ ከሚፈጥሩት ደስታ፣ ሃዘን እና ልዩልዩ ስሜቶች አኳያ መለየት እና መመደብ ይቻላል።

ባህላዊ ውዝዋዜዎች ከጥንት ዘመን ጀምሮ በተለያዩ ማህበራዊ ክዋኔዎች ማለትም በሰርግ፣ በባዓላት፣ በአደን፣ በተለያዩ ስራዎች (በአጨዳ፣ በቤት ስራ) በእነዚህ እና በመሳሰሉት ሁነቶች ደስታውን እና ማህበራዊ ግንኙነቱን እያጠነከረባቸው የመጡ የውዝዋዜ ምድብ ናቸው።

ባህላዊ ውዝዋዜዎች እንደየ አካባቢው ባህል በአለባበስ፣ በውዝዋዜ ስልት (በጥንድ በመሆን፣ በህብረት በመሆን፣ በተናጠል)፣ በሚጠቀሙት ዜማ፣ በሚጠቀሙት ባህላዊ ቁሳቁሶች፣ በሙዚቃ መሳሪያ፣ በፆታ እና በሚከወንበት ጊዜ ልዩነት አለው። ይህ የሚያመለክተው ባህላዊ ውዝዋዜ ከአንድ አካባቢ ባህል ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት እንዳለው ነው። በአጠቃላይ ባህላዊ ውዝዋዜ የባህል ዋነኛ መገለጫ ነው።

ተግባር 3.3

1. በአካባቢያችሁ በተለያዩ ኃይማኖታዊ በዓላት እና በሰርግ የምትጠቀሙባቸው ባህላዊ ውዝዋዜዎች አንድ አይነት ናቸው ? ልዩነት ካላቸው ለምን ልዩነት እንዳላቸው በምሳሌ በማስደገፍ ማብራሪያ ስጡባቸው።
2. በተለያዩ ሁነቶች ማህበረሰቡ ሲከውናቸው የምትመለከቷቸው ባህላዊ ውዝዋዜዎች በትክክል የአካባቢውን ባህል የሚያንጸባርቁ(የሚገልፁ) ናቸው ብላችሁ ታስባላችሁ? መልሳችሁ አያንጸባርቁም ከሆነ ምክንያቱ ምን እንደሆነ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩ።
3. ከዚህ በታች የተቀመጠውን የባህላዊ ዉዝዋዜ ምስል በማየት ምን እንደተረዳችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።



ሥዕል 34 በክብረ በዓላት ጊዜ የሚከወን ውዝዋዜን የሚያሳይ

ተግባር 3..4

1. ባህላዊ ሙዚቃን ማህበረሰቡ በጥንት ዘመን እንዴት ሲጠቀምበት እንደነበረ በምሳሌ በማስደገፍ ማብራሪያ ስጡ።
2. የአንድ አካባቢ ባህላዊ ውዝዋዜ ከሌሎች አካባቢ ባህላዊ ውዝዋዜዎች በምን በምን ሊለያይ እንደሚችል በምሳሌ አስደግፋችሁ ማብራሪያ ስጡ።
3. ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ከባህላዊ ውዝዋዜ ጋር ምን ግንኙነት ሊኖራቸው እንደሚችል አብራሩ።
4. በአንዱ ማህበራዊ ሁነት የምትጠቀሙት ባህላዊ ውዝዋዜ በሌላ ማህበራዊ ሁነት ከምትጠቀሙት ጋር ያለውን ልዩነት በማስረጃ በማስደገፍ ማብራሪያ ስጡ።

3.2 የኢትዮጵያ ጥንታዊ ሀውልቶች እና የዕደ-ጥበብ ስራዎች

3.2.1 የኢትዮጵያ ጥንታዊ የሀውልት ስራዎች

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. በሀገራችን ከሚታወቁ የኢትዮጵያ ጥንታዊ የሀውልት ስራዎች መካከል የምታስታውሱትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

በሀገራችን በኢትዮጵያ እጅግ ጥንታዊ የሆኑ የሀውልት ስራዎች ይገኛሉ። ከአንድ ወጥ ድንጋይ ተቀርጸው ከተሰሩ የሀውልት ስራዎች መካከል በሰሜኑ የአክሱም ሀውልት፣ በደቡብ የሀገራችን ክፍል የጢያ ትክል ድንጋይ እና የኮንሶ ዋካዎች በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው።

በዘመናዊው የሀገራችን ታሪክ ደግሞ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በርካታ ታሪካዊ የመታሰቢያ ሀውልቶች የተሰሩ ሲሆን አብዛኞቹ የሀገራችንን ታሪክ የሚያስታውሱ እና ለትውልድ የሚያስተላልፉ ናቸው። ለገሀር ባቡር ጣቢያ አካባቢ ያለው የይሁዳ አንበሳ ሀውልት፣ የአፄ ሚኒልክ የአደባባይ ሀውልት፣ አራት ኪሎ አደባባይ የአርበኞች መታሰቢያ ሀውልት፣ ስድስት ኪሎ የየካቲት 12 ሰማዕታት መታሰቢያ የአደባባይ ሀውልት፣ የካራማራ ድል መታሰቢያ ሀውልት እና የአቡነ ጴጥሮስ የመታሰቢያ የአደባባይ ሀውልት በቅርቡ ከተሰሩ የሀገራችን ታሪክ መታሰቢያ የሀውልት ስራዎች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው።





ሥዕል 35 የለገሀር የይሁዳ አንበሳ እና የካራ ማራ ድል መታሰቢያ ሀውልቶች



ሥዕል 36 የአርበኞች የመታሰቢያ ሀውልቶች አራት ኪሎ

ከዚህ በላይ የተቀመጡት የሀዉልት ስራዎች በቅርብ ጊዜ የተሰሩ ሲሆን በዚህ ምዕራፍ ግን በዝርዝር የምንማረዉ ስለ ጥንታዊ የኢትዮጵያ የሀዉልት ስራዎች ይሆናል።

ሀ አክሱም ሀውልቶች

የአክሱም ሀዉልቶች በኢትዮጵያ ከተሰሩ ጥንታዊ ሀውልቶች መካከል የሚጠቀሱ ናቸዉ። የአክሱም ሀውልቶች የተለያየ መጠን ያላቸው ሲሆን ከ24 እስከ 33 ሜትር ድረስ ርዝመት አላቸው። ከአንድ ወጥ አለት ተፈልፍለው የተሰሩ ሲሆን ለአክሱም ነገስታት የመታሰቢያ መቃብርነት ታስበው እንደተሰሩ ይነገራል። ሀውልቶቹ አራት መዓዘን ቅርፅ ያላቸው ሲሆን ከታች ሰፋ ብለው ወደ ላይ እየጠበቡ የተደራረበ የቤት ዲዛይን የያዙ ናቸው። የውሸት በርና መስኮት ቅርፅ የተሰራላቸው ሲሆን ከአናታቸው ላይ የግማሽ ክብ ቅርፅ አላቸው።

የአክሱም ሀውልቶች እጅግ ግዙፍ ሲሆኑ 33 ሜትር ርዝመት ያለው ሀውልት ተሰባብሮ ወድቆ ይገኛል። ሌላው ደግሞ በፋሽስት ጣልያን ወረራ ወቅት ተሰርቆ ወደ ሮም ከተማ ተወስዶ የነበረ ሲሆን በቅርቡ ወደ ሀገር ቤት ተመልሶ ከነበረበት ቦታ እንዲቆም ተደርጓል። የአክሱም ሀውልት ስራዎች በዘመኑ የነበሩት ነገስታትን የስልጣኔ አሻራ የሚያመላክቱ ሲሆን የሀገራችንንም ታሪክ የሚያስታውሱ ናቸው።



ሥዕል 37 ሃያ አራት ሜትር ርዝማኔ ያለው የአክሱም ሀውልት



ሥዕል 38 ወድቆ የተሰበረው ሰላሳ ሦስት ሜትር ርዝመት ያለው የአክሱም ሀውልት

ለ) የኮንሶ ዋካ ሀዉልቶች

ኮንሶ ዋካዎች በደቡብ የሀገራችን ክፍል ከተሰሩ የኢትዮጵያ ጥንታዊ የእንጨትና የድንጋይ ሀውልት ስራዎች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው። የኮንሶ ዋካዎች በዋናነት በህይወት ዘመኑ ጀግና ለነበረ ሟች መታሰቢያ የሚቆሙ የእንጨትና የድንጋይ ላይ የሀውልት ስራዎች ናቸው። በኮንሶ ባህል መሰረት በጦር ሜዳ ብዙ የማረከና ጫካ ሄዶ አንበሳና ነብር የገደለ ጀግና ሲሞት ሚስቶቹ እና የአካባቢው ነዋሪዎች የእንጨት የመታሰቢያ ሀውልት የሚያሰሩለት ሲሆን ሀውልቱን በመንደሩ መግቢያ መንገዶች ዳር ላይ በማቆም ጀግናቸውን ይዘክሩበታል። ይህ ሀውልት በዋናነት በመንደሩ ባለሙያዎች የሚሰራ ሲሆን ከፍተኛ ሀብት ለባለሙያዎቹ በመስጠት ጀግንነቱን በሚያስታውስ መልኩ የሚች ቤተሰቦች ያሰሩለታል።



ሥዕል 39 ኮንሶ ዋካዎች

ሐ) የጢያ ትክል ድንጋይ ሀውልቶች

የጢያ ትክል ድንጋዮች ከኢትዮጵያ ጥንታዊ ሀውልት ስራዎች በርካታ ቁጥር ያላቸው ተፈጥሯዊ የሚመስሉ ድንጋዮች ሲሆኑ የተቀረጹ ምስሎችን የያዙ ናቸው። የጢያ ትክል ድንጋዮች በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በጉራጌ ዞን በተለይም ከአዲስ አበባ ወደ ቡታጂራ በሚወስደው መንገድ 88 ኪሎ ሜትር ርቃ ከምትገኘው ሶዶ ወረዳ በጥያ ከተማ ይገኛሉ። በቁጥር 44 የሚደርሱ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 32 ያህሉ ልዩ ልዩ የቅርፅ ምስሎች ያሉባቸው ናቸው። ሁሉም ድንጋዮች የተለያየ ርዝመት፣ ስፋትና ውፍረት አላቸው። ይሁንና በሌሎቹ ሥፍራዎች ማለትም በሀገር ውስጥ በስልጤ፤ በዉጭ ሀገር በግብፅ፣ በመካከለኛው ምሥራቅ፣ በሩቅ ምሥራቅ፣ በአውሮፓና በላቲን አሜሪካ እንደምናያቸው የመቃብር ድንጋዮች አንድም አራት ማዕዘን ወይም ድቡልቡል አይደሉም። በአብዛኛው ከታች ሰፋ ብለው ወደ ላይ እየሾጠጡ የሚሄዱ ናቸው። የአንዳንዶቹ ትክል ድንጋዮች ቁመትም ከ1-5 ሜትር ሊረዝም እንደሚችል የአርኪዮሎጂ አጥኚዎች ይጠቁማሉ። በድንጋዮቹ ላይ የተቀረጹት ምስሎችም የጎራዴ ወይም የሰይፍ ወይም የጩቤ፣ የጦር፣ የትራስ እንጨት፣ ክብ ዳቦ ወይም ፀሐይ መሰል ቅርጾች፣ የግማሽ ጨረቃ ምስሎች እና እጆቹን ወደላይ የዘረጋ ሰው ክንዶች ናቸው።



ሥዕል 40 የጢያ ትክል ድንጋዮች (በከፊል)

ተግባር 3.5

1. የኢትዮጵያ ጥንታዊ ሀውልቶች ከዘመናዊ ሀውልቶች በምን በምን ይለያሉ?
2. በሀገራችን የምታውቋቸውን የኢትዮጵያ ጥንታዊ ሀውልቶች በመዘርዘር የሚሰጡትን ጠቀሜታ ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ።
3. የኢትዮጵያ ጥንታዊ ሀውልቶች የሀገራችን ባህል ከመግለጽ አንጻር ያላቸውን ጠቀሜታ ዘርዝሩ።

3.2.2 የኢትዮጵያ ጥንታዊ የዕደ-ጥበብ ስራዎች

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. በአካባቢያችሁ የምታውቋቸውን የኢትዮጵያ ጥንታዊ የዕደ-ጥበብ ስራዎችን በመዘርዘር ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

የኢትዮጵያ ጥንታዊ የዕደ-ጥበብ ስራዎች ፈጠራቸው ሙሉ በሙሉ ሀገር በቀል የሆኑ ቁሳቁሶችን ይጠቀማሉ። የኢትዮጵያ ጥንታዊ የእደ ጥበብ ስራዎች ብዙውን ጊዜ መደበኛ በሆነ እና መደበኛ ባልሆኑ መንገዶች ይሰሩ ነበር። ስራዎቹም ችሎታን እና ትግስትን የሚጠይቁ እና በማንኛውም ክህሎት ባለው ሰው የሚሰሩ ናቸው።

የኢትዮጵያ ጥንታዊ የዕደ-ጥበብ ስራዎች ተግባራት ከጥንታዊ አክሱማዉያን ዘመን አንስቶ የተለያዩ ሳንቲሞችን፣ የእጅ እና ደረት ጌጣጌጦችን፣ የበር መቀርቀሪያዎችን፣ የሸክላ ስራዎችን፣ የሽመና ስራዎችን እና ሌሎችንም ስራዎች እየሰሩ መምጣታቸው ይታወቃል። ምንም እንኳን በውጭ ወራሪዎች ምክንያት ሙያው እየተዳከመ ቢመጣም በሀገራችን እስካሁን ድረስ በመስራት እየተገለገልንባቸው እንገኛለን።


በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ጥንታዊ የዕደ-ጥበብ ስራዎች የምንላቸዉ የሰው ልጅ በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴው ውስጥ ሊገለገልባቸው የሚችልባቸው ቁሳቁሶች ከመፍጠር እና ከመስራት ጋር ተያይዞ እያደገ የመጣ ጥበብ ነው። ሙያው ከሌሎች የሥነ-ጥበብ ስራዎች የሚለየው ለመገልገያነት ታስቦ በእጅ የሚሰራ እና ማንኛውም ክህሎት ያለው ሰው ሊሰራው ስለሚችል ነው።

የኢትዮጵያ ጥንታዊ የዕደ-ጥበብ ስራዎች የምንላቸው የተለያዩ ጥንታዊ የሸክላ ስራዎች፣ ጥንታዊ የሽመና ስራዎች፣ ጥንታዊ ሳንቲሞች፣ ጥንታዊ ስፌቶች ወዘተ ስራዎችን የያዙ ናቸው።

ሀ) ሽመና (weaving)

ሽመና ከኢትዮጵያ ጥንታዊ የዕደ-ጥበብ ስራዎች አንዱ ሲሆን በተለያዩ የአሰራር ቴክኒኮች፣ ከጥጥ፣ ከሱፍ፣ ከክር እና ከመሳሰሉት ግብዓቶች ተጠቅመን የምንሰራቸው ናቸው። ለምሳሌ ቀሚስ፣ ሹራብ፣ ባርኖስ፣ ባት ከሁለት፣ የአልጋ ልብስ ፣ የቤተክርስቲያን አልባሳት፣ ካባ፣ አክሊል እና የመሳሰሉት ሲሆኑ እነዚህ የሽመና ውጤቶችም ለተለያዩ ተግባሮች እንጠቀምባቸዋለን። ለምሳሌ፦

ለፍርድ ሸንጎ ሲቀመጡ፣ ለሰርግ፤ ለሀዘን፣ ለተለያዩ በዓላት እና በእለትዕለት ኑሯቸው የሚለበሱት የሽመና የስራ ውጤቶች ናቸው።



ሥዕል 41 የሽመና ስራ



ሥዕል 42 የሽመና ስራ ውጤት

ለ) የሸክላ ስራ (potery)

ሸክላ ስራ በአክሱማዉያን ዘመን የተጀመረ መሆኑ በታሪክ ይነገራል። በመሆኑም የሸክላ ስራ ከጥንታዊ ዘመን የዕደ-ጥበብ የሚመደብ ሲሆን በሚሰሩት ስራዎች ላይም ኃይማኖትን፣ ባህልን፣ የንጉሶች የስራ ውጤት የሚያጸባርቁ ነገሮችን እና ትንንሽ ቅርጾችን ይሰሩባቸው ነበር። ከጥንታዊ ዘመን የሸክላ ስራዎች መካከል የአበባ ማስቀመጫዎች፣ እንስራ፣ ድስት፣ ማሰሮ፣ ጀበና፣ ጋን እና የመሳሰሉት ተጠቃሽ ናቸዉ። በኢትዮጵያዉያን ዘንድ እነዚህ የጥበብ ስራዎች በህብረተሰቡ ዘንድ ዝቅተኛ ስፍራ ይሰጣቸዉ ነበር።

በአጠቃላይ የሸክላ ስራ ዉጤቶች ከጥንት ነገስታት ጀምሮ ለተለያዩ ተግባራት ሲጠቀሙባቸዉ የቆዩ የዕደ-ጥበብ ዉጤቶች ናቸዉ።





ሥዕል 43 ጥንታዊ የሸክላ ስራ

ሐ) ጥንታዊ የድንጋይ መሳሪያዎች

የኢትዮጵያ ጥንታዊ የድንጋይ መሳሪያዎች የምንላቸው የሰው ልጅ ከጥንት ጊዜ ጀምሮ ለአደን፣ ለቤት መስሪያነት፣ ለመገልገያ ቁሳቁሶች፣ ወዘተ ሲጠቀሙባቸዉ የቆዩ የዕደ-ጥበብ ዉጤቶች ናቸዉ። ለምሳሌ፦ ጦር፣ ቢላዋ፣ መሮ፣ የድንጋይ ወፍጮ እና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል።



ሥዕል 44 ጥንታዊ የድንጋይ መሳሪያዎች

መ) ጥንታዊ የአክሱም የመገበያያ ሳንቲሞች

የኢትዮጵያ ጥንታዊ የመገበያያ ሳንቲሞች በአብዛኛው የተሰሩት በነገስታቱ ሲሆን በጋይማኖት እቃዎች ማለትም እንደ መስቀሎች፣ የንጉሱ ከአንገት በላይ ፎቶዎች እና የግዕዝ ፊደላትን በሳንቲሞቹ ላይ ገላጭ ሆነዉ ይቀመጡ ነበር። በጥንት ዘመን በስልጣኔያቸው ቀደምት ከነበሩት መንግስታት መናገሻ መካከል አንዷ የሆነችውና በገናናነቷም ከነዚሁ ጋር የምትመደበዋ አክሱም ለንግድ እንቅስቃሴዋ መሰረት የሆነ በደንብ የተደራጀ የሳንቲም ገንዘብ ነበራት። የአክሱም ጥንታዊ የመገበያያ ሳንቲሞች የሚሰሩት ከወርቅ፣ ከብር እና ከነሀስ እንደተሰሩ ታሪክ ይጠቁማል።

በገንዘቦቹ ላይ በአንደኛው ገፅ የራሳቸውን የነገስታት ምስሎች በገብስ ወይም በስንዴ ዘለላ ተከቦ ሲታይ በሌላው ገፅ ደግሞ የፀሀይ፣ የጨረቃ እና የመስቀል ምስሎች ተስሎባቸው ይገኛል። በአንዳንዶቹም ላይ አጭር ምሳሌአዊ አነጋገር ተፅፎ ይገኝባቸዋል። ከአክሱም ገንዘቦች ጥቂቶቹ በአሁኑ ጊዜ አዲስ አበባ በሚገኘው ብሄራዊ ሙዚየም ለናሙና ቀርበው የሚገኙ ሲሆን አብዛኞቹ ግን በውጭ ሀገር በሚገኙ ሙዚየሞች በተለይም በፓሪስ፣ በለንደን፣ በበርሊን፣ እንዲሁም ገንዘብ በሚያጠራቅሙ ግለሰቦች ዘንድ ይገኛሉ። የአክሱም የወርቅ ገንዘቦች አላዶ በመባል ይታወቃሉ።






ሥዕል 45 ጥንታዊ የአክሱም የመገበያያ ሳንቲሞች

ሠ) ጥንታዊ ጌጣጌጦች

አንድ ማህበረሰብ ከአካባቢው በሚያገኛቸው ግብዓቶች ተጠቅሞ ራሱን እና በቤቱ የሚያረባቸው እንስሳቶቹን ለማስዋብ የሚጠቀምባቸው ሀገር በቀል ባህሎች በሀገረሰባዊ ጌጣጌጥ ውስጥ ይመደባሉ።

ሀገር በቀል ጌጣጌጦች ማህበረሰቡ ከወርቅ፣ ከነሀስ፣ ከብር፣ ከአልማዝ እና ከሌሎችም ማዕድናት፤ ከክር፣ ከከበረ ድንጋይ፣ ከእንጨት እና ከተለያዩ ተፈጥሯዊ እና ሰው ሰራሽ ግብዓቶች የሚያዩትን ቁስ በተለያየ ቅርፅ እና ስልት በማዘጋጀት በእጅ፣ በጆሮ፣ በአንገት፣ በጸጉር፣ በክንፈር፣ በአፍንጫ እና በመሳሰሉት የሰውነት የአካል ክፍሎች ላይ የሚደረጉ የውበት መጨመሪያ ናቸው።






ሥዕል 46 ጥንታዊ የተለያዩ ጌጣጌጦች

ተግባር 3.6

1. የአክሱም ሀውልቶች የተሰሩት ምን ነገሮችን ታሳቢ ተደርጎ ነው?
2. የጥያ ትክል ድንጋይ የሚገኝበትን ቦታ እና ባህላዊ ገጽታዎችን ዘርዝሩ።
3. በጥንታዊ የተሰሩ የዕደ-ጥበብ ዉጤቶችን በመዘርዘር የሚሰጡትን ጠቀሜታ አብራሩ።
4. የኢትዮጵያ ጥንታዊ ሳንቲሞችን በመዘርዘር ከምን እንደተሰሩ አብራሩ።
5. የኢትዮጵያ ጥንታዊ ጌጣጌጦች ከምን ከምን ይሰሩ እንደነበረ እና ስለጠቀሜታቸው ማብራሪያ ስጡ።

3.3 አካባቢያዊ ታሪኮች ለቴያትር እና ለፊልም ያላቸው አስተዋጽዖ

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. አካባቢያዊ ታሪክ ማለት ምን ማለት ነው?
2. አካባቢያዊ ታሪኮች ለቴያትር እና ለፊልም ድርሰት አስተዋጽዖ አላቸው ወይስ የላቸውም በሚል ርዕሰ ጉዳይ በመነሳት ክርክር አድርጉ።
3. የምታውቋቸውን አካባቢያዊ ታሪኮች ተናገሩ።
4. በአካባቢያዊ ታሪክ የተሰሩ ቴያትር አይታችሁ ታውቃላችሁ? መልሳችሁ አዎ ከሆነ ያያችሁትን ቴያትር ስያሜ በመናገር በምን ታሪክ ላይ እንዳጠነጠነ እና ከአካባቢ ታሪክ መነሳቱን በማረጋገጥ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

የቴያትር እና ፊልም ጥበብ ታሪካዊ መሰረታቸው በገሃዱ ዓለም በሚተወኑ ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ላይ በመሆኑ የማህበረሰቡ ታሪካዊ ቅብብሎሽ፣ ባህላዊ ስርዓቶች፣ ቋንቋ እና መሰል ተግባሮች ቴያትር እና ፊልም እንደ አንድ መስክ ተደርጎ እንዲነሳ ያደርጉታል። በመሆኑም የቴያትር እና የፊልም ጥበብ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ በንግግር፣ በእንቅስቃሴ እና በቁሳቁሶች የሚመሰረቱ ጥበባዊ እሴት ተጨምሮባቸው የማህበረሰቡን ንቃተ ህሌና ለማሳደግ በሚረዳ መልኩ መልሰው በጊዜ እና በቦታ ተወስነው እና ተመስለው የሚቀርቡ ክውን ጥበባት ናቸው። የፊልም እና ቴያትር ጥበብ አቀራረቦች የተለያዩ ይሁን እንጅ ክውን ጥበባት ነው።

በአካባቢያችን በተለያዩ ጊዜያት የሚፈጠሩ የተለያዩ አካባቢያዊ ታሪኮች አሉ። ለምሳሌ የሽምግልና ስርዓቶች ብንወስድ በዚህ ታሪክ በመነሳት የቴያትር እና የፊልም ድርሰት ብንደርስ ማህበረሰቡን በግልጽ ማስተማር እና ባህሉን በግልጽ እንዲረዳ ማድረግ ይቻላል።

አንድ ቴያትር እና ፊልም በአካባቢያዊ ታሪኮች የሚሰራ ከሆነ ማህበረሰቡ መልዕክቱን በግልጽ እንዲረዳው እና አካባቢውን እንዲያውቅ ማድረግ ይቻላል።

በአጠቃላይ በሀገራችን በርካታ አካባቢዊ ባህሎች እና ታሪኮች ስላሉን በቴያትር እና በፊልም ድርስት ውስጥ በማካተት ማህበረሰቡን ማስተማር እና ጥበብን የእኔ ነው ብለው እንዲረከቡት ማድረግ ይቻላል። በአካባቢችን ከሚገኙ ባህላዊ ታሪኮቻችን ውስጥ የጥምቀት በዓል አከባበር፣ የቅዳሴ ስርዓት፣ የመውሊድ ስርዓት፣ የሽምግልና ስርዓት፣ ባህላዊ ህክምና ፣ የምርቃት ስርዓት፣ የሰርግ ስርዓት፣የለቅሶ ስርዓት የመሳሰሉት ይገኛሉ። በመሆኑም እነዚህን አካባቢያዊ ታሪኮች ለቴያትር እና ለፊልም ድርሰት እንዲውሉ በማድረግ ሰላምን፣ አንድነትን፣ መረዳዳትን፣ ታሪክን ከትውልድ ወደትውልድ ማስተላለፍ እና ትምህርት ማስጨበጥ ይቻላል።

ተግባር 3.7

1. አንድ ቴያትር ወይም ፊልም በማየት ድክመቱን እና ጥንካሬውን በማስረጃ በመገምገም ለክፍል ጓደኞቻችሁ በዘገባ መልክ አቅርቡ።
2. አካባቢያዊ ታሪክ የምትሏቸውን በመዘርዘር ለምን አካባቢያዊ እንደተባሉ ተናገሩ።
3. የአንድ ቴያትር ወይም ፊልም ድርሰት ከአካባቢያዊ ታሪክ መነሳቱ ለደራሲው እና ለማህበረሰቡ ያለውን ጠቀሜታ በምሳሌ በማስደገፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ማብራሪያ ስጡ።

የምዕራፉ ማጠቃለያ

ሙዚቃ በሰው ልጅ የሚከወን ለሰው ልጅ የሚቀርብ ክውን ጥበባት ነው። በመሆኑም ሙዚቃ የሚያነሳቸው መሰረታዊ ሃሳቦች፣ ማህበራዊ እውቀቶች እና ልማዶችን መንፈስን እንዲገዙ ተደርገው የተቀነባበሩ በሙዚቃ ድምፆች አማካኝነት ነው። ከማህበረሰቡ ልምድ እና ባህል የሚቀዱ ስርዓቶችን፣ ወጎችን፣ ማህበራዊ ህጎችን እና መሰል በሆኑ ሃሳቦች የሚገነባ በመሆኑ ሙዚቃ በራሱ የባህል ክፍል ነው። በሙዚቃ የሚገለፁ ሃሳቦች ጥንካሬ እንዲኖራቸው ማህበረሰቡ በአካባቢው ቁሳቁስ እና ግብዓት ተጠቅሞ የሚያዘጋጃቸው የሙዚቃ መሳሪያዎች ሙዚቃን ከማሳመር እና ከማድመቅ በተጨማሪ ትዕምርት ሆነው የማህበረሰቡን ሁለንተናዊ ማንነት መግለፅ የሚችሉ ናቸው።

የባህል ሙዚቃ በቡድን ወይም በህብረት የሚከወን ሲሆን በውስጡ ባህላዊ ሙዚቃ መሳሪያዎችን እና ውዝዋዜን የሚያካትት ነው። ባህላዊ ውዝዋዜ ከማህበረሰቡ የባህል ልዩነት አኳያ በተለያዩ ስልተ-ምቶች ላይ ተመስርቶ የሚከወን በመሆኑ ከአካባቢ አካባቢ ይለያያል።

የባህላዊ ሙዚቃ፣ የሙዚቃ መሳሪያዎች እና ውዝዋዜዎች ከማህበራዊ እድገት ጋር አብረው ብዙ መሻሻሎችን በማድረግ ከጥንት ጀምረው የመጡ ናቸው። ባህላዊ ሙዚቃዎች ተፈጥሯዊ ከሆኑ ድምፆች (የነጎድጓድ ድምፅ፣ የነፋስ ድምፅ፣ የፏፏቴ ድምፅ) መነሻ በማድረግ ነው። የሙዚቃ መሳሪያዎች ጥቅም ላይ መዋል የጀመሩት በጥንት ዘመን ሰዎች እንስሳት ለማደን በሚወጡበት ጊዜ እንደ ምልክት መስጫነት በመጠቀም ነበር። የባህላዊ ውዝዋዜዎች መነሻ ምንጫቸው የተለያዩ የእንስሳት እንቅስቃሴች መሆናቸውን ማረጋገጥ ይቻላል።

የኢትዮጵያ ጥንታዊ ሀውልቶች በአብዛኛው በሀገራችን በተለያዩ ቦታዎች ማለትም በኢትዮጵ በተለያዩ አካባቢዎች እንደ አክሱም ሀውልት፣ የጥያ ትክል ድንጋይ፣ ኮንሶ ዋካዎች፣ የንጉስ ኢዛና ሀውልት ይገኙበታል። ከዚህ በተጨማሪም የተለያዩ የኢትዮጵያ ጥንታዊ የዕደ-ጥበብ ስራዎች ማለትም የሽክላ ስራዎች፣ የሽመና ስራዎች፣ ሳንቲሞች በአጠቃላይ የዕደ-ጥበብ ውጤቶች በሀገራችን በብዛት ይገኛሉ።

የቴያትር እና የፊልም ጥበብ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ በንግግር፣ በእንቅስቃሴ እና በቁሳቁሶች የሚመሰረቱ ጥበባዊ እሴት ተጨምሮባቸው የማህበረሰቡን ንቃተ ህሌና ለማሳደግ በሚረዳ መልኩ መልሰው በጊዜ እና በቦታ ተወስነው እና ተመስለው የሚቀርቡ ክውን ጥበባት ናቸዉ።

አካባቢያዊ ታሪኮች ለቴያትር እና ለፊልም ስራዎች ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ አላቸው። የአንድ አካባቢ ታሪክ የማህበረሰቡን ባህል በግልጽ የሚያሳይ የማንነት መገለጫ እና ስጦታ ነው። በመሆኑም አንድ ቴያትር ሲሰራ ትክክለኛ እና ታማኝ እንዲሆን እና የአንድ አካባቢን ማህበረሰቡ ባህል ለማስተዋወቅ የተውኔቱ ድርሰት ከአካባቢ ታሪክ የሚነሳ መሆን አለበት።

የምዕራፉ ቼክሊስቶች

ተማሪዎች በዚህ ምዕራፍ የተማራችኋቸውን ዋና ዋና ነጥቦች ማወቃችሁን አረጋግጡ።

ተ.ቁ	ይዘት	አሳክቻለሁ	አላሳካሁም
1	ሙዚቃ የማህበረሰቡን እውቀት፣ ልምድ፣ እምነት፣ ፖለቲካ ወዘተ በክዋኔ የሚገልፀ ባህላዊ ጥበብ መሆናቸውን ተገንዝቢያለሁ።		
2	ሙዚቃ የሰው ልጅ ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የነበረ እና እያደገ የመጣ ታሪካዊ ጥበብ መሆኑን ተረድቻለሁ።		
3	የሙዚቃ መሳሪያዎች ከማህበረሰቡ ባህል (እምነት፣ ልምድ፣ ችሎታ፣ እውቀት....) ጋር የተቆራኘ መሆኑን ተገንዝቢያለሁ።		
4	የሙዚቃ መሳሪያዎች የሰው ልጅ በሕይወት ልምዱ በጥራታቸው እና አጨዋወታቸው እየዳበሩ የመጡ መሆናቸውን አውቂያለሁ።		
5	በሰው ልጅ የሙዚቃ መሳሪያ አጠቃቀም ሂደት በቅድሚያ ጥቅም ላይ የዋሉት የምት እና የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያዎች እንደነበሩ አዉቂያለሁ።		
6	ባህላዊ ውዝዋዜ የንግግር ቋንቋዎች ከመፈጠራቸው በፊት ቃል አልባ በሆነ መንገድ ተግባቦትን እንደሚፈጥር እና ታሪክን የሚነግር እንደነበር ተረድቻለሁ።		
7	ባህላዊ ውዝዋዜዎች የማህበረሰቡን ባህል (እውቀት፣ ቁስ፣ ታሪክ፣ እምነት፣ እውቅት...) በአካላዊ እንቅስቃሴ እና ምልክቶች የሚገልፅ ባህላዊ ጥበብ መሆኑን ተረድቻለሁ።		
8	በውዝዋዜ የሚገለፁ ስሜቶችን እና የሚከወኑበትን ማህበረሰባዊ አውዶችን ለይቼ አውቂያለሁ።		
9	የቴያትር ጥበብ ቀደምት ታሪክ ያለው መሆኑን ተገንዝቢያለሁ።		

10	የቴያትር እና የፊልም ጥበብ ሁለንተናዊ የሆነውን የማህበረሰቡን እንቅስቃሴ በተለየ መልኩ ጥበባዊ እሴት ተጨምሮባቸው ተመልሰው ለማህበረሰቡ የሚቀርቡ ክውን ጥበባት መሆናቸውን ተገንዝቢያለሁ።		
11	አካባቢያዊ ታሪኮች ለቴያትር እና ለፊልም ድርሰት ያላቸው አስተዋጽኦን በግልጽ ተረድቻለሁ።		
12	የኢትዮጵያ ጥንታዊ ሀውልቶች ታሪክ አውቂአለሁ።		
13	የኢትዮጵያ ጥንታዊ የዕደ-ጥበብ ስራ ውጤቶችን መለየት ችያለሁ።		
14	የኢትዮጵያ ጥንታዊ የመገበያያ ሳንቲሞችን አውቃለሁ።		
15	የኢትዮጵያ ጥንታዊ ሀውልቶች እና የዕደ-ጥበብ ስራዎችን ታሪካዊ አመጣጥን መረዳት ችያለሁ።		
16	የኢትዮጵያ ጥንታዊ የዕደ- ጥበብ ስራ መስራት ችያለሁ።		

የማጠቃለያ መልመጃዎች

ትዕዛዝ አንድ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጡ።

1. ባህላዊ ሙዚቃ በምን በምን ማህበራዊ ሁነቶች እንደሚተገበር በመዘርዘር ከማህበራዊ ሁነቱ ጋር ያለውን ዝምድና ማብራሪያ ስጡ።
2. የሙዚቃ ታሪካዊነትን የሚያሳዩ ማረጋገጫዎችን ዘርዝሩ።
3. ቀደምት እና አሁናዊ የሙዚቃ አቀራረብ መሰረታዊ ልዩነቶችን ከነምክንያታቸው አስረዱ።
4. የሙዚቃ መሳሪያዎች ከባህል ጋር ያላቸውን ዝምድና ተናገሩ።
5. ውዝዋዜዎች ከባህል ጋር ያላቸውን ትስስር አስረዱ።
6. አካባቢያዊ ታሪኮች ማወቅ ለአንድ የተውኔት ደራሲ ያለውን ጠቀሜታ አብራሩ።

7. አንድ በአካባቢያዊ ታሪክ የተደረሰ ተውኔት በማንበብ የሚያስተላልፈውን መልዕክት በአጭሩ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለፁ።

8. በበራይ (ውቂያ) እና በእርሻ ወቅት የምንጠቀምባቸው ስነቃሎችን ሰብስባችሁ በመምጣት በዜማ በክፍል ውስጥ ለመምህራችሁ አቅርቡ።

9. በሽለላ እና በፉከራ የአንድን አካባቢ ባህል ለሌላ አካባቢ እንዴት ማስተዋወቅ ይቻላል? መልሳችሁን በምሳሌ በማስደገፍ ማብራሪያ ስጡ።

10. ስለ ጀግንነት እና የሀገር ፍቅር ስሜት የሚያነሳሱበት ግጥም ፅፋችሁ በመምጣት በተግባር በዜማ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

11. የኢትዮጵያ ጥንታዊ ሀውልቶች የሚገኙበትን ቦታ ዘርዝሩ።

12. በጣም ትልቁ የአክሱም ሀውልት ርዝመቱ ስንት ሜትር ነው?

13. የኢትዮጵያ ጥንታዊ ሽክላ ስራዎች ከምን አይነት ቁሳቁስ ይሰሩ እንደነበር ግለጹ።

14. በአብዛኛው የኢትዮጵያ ጥንታዊ ሀውልቶች የተሰሩበትን ዋናዋና ቁሳቁሶች ዘርዝሩ።



የምዕራፉ ዓላማዎች፦

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፦

- የክውን ጥበባት ጠቀሜታን ትገነዘባላችሁ።
- የክውን እና ዕይታዊ ጥበባትን ተግባር ታወዳድራላችሁ።
- የሀዉልቶች እና የዕደ-ጥበብ መስሪያ ቁሳቁሶችን መለየት ትችላላችሁ።
- የተሰሩ ሀዉልቶች እና የዕደ-ጥበብ ስራዎችን የሚያስተላልፉትን መልዕክት ትገነዘባላችሁ።
- የሥነ- ጥበባት ስራዎችን ታደንቃላችሁ።

መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ የምንማረው የክውን ጥበባት ጠቀሜታ፣ የክዉን ጥበብ እና የዕይታዊ ጥበባትን ማወዳደር እና ማነፃፀር፣ የሀዉልቶች መስሪያ መሳሪያዎች እና የሚያስተላልፉት መልዕክት እንዲሁም የዕደ-ጥበብ ስራ መስሪያ መሳሪያዎች እና የሚያስተላልፉት መልዕክትን ይሆናል።

4.1 የክውን ጥበባት ጠቀሜታዎች

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. የክውን ጥበባት ጠቀሜታን አብራሩ።
2. የክውን ጥበባትና የዕይታዊ ጥበባት ልዩነትን ታውቃላችሁ? የምታውቁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

የክውን ጥበባት ማህበረሰቡ ሕይወትን የተሳካ እና ጥሩ የአኗኗር ዘይቤ እንዲኖረው ለማድረግ የሚያስችሉ የጥበብ ዘርፎች ናቸው። ሃሳብን ከተለመደው በተለየ ሳቢ እና ማራኪ አድርጎ ለመግለፅ፣ ብሔራዊ አንድነትን ለመገንባት፣ ሥነ-ልቦናዊ ስሪትን ለመፍጠር የሚያገለግሉ ጥበባዊ ተግባራት በመሆናቸው ልዩ ችሎታ እና ክሂሎትን የሚጠይቁ መስኮች ናቸው። በማህበረሰቡ ውስጥ ከሚኖራቸው ፋይዳ አንፃር በሚከተለው መንገድ መመልከት አስፈላጊ ነው።

4.1.1 የክውን ጥበባት ሥነ-ውበታዊ ጠቀሜታ

ሀገር በተለያዩ ማህበራዊ ጠቀሜታ የተገነቡ ማህበረሰቦችን ያካተተ በመሆኑ በማህበራዊ ልማድ እና እውቀት የሚመሰረቱ ማንነቶችን ይፈጥራል። በእነዚህ ማህበራዊ እውቀቶች እና ልማዶች ላይ የሚመሰረቱ ማህበረሰባዊ መሰረት ያላቸው ጨዋታዎችን እና ቁምነገሮችን መግለፅ አስፈላጊ ነው። ጨዋታዎች መንፈስን በሚገዙ ውብ ዜማ የተደገፉ ግጥሞችን በመጠቀም የተደበቀውን የሰውልጅ ስሜት እና ፍላጎት የሚገልጹ ለማህበረሰቡ መልሰው በልዩ ሁኔታ የሚቀርቡ ናቸው። በእነዚህ ክውን ጥበባት ከሚገለፀው ማህበራዊ ሃሳቦች ውስጥ እምነት፣ አስተዳደራዊ ክህሎቶች፣ ፍቅር፣ ውበት፣ ሀገር ወዘተ በተዋበ መንገድ የሚያቀርብ በመሆኑ ትርጉም ያለው ማህበራዊ ተግባቦት መፍጠር የሚያስችሉ ናቸው።

4.1.2 የክውን ጥበባት ባህላዊ (ብሔራዊ) ጠቀሜታ

ክውን ጥበባት በማህበረሰቡ ልምድ እና እውቀት የሚፈጠሩ እና የማህበረሰብን ታሪክ፣ ወግ፣ ልምድ፣ እውቀት፣ እምነት፣ ፖለቲካ፣ ትምህርት እና መሰል ሁኔታዎችን የሚናገሩ እና ከትውልድ ትውልድ የሚያሻግሩ ናቸው። የሀገር አንድነትን የሚያስቀጥሉ ሀገር ወዳድነትን የሚሰብኩ ናቸው። በሀገራችን ስለሀገር አንድነት የሚያወሱ በርካታ መዚቃዎች ያሉ ሲሆን “እናት ኢትዮጵያ”፣ “ሀገሬን አረሳም”፣ “አጥንቴም ይከስክስ ደሜም ይፈስስላት”፣ “ሆብየ እመጣለሁ ሆብየ በድል” የሚሉት ዜማዎች መጥቀስ ይቻላል።

ተግባር 4.1

1. ከላይ ከተጠቀሱት ሀገራዊ አንድነትን የሚያወሱ ዘፈኖች መካከል አንዱን መርጣችሁ ግጥሙን በመፃፍ በተግባር ሰርታችሁ አሳዩ እና የዘፈኑን መልዕክት አስረዱ።

4.1.3 የክውን ጥበባት ሥነ-ልቦናዊ ጠቀሜታ

የሰው ልጅ በማህበራዊ ሕይወቱ የተሳካለት እንዲሆን የመሆን፣ የማሰብ እና በራስ የመተማመን አቅሙን ማጎልበት ያስፈልገዋል። በዚህ ረገድ ደግሞ የሥነ-ልቦናዊ ስራቱ እና ዝግጅቱ በተለያዩ ጥበባዊ ስራዎች ይገለፃሉ። ይህንን ሥነ-ልቦናዊ ጥንካሬ በቀላሉ መገንባት የሚያስችሉ የተለያዩ የጥበብ ስራዎች አሉ። ይሁን እንጅ ማህበረሰቡን በማንቃት ሂደት የሰው ልጅ ማህበራዊ እና ኃይማኖታዊ ህጎችን እንዲያከብር፣ እንዲመራባቸው ወዘተ ማድረግ የሚያስችሉት ክውን ጥበባት ጉልህ ሚና አላቸው። በመሆኑም ማህበራዊ እና ግለሰባዊ ፈውስን፣ የጀግንነት (ጀብደኝነት) ስሜትን የሚያረጋግጡ ጥበባዊ ስራዎች በቴያትር፣ ሙዚቃ እና ውዝዋዜዎች አማካኝነት ማስረፅ ይቻላል። ክውን ጥበባት ከሚያረጋግጡት ደህንነቶች ውስጥ ሀይማኖታዊ፣ ሀገር መውደድን፣ ከራስ አልፎ ለሰዎች መኖርን፣ ሥነ-ምግርን ወዘተ ሥነ-ልቦናዊ ደህንነቶችን ማረጋገጥ የሚያስችሉ የቴያትር እና ሙዚቃ ስራዎችን መመልከት ይቻላል።

ተግባር 4.2


1. ሀገራዊ ስሜትን ሊያረጋግጥ የሚችል አንድ ዘፈን መርጣችሁ በተግባር በመስራት ዘፈኑ እንዲፈጥር የታሰበውን ሥነ-ልቦናዊ እሴት ተናገሩ።
2. የክውን ጥበባትን ሥነ-ውበታዊ ጠቀሜታ በምሳሌ በማስደገፍ ማብራሪያ ስጡ።
3. የክውን ጥበባትን ብሔራዊ ጠቀሜታ በምሳሌ በማስደገፍ ማብራሪያ ስጡ።

የመዝሙሩ ርዕስ፦ ስራ

የመዝሙሩ ግጥም

ስራ መስራት መስራት መስራት ያስደስታል፣
ሀገርን ወገንን እራስን ያኮራል፣
አናጢነት፤
ግንበኝነት፤
ስራ ነው ክቡር ነው፤
ሰውን ሰው ያሰኘው። (2 ጊዜ)

ስራ መስራት መስራት መስራት ያስደስታል፣
ሀገርን ወገንን እራስን ያኮራል፣
ሽማኔነት፣
ቀጥቃጭነት፣
ስራ ነው ክቡር ነው፣
ሰውን ሰው ያሰኘው። (2 ጊዜ)
ስራ መስራት መስራት መስራት ያስደስታል፣
ሀገርን ወገንን እራስን ያኮራል፣
ሰዓሊነት፣
ሙዚቀኛነት፣
ስራ ነው ክቡር ነው፣
ሰውን ሰው ያሰኘው። (2 ጊዜ)
ስራ መስራት መስራት መስራት ያስደስታል፣
ሀገርን ወገንን እራስን ያኮራል፣
አስተማሪነት፣
ሐኪምነት፣
ስራነው ክቡር ነው፣
ሰውን ሰው ያሰኘው። (2 ጊዜ)



4.2 ዕይታዊ እና ክውን ጥበባትን ማወዳደር

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. የዕይታዊ ጥበባት የምንላቸውን ዘርዝሩ?
2. የክውን ጥበባት የምንላቸውን ዘርዝሩ?
3. የዕይታዊ ጥበባት እና የክዉን ጥበባት የአንድን አካባቢ ባህል ለመግለጽ ያላቸው አስተዋጽኦ እኩል ነው ወይስ እኩል አይደለም? ይሽን መነሻ በማድረግ ክርክር አድርጉ።
4. የክውን ጥበባትና የዕይታዊ ጥበባት ለማህበረሰብ የሚሰጡትን ጠቀሜታ በመዘርዘር ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

የዕይታዊ ጥበባት ሃሳብን፣ ውስጣዊ ስሜትን፣ መልዕክቶችን በፎቶ ግራፍ፣ በቀለም ቅብ፣ በቅርፅ እና በንድፍ የምንገልጽባቸው ጥበባት ሲሆኑ በዋናነት የተለመዱ አቀራረቦችን በተለየ መንገድ ለመንገር የምንጠቀምባቸው ጥበባዊ መንገዶች ናቸው።

የዕይታዊ ጥበባት በእጃችን አንድን ነገር በማከናወን የምንፈጥራቸው ናቸው።

የዕይታዊ ጥበባት ታሪካዊ ቦታዎችን እና ባህላችንን ለሚቀጥለው ትውልድ በሸራላይ ወይም በፎቶግራፍ አማካኝነት ማስተላለፍ የሚያስችሉን የጥበብ ዘርፍ ናቸዉ።

የክውን ጥበባት ውስጣዊ ስሜታችን፤ባህላችንን እና መልዕክታችንን በሙዚቃ፣ በዳንስ፣ በቴያትር ድምጽን እና አካላዊ እንቅስቃሴን በመጠቀም የምንገልጽባቸው ጥበባት ሲሆኑ በህዝብ ታዳሚዎች ፊት ትሪዒትን እና ክሂሎትን የሚጠይቁ ናቸው።

የክውን ጥበባትን በመጠቀም ማለትም በሙዚቃ፣ በዳንስ እና በቴያትር የአንድን አካባቢ ባህል ለሌሎች ማህበረሰብ ማስተዋወቅ ይቻላል።

የዕይታዊ እና ክውን ጥበባት ለሁሉም ማህበረሰብ በጣም አስፈላጊ ናቸው። በእነዚህ ጥበባት የአንድን ሀገር ባህል ለቀጣይ ትውልድ እና ለአሁኑ ትውልድ ለማስተላለፍ ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ አላቸው። የዕይታዊ እና ክውን ጥበባት የማይነጣጠሉ ጥበቦች ሲሆኑ የሚለያዩት በሚተላለፉበት መንገድ ነው።

ተግባር 4.3

1. የክውን እና ዕይታዊ ጥበባት አንድነት እና ልዩነታቸውን አብራሩ።
2. በዕይታዊ ጥበባት እንዴት ሃሳብና ስሜትን መግለፅ እንደሚቻል በምሳሌ በማስደገፍ ማብራሪያ ስጡ።
3. በክውን ጥበባት እንዴት ሀሳብና ስሜትን መግለፅ እንደሚቻል በምሳሌ በማስደገፍ ማብራሪያ ስጡ።
4. በአካባቢያችሁ አንድ ርዕሰ ጉዳይ በመምረጥ በክውን ጥበባት እና በዕይታዊ ጥበባት መካከል ያለውን ልዩነት በተግባር ሰርታችሁ አሳዩ።

4.3 የሀውልቶች እና የዕደ- ጥበብ መስሪያ መሳሪያዎች እና መልዕክቶቻቸው

4.3.1 የሀውልቶች መስሪያ መሳሪያዎች እና የሚያስተላልፉት መልዕክት

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. የምታዉቋቸዉን ሀዉልቶች በመዘርዘር ከምን እንደተሰሩ እና የሚያስተላልፉትን መልዕክት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።
2. በአካባቢያችሁ ከምታውቋቸው ሀውልቶች መካከል የተወሰኑትን በመዘርዘር ያላችሁን አድናቆት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

በሀገራችን የተከሰቱ ታሪካዊ ክስተቶችን ለመዘከር እና ታሪካዊ ሰዎችን ለማስታዎስ በርካታ ሀውልቶች ይገኛሉ። እነዚህ ህያው የታሪክ ምስክሮች ሀገራችን ያለፈችበትን ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ኪነ-ጥበባዊ እና ባህላዊ ገጽታ የሚያስታውሱ በመሆናቸው በሀገር ውስጥም ሆነ በሀገር ውጭ ቱሪስት ይጎበኛሉ።

ብዙዎቹ ሀውልቶች መሰረታቸው ላይ የሰሩትን ስራ በመጥቀስ ከግርጌያቸው የሚነበብ ጽሁፍ ይጻፉባቸዋል። እነዚህ በከተሞች በተለያዩ ቦታዎች የተሰሩ ሀውልቶች በጎብኝዎቻቸው የሚያስተላልፏቸው እጅግ በርካታ ቁም ነገሮች አሉ።

በሀገራችን በኢትዮጵያ በተለያዩ ጊዜያት (ዘመን) በሚሰሩት ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ጉዳዮች (ክስተቶች) የተሰሩ ወይም የተተገበሩ ጉዳዮችን ለማስተላለፍ የተለያዩ ሀውልቶች ይሰራሉ። ለምሳሌ ያህል የተወሰኑትን ሀውልቶችና የሚያስተላልፉትን መልዕክት እንመልከት፤-

ሀ) **የአክሱም ሀውልቶች፦** እነዚህ ሀውልቶች በብዛት የሚገልፁት አክሱም በስልጣኔ ምን ደረጃ ላይ ደርሳ እንደነበር የሚጠቁሙና በመሰረታቸው ደግሞ የንጉሱ ቤተሰቦች እንዲሁም ከፍተኛ ስልጣን ያላቸው ሰዎች መቃብር ይሆን ዘንድ ታስቦ መሰራቱን አንዳንድ የታሪክ መዛግብት ይጠቁሙናል። ሀውልቶችም የተሰሩት ከአንድ ቋጥኝ ድንጋይ በመቦርቦር ወይም በመቅረፅ ነዉ።

ለ) **የአጼ ምንሊክ ሀውልት፦** በኢትዮጵያ ዋና ከተማ አዲስ አበባ ስላሉት ሀውልቶች ሲነሳ በቅድሚያ የሚጠቀሰው የቀድሞ አራዳ የዛሬው ፒያሳ ከአራዳ ጊወርጊስ ፊት ለፊት የቆመው የዳግማዊ አጼ ምንሊክ ሀውልት ነው።

በጸረ ኮሎኒያሊዝም ትግላቸውና የዘመናዊ ስልጣኔም ወደ ኢትዮጵያ በማስገባት የሚታወቁት ዳግማዊ አጼ ምንሊክ ማስታዎሻ እንዲሆን ልጃቸው ንግስት ዘውዲቱ ያሰሩት ሀውልት ነው። የተሰራበት ቁሳቁስም ከነሃስ ነው። ጥበባዊው አሰራሩም እጅግ የተዋጣለት ነዉ። ይህ ሀውልት የተሰራበት ዋና ዓላማ በስልጣን ዘመናቸው ለኢትዮጵያ ብሎም ለአፍሪካ ጥቁር ህዝቦች ትልቅ ኩራት የሆነዉን የአድዋ ድል ታሳቢ በማድረግ ነዉ። ፈረሱ የተመሰለውም በአባዳኘው በሚል መጠሪያ ነው።



ሥዕል 47 የአጼ ምንሊክ ሀውልት

ሐ) **የቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ሀውልት፦** ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ጣሊያን ለሁለተኛ ጊዜ ኢትዮጵያን ስትወር ለአምስት አመት ያህል ከፍተኛ የሆነ ትግል አድርገዋል። በተጨማሪም የአፍሪካ ህብረት ዋና መቀመጫው አዲስ አበባ እንዲሆን ከፍተኛ ስራ በመስራታቸው በአፍሪካ ዩኔን የታወቁ ንጉስ በመሆን ሀውልት ተሰርቶላቸዋል። ሀውልቱ የተሰራውም ከነሃስ ነው። ይህ ሀውልት የተሰራበት ዋና ዓላማ በስልጣን ዘመናቸው ለኢትዮጵያ ትልቅ ስራ የሰሩ መሆናቸውን ለመጭው ትውልድ ታሪካቸውን ለማስተላለፍ ነው።



ሥዕል 48 የቀዳማዊ ኃ/ስላሴ ሀውልት

መ) **የብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ሀውልት፦** 1929 ዓ.ም ለሀገራቸው እና ለዕምነታቸው መሰዋትነት ከፍለው ካለፉ ኢትዮጵያዊያን ውስጥ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ አንዱ ናቸው። ሀገራችን በጠላት ተወራ በነበረበት ዘመን ህዝቡ ለሀገሩ ነጻነት አጥብቆ እንዲዋጋ፣ ለጠላት እንዳይንበረከክ በትጋት ይሰብኩ እና ያስተምሩ ነበር። ከሀገራቸው ክብር ውጭ የሚያስቀድሙት ምንም ነገር እንደሌለ እና ከጣሊያን መንግስት ጋር እንደማይተባበሩ በቁርጠኝነት በመናገራቸው በጣሊያን ወታደሮች በመትረጊስ ተደብድበው በ1929 ዓ.ም ተገደሉ። የአቡነ ጴጥሮስ ሀውልት የተሰራው ነጻነት ከተመለሰ ሳይውል ሳያድር በ1933 ዓ.ም ሃምሌ 22 ቀን በዚያው በጥይት ተደብድበው ከሞቱበት ቦታ ላይ ነዉ። ከሀዉልቱ ግርጌ የጳጳሱ ታሪክ በአጭሩ ተጽፎ የሚገኝ ሲሆን ሀውልቱ የተሰራበት ግባትም ከነሀስ ነዉ።



ሥዕል 49 የብጹዕ አቡነ ጴጥሮስ ሀውልት

ከእነዚህ ሀዉልቶች በተጨማሪ ብዙ የመታሰቢያ ሀዉልቶች መዘርዘር እና መጥቀስ ይቻላል። ለምሳሌ፦ የደጃ አዝማች በላይ ዘለቀ፣ የአጼ ቴወድሮስ መታሰቢያ ሀዉልት፣ የይሁዳ አንበሳ፤የኢትዮጵያ አርበኞች፣ የካራ ማራ ድል መታሰቢያ ሀዉልቶችን መጥቀስ ይቻላል።



ሥዕል 50 የደጃዝማች በላይ ዘለቀ ሀውልት



ሥዕል 51 የአፄ ቴወድሮስ ሀውልት

ተግባር 4.4

1. ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ሀውልቶች ከተመለከታችሁ በኋላ ለእያንዳንዳቸው የሚያስተላልፉትን መልክት እና የተሰሩበትን መስሪያ መሳሪያ በአጭሩ ግለጹ።
2. ሀውልት ሲሰራ ምን ምን ነገሮችን ማካተት ወይም መግለጽ አለበት?
3. የሀውልቶች መልዕክትና ጠቀሜታ ዘርዝሩ።
4. በሀገራችን ስለምታውቋቸው ሀውልቶች ስለአሰራራቸው ያላቸውን አድናቆት ለክፍል ለጓደኞቻችሁ በዘገባ መልክ አቅርቡ።
5. ከላይ ከተዘረዘሩት ሀውልቶች በተጨማሪ በአካባቢያችሁ የምታውቋትን በመዘርዘር ከምን እንደሚሰሩ ማብራሪያ ስጡ።
6. በሀገራችን የተሰሩ ሀውልቶች በመዘርዘር ስለተሰሩት የሀውልት ስራዎች በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸውን ተቀባይነትና መልዕክቶቻቸውን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።
7. የምትፈልጉትን የሀውልት ስራ በኪነ-ቅርጽ በተግባር ሰርታችሁ አሳዩ።

4.3.2 የዕደ-ጥበብ መስሪያ መሳሪያዎች እና የሚያስተላልፉት መልዕክት

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. የዕደ-ጥበብ ስራ ማለት ምን ማለት ነው?
2. የዕደ-ጥበብ ስራዎች ለማህበረሰቡ ምን አይነት አስተዋጽኦ እንዳላቸው እና የሚሰሩበትን ግብዓት በመለየት ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ።

በሀገራችን በሁሉም ብሔር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ዘንድ የራሳቸው የሆኑ ልዩልዩ ባህላዊ ትርጓሜ እና ጠቀሜታ ያሏቸው ሀገራዊ የዕደ-ጥበብ ስራዎች አሉ። እነዚህ ሀገራዊ የዕደ-ጥበብ ስራዎች የሚሰሩበትን ግብዓቶች መነሻ በማድረግ የእጨት፣ የወረቀት፣ የጸጉር፣ የክር፣ የቆዳ፣ የቀንድ፣ የብረት፣ የድንጋይ ወዘተ በሚል ይቀመጣሉ።

ሀ) ስፌት እቃዎች

የስፌት እቃዎች የሚባሉት ሞሰበ ወርቅ፣ ቀለምሻሽ፣ ሞሰብ፣ ወስከንቢያ፣ ቁና፣ ወንፊት፣ ሰፌድ፣ አገልግል እና የመሳሰሉት ሲሆኑ በአብዛኛው በሀገራችን ባህል ሴቶች ብቻ ሲሰሯቸው የመጡ የእጅ ስራ ዉጤቶች ናቸዉ። እነዚህን የጥበብ ስራዎች ከጥንት ጀምሮ ለመመገቢያ፣ ባህልን ለመግለጽ እና ለቤት ጌጣጌጥ ወይም ማስዋቢያ እንጠቀምባቸዋለን። የሚሰሩበት የመስሪያ ግብዓቶችም ግራምጣ፣ የቀጠማ አንን፣ የተለያዩ የኬሻ ክሮች፣ የሰኔል አንን እና የመሳሰሉት ናቸው።



ሥዕል 52 የስፌት እቃዎች

ለ) የሸክላ ስራዎች

የሸክላ ስራዎች የአካባቢን ባህል ከጥንት ዘመን ጀምሮ የአባቶቻችን እና የእናቶቻችን ልምድ በመቀበል ለመመገቢያ ዝግጅት አገልግሎት፣ለገቢ ምንጭነት እና ባህልን ለመግለጽ የምንጠቀምባቸዉ የዕደ-ጥበብ ዉጤቶች ሲሆኑ የሚሰሩትም ከሸክላ አፈር ሆኖ በባህላዊ እና በዘመናዊ መንገድ ነው።





ሥዕል 53 የተለያዩ የሸክላ ስራ ውጤቶች

ሐ) ተለያዩ የጦር መሳሪያዎች

የጦር መሳሪያዎች የምንላቸው ከጥንት ዘመን ጀምሮ አባቶቻችን ከጠላት እራስን እና ሀገርን ለመጠበቅ እንዲሁም ለአደን ተግባራት ሲጠቀሙባቸው የነበሩ እንደ ጠመንጃ፣ ጦር፣ ጩቤ፣ ጋሻ፣ ጎራዴ እና የመሳሰሉት ናቸው። እነዚህ መሳሪያዎች ከእንጨት፣ ከድንጋይ፣ ከብረታብረት ወዘተ ይሰራሉ።






ሥዕል 54 የተለያዩ የጦር መሳሪያዎች

መ) ተለያዩ ጌጣጌጦች

ጌጣጌጦች የሰዉን ልጅ ዉበት እና ድምቀት ለመጨመር ታስበዉ የሚሰሩ ሀገር በቀል የዕደ-ጥበብ ዉጤቶች ሲሆኑ የሚሰሩትም ከመደብ፣ ከብር፣ ከነሀስ፣ ከወርቅ፣ ከክር፣ ከፀጉር ወዘተ የሚሰሩ የጥበብ ዉጤቶች ናቸዉ።





ሥዕል 55 የተለያዩ የጌጣጌጥ ስራ ውጤቶች

ተግባር 4.5.

1. ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን የዕደ -ጥበብ ስራ በደንብ ካስተዋላችሁ በኋላ የሚያስተላልፉትን መልዕክት ለእያንዳንዳቸው ማብራሪያ ስጡ።
2. የዕደ-ጥበብ ስራ የሚሰሩ ባለሙያዎችን ሂዳችሁ በማየት ስለሰሩት ጥበብ አጭር ዘገባ በማዘጋጀት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።
3. ከቤታችሁ ከምታውቋቸው የዕደ-ጥበብ ስራ ውጤቶች መካከል አንዱን በመምረጥ በምትፈልጉት መንገድ በተግባር ሰርታችሁ አሳዩ።
4. ከአካባቢያችሁ በመነሳት ስለዕደ-ጥበብ ባለሙያዎች እና የዕደ-ጥበብ ውጤቶች የማህበረሰቡ አስተያየት ወይም አቀባበል ምን እንደሚመስል የሚገልጽ አጭር ዘገባ አቅርቡ።

የምዕራፉ ማጠቃለያ

ሙዚቃ እጅግ በጣም የተለያዩ በሆኑ አውዶች ውስጥ የሚገኝ እና የማህበረሰቡን ታሪክ የሚዘግብ ነው። ውዝዋዜ በጣም የተወሳሰበ ቢሆንም በአካላዊ እንቅስቃሴ ሃሳብ እና ስሜትን የምንገልጽበት ነው።

ክውን ጥበባት ውስጣዊ ስሜታችን፣ ባህላችንና መልዕክቶቻችንን በአካላዊ እንቅስቃሴ የምንገልጽባቸው የጥበብ አይነቶች ናቸው። ዕይታዊ ጥበባት ውስጣዊ ስሜታችንና መልዕክቶቻችንን በፎቶግራፍ እና በቀለም ቅብ እና በኪነ-ቅርፅ የምንገልጽባቸዉ የጥበብ አይነቶች ናቸው።

ክዉን ጥበባት ሥነ- ዉበታዊ፣ ብሄራዊ እና ሥነ- ልቦናዊ ጠቀሜታ ያለዉ የጥበብ ዘርፍ ነዉ።

በሀገራችን ውስጥ የተከሰቱ ታሪካዊ ክስተቶችን ለመዘከር እና ታሪካዊ ሰዎችን ለማስታዎስ በኢትዮጵያ በርካታ ሀውልቶች እና የዕደ-ጥበብ ስራዎች ይገኛሉ። እነዚህ ሀያው የታሪክ ምስክሮች ሀገራችን ያለፈችበትን የፖለቲካ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ኪነ-ጥበባዊ፣ እና ባህላዊ ገጽታን የሚያስታውሱ በመሆናቸው በሀገር ውስጥም ሆነ በሀገር ውጭ በቱሪስት ይጎበኛሉ። ብዙዎቹ ሀውልቶች መሰረታቸውን ምክንያት በመጥቀስ ከግርጌያቸው የሚነበብ ይጻፍባቸዋል። እነዚህ በከተሞች በተለያዩ ቦታዎች የተተከሉ ሀውልቶች በጎብኝዎቻቸው የሚያስተላልፏቸው እጅግ በርካታ ቁም ነገሮች አሉ።

ሀውልት በአደባባይ ላይ ሊሰራ የሚችል፣ የአፍሪካን ባህላዊ ትስስርን እና አንድነትን የሚያመላክት ጥበባዊ ዘርፍ ነው። ከጥንት ሉሲ ጀምሮ የአክሱም ሀውልትን ይዞ ልዩ ልዩ የአፍሪካ ሀውልቶችና የዕደ- ጥበብ ስራዎችን አካቶ ከእስክንደሪያ እስከ ደቡብ አፍሪካ፣ ከሶማሊያ እስከ ሴኔጋል እና ጊኒ ያሉትን የአፍሪካ ባህልን ያንጸባርቃል።

የሀውልቶች እና የዕደ-ጥበብ መስሪያ መሳሪያዎች እና ግብዓቶች ሊለይ ይችላል።

የሀውልቶች እና የዕደ-ጥበብ መስሪያ ወይም ግብዓቶች የሚባሉት፣ ጆሶ፣ ስሚንቶ፣ ድንጋይ፣ አሸዋ፣ እንጨት፣ ብረት፣ ሸቦ፣ እንደ አስፈላጊነቱም ከመዳብ፣ ከነሃስ፣ እና ከመሳሰሉት ግብዓቶች ይሰራሉ።

የምዕራፉ ቼክሊስቶች

ተማሪዎች በዚህ ምዕራፍ የተማራችኋቸውን ዋና ዋና ነጥቦች ማወቃችሁን አረጋግጡ

ተ.ቁ	ይዘት	አሳክቻለሁ	አላሳካሁም
1	የክውን ጥበባት ጠቀሜታን ተረድቻለሁ።		
2	የዕይታዊ እና ክውን ጥበባት ልዩነትን ተረድቻለሁ።		
3	ዕይታዊ እና ክውን ጥበባት በመጠቀም ሀሳብ እና መልዕክትን መግለጽ ችያለሁ።		
4	የሀውልቶች እና የዕደ-ጥበብ ስራ መስሪያ መሳሪያዎችን አውቃለሁ።		
5	ሀውልቶች የሚያስተላልፉትን መልዕክት መገንዘብ ችያለሁ።		
6	የዕደ-ጥበብ ስራ ውጤቶችን በተግባር መስራት ችያለሁ።		
7	የእደ ጥበብ ስራ የሚያስተላልፉትን መልዕክት ተረድቻለሁ።		

የማጠቃለያ መልመጃዎች

ትዕዛዝ አንድ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ማብራሪያ ስጡ

1. አንድ ታሪካዊ ሀውልት ሲሰራ መካተት ያለበት ጉዳይ ምንድን ነው?
2. የዕደ -ጥበብ ስራ በህብረተሰቡ ዘንድ ሲሰሩ የሚጠቀሙባቸውን ግብዓቶች ዘርዝሩ።
3. ሀውልቶች እና የዕደ-ጥበብ ስራ ለህብረተሰቡ የሚያስተላልፉትን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ መልዕክት ለጓደኞቻችሁ ግለጹ።
4. የቴያትር፣ የዳንስ፣ እና የሙዚቃ ቅንጅታዊ ስራን በማብራራት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።
5. የክውን እና የዕይታ ጥበባትን ልዩነትን በማብራራት በተግባር ሰርታችሁ አሳዩ።
7. የክውን ጥበባት ሥነ- ውበታዊ እና ሥነ- ልቦናዊ ጠቀሜታን አብራሩ።
8. ታሪክን ከትዉልድ ወደ ትዉልድ ለማስተላለፍ ዕይታዊ እና ክዉን ጥበባት ያላቸዉን ፋይዳ በምሳሌ በማስደገፍ ማብራሪያ ስጡ።

ምዕራፍ 5

የሥነ-ጥበባት ትምህርት ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ያለው ዝምድና

የምዕራፉ ዓላማዎች፦

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፦

- የሥነ-ጥበባት ትምህርት ከተለያዩ የትምህርት አይነቶች ጋር ያለውን ዝምድና ትረዳላችሁ።
- የሥነ-ጥበባት ትምህርት ሌሎች የትምህርት አይነቶችን በቀላሉ ለማስተማር ያለዉን ጠቀሜታ ትረዳላችሁ።
- የሥነ-ጥበባት ትምህር ከወቅታዊ ጉዳዮች ጋር ያለውን ዝምድና ትረዳላችሁ።
- በክውን እና በዕይታዊ ጥበባት የተሰሩ ስራዎችን ታደንቃላችሁ።
- የዕይታዊ እና ክውናዊ ጥበባትን በመጠቀም ወቅታዊ ጉዳዮችን ለማህበረሰቡ በቀላሉ እንዴት ማስገንዘብ እንደሚቻል ታውቃላችሁ።

መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ በዋናነት የምንማረው የሥነ-ጥበባት ትምህርት ጽንሰ ሀሳብ ከሌሎች ትምህርቶች እና ወቅታዊ ጉዳዮች ጋር ማስተሳሰርን የምትማሩበት ምዕራፍ ነው።

5.1 የሥነ-ጥበባት ትምህርት ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ያለዉ ዝምድና

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. የሥነ-ጥበባት ትምህርት ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ምን ዓይነት ዝምድና አላቸው?
2. የሥነ-ጥበባት ትምህርት ለሌሎች የትምህርት ዓይነቶች የሚሰጡትን ጠቀሜታ ታውቃላችሁ? ማብራሪያ ስጡ።
3. የሥነ-ጥበባት ትምህርት ከወቅታዊ ጉዳዮች ጋር እንዴት ማስተሳሰር እንደሚቻል ማብራሪያ ስጡ።

ሥነ-ጥበባት የሰው ልጅ የሚያየውን፣ የሚሰማውንና ወደፊት የሚመኘውን ነገር ሃሳቡን፣ እይታውን፣ እውቀቱን፣ ማንነቱን ወ.ዘ.ተ ከሚገልፅባቸው እና ከሚያንፀባርቅባቸው መንገዶች ውስጥ ዋናዎቹ ናቸው።


በመሆኑም እነዚህ የሙያ መስኮች ሌሎች የትምህርት ዓይነቶችን በተማሪዎች ተወዳጅ እና አይረሴነት እንዲኖራቸው በተዘዋዋሪም ሆነ በቀጥታ ከፍተኛ የሆነ አስተዋፅዖ ያደረጋሉ። ተማሪዎች የሚማሯቸውን የተለያዩ የትምህርት አይነቶችን ከመዝሙር፣ ከግጥም (ከድራማ) እና ከሥዕል ጋር በማቀናጀት በተማሪዎች ዘንድ የሚፈለገውን የትምህርት ውጤት ማምጣት ይቻላል።

ሥነ-ጥበባት ከሁሉም የትምህርት አይነቶች ጋር ዝምድና እንዳለው ለማሳየት የተወሰኑ ምሳሌዎችን መመልከት ይቻላል።

- ከተፈጥሮሳይንስ
- ከማህበራዊ ሳይንስ
- ከሒሳብ
- ከቋንቋ እና ከመሳሰሉት የትምህርት ዓይነቶች ጋር ካለው ዝምድና በተጨማሪ ይዘቶችን ቀላል እና አይረሴነትን ለመፍጠር የሚያገለግሉ እንዲሁም በተጨማሪ የድግግሞሽ መማር እድልን የሚፈጥሩ ናቸው።

የሥነ-ጥበባት ዘርፎች (ክውን እና ዕይታዊ ጥበባት) በሰው ልጅ የሕይወት እንቅስቃሴ ላይ ትኩረት በሚያደርጉ ሁለንተናዊ ተግባራት ላይ ስኬታማ ማህበራዊ መስተጋብር እንዲኖር ከማድረጋቸው በተጨማሪ የተለያዩ እውቀቶችን ለማስጨበት በሚደረጉ የእውቀት ሽግግሮች ሂደት ላይ የሚኖራቸው ሚና ከፍተኛ ነው።

የሰው ልጅ በመሰረታዊነት ሕይወትን የተሳካ እና ሙሉ ለማድረግ ያስችላሉ ብሎ እንደትምህርት መስክ ተደርገው የተቀመጡ እና ሳይንስ እና ቴክኖሎጅን ማጎልበት፣ አዲስ ሃሳብን ማበልፀግ፣ ነገን የተሻለ ከማድረግ እና የተሳካ ተግባቦትን መፍጠር ከሚያስችሉ የትምህርት መስኮች ጋር የሥነ-ጥበባት ትምህርትን (ክውን እና ዕይታዊ ጥበባት) ያላቸውን ተዛምዶ መመልከት ይቻላል።



5.1.1. ክውን ጥበባት ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ያላቸው ዝምድና

ሀ) ክውን ጥበባት ከተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርት ጋር ያላቸው ዝምድና

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. ክውን ጥበባት ከተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርት ጋር ምን ዝምድና አላቸው?
2. ክውን ጥበባትን በመጠቀም ተፈጥሮ ሳይንስን እንዴት ማስተማር ይቻላል?


ክውን ጥበባት ከተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርት ጋር በድምፅ አፈጣጠር፤በድምፅ ከፍታና ዝቅታ፣በትንፋሽ አጠቃቀም፣በንዝረት፣በርግብግቦሽ፣ በሙዚቃ መሳሪያዎች ቅኝት እና በመሳሰሉት ርዕሰ ጉዳዮች ከፍተኛ የሆነ ዝምድና አላቸዉ። ለምሳሌ ያህል በትንፋሽ አጠቃቀም ብናይ በክዉን ጥበብ አንድ ዜማ ለመጫወት የግድ የትንፋሽ አጠቃቀምን ማለትም አየር መቸ ማስገባት እንዳለብን እና ማስወጣት እንዳለብን እናዉቃለን። ስለዚህ ከዚህ ምሳሌ መረዳት የሚቻለዉ ክዉን ጥበብ ከተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርት ጋር ከፍተኛ የሆነ ዝምድና እንዳለዉ ነዉ።

የክውን ጥበባትን በመጠቀም የተፈጥሮ ሳይንስ ይዘቶችን በመዝሙር፣ በቴያትር፣ በድራማ፣ በፊልም እና በዘፈን በመሳሰሉት የማስተማሪያ ዘዴዎች በቀላሉ ማስተማር ይቻላል። ለምሳሌ ከዚህ በታች ያለውን መዝሙር በመዘመር እንዴት የተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርትን በቀላሉ ማስተማር እንደሚቻል እንመልከት።

የመዝሙር ርዕስ፦ ኤድስ እንዳያጠቃን

የመዝሙሩ ግጥም

አስከፊው በሽታ ኤድስ እንዳያጠቃን፣
እኛ ተማሪዎች መጠንቀቅ አለብን።
ባለም ዙሪያ ሁሉ ህዝብን የበከለው፣
በህክምና ዘርፍ ምንም መፍትሄ ያጣው፣
የሰው ልጆች ጠላት ቀሳፊው ኤድስ ነው።
ጥቁር ነጭ አይመርጥም ድንበር አያግደው፣
አስከፊው በሽታ ኤድስ እንዳያጠቃን፣
እኛ ተማሪዎች መጠንቀቅ አለብን።
ሁሉንም ይቀስፋል ቀሳፊው በሽታ፣
ካልተጠነቀቅንን አይሰጠንም ፋታ።
እንከላከለው ነገ ዛሬ ሳንል፣
ከጤና አገልግሎት ምክር በመቀበል።



ተግባር 5.1

1. ከዚህ በላይ የተቀመጠው መዝሙር በመጠቀም እንዴት የተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርትን በቀላሉ ማስተማር እንደሚቻል ተወያዩ እና ማብራሪያ ስጡ።
2. የክውን ጥበባትን ተጠቅመን እንዴት የተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርትን በቀላሉ ማስተማር እንደሚቻል የሚያሳይ አንድ የተግባር ስራ ሰርታችሁ አሳዩ።

ለ) ክውን ጥበባት ከማህበራዊ ሳይንስ ጋር ያላቸው ዝምድና

ክውን ጥበባት በማህበረሰቡ ጠቀሜታ ላይ የሚያተኩር ግለሰቦችን ወይም የማህበረሰቡ አባል የሆኑ ሰዎችን ማህበራዊ ትስስሮቻቸውን በማጠንከር ህብረተሰባዊነት አንድነትን መፍጠር የሚያስችል አካባቢያዊ ባህል ነው። ክውን ጥበባት ማህበራዊ እንቅስቃሴዎችን፣ ንግግሮችን፣ እውቀቶችን እና የተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮችን የጥበብ እሴት የሆኑትን አሳምሮ እና አስውበው የሚያቀርቡ እና ሁለንተናዊ ትኩረት የሚያሰርፁ ናቸው። ለምሳሌ የማህበረሰቡን የጋራ ሃብት፣ መልከዓ-ምድር፣ ጀግንነት፣ አዋቂነት እና መሰል ተግባራቱን ከተለመደው በተለየ እና በሚስብ መልክ የሚያቀርቡ በመሆኑ ማህበራዊ ትስስርን ያጠናክራሉ።

የማህበራዊ ሳይንስ ትምህርቶች እንዲያስተላልፉ የሚፈለጉትን የሥነ-ምግባር፣ የማህበራዊ ደህንነትን፣ መረዳዳት፣ መቻቻል፣ መፈቃቀር፣ ማህበራዊ አስተዳደር እና መሰል እውቀቶችን በቀላሉ ለማህበረሰቡ ማስጨበጥ የሚያስችሉ መስኮች ናቸው።

ተግባር 5.2


1. በመከባበር እና መረዳዳት ላይ የሚያተኩር ግጥም እና ዜማ አዘጋጅታችሁ በአካላዊ እንቅስቃሴ በታጀበ መልኩ አቅርቡ።
2. አንድ አካባቢያዊ ታሪክን የሚገልፅ አጭር ጭውውት በማዘጋጀት እንዴት የማህበራዊ ሳይንስ ትምህርትን በቀላሉ ማስተማር እንደሚቻል ማብራሪያ ስጡ።


ሐ) ክውን ጥበባት ከሂሳብ ትምህርት ጋር ያላቸው ዝምድና

የሙዚቃ ትምህርት የተለያዩ ስሌቶችን ምናባዊ (አእምሯዊ) በሆነ መንገድ በማስላት እና በማሰብ በተግባር መግለፅ ነው። ምንም እንኳን ሂሳባዊ ቀመሮችን በሚታይ መልኩ በቀጥታ መማር ባይሆን ሂሳባዊ የሆኑ ስሌቶች እና ቁጥሮችን በእያንዳንዱ የሙዚቃ ትግበራ ወቅት ይከወናሉ።

በተጨማሪም የሙዚቃ ትምህርትን ተጠቅሞ የሂሳብ ትምህርትን ማስተማር የሚያስችሉ መንገዶችን በውስጡ የያዘ ከመሆኑም በላይ ትምህርቱ እንዳይረሳ በዝማሬ ተማሪዎች ደጋግመው እንዲማሩት እድል ይፈጥርላቸዋል። እንዲሁም የፈጠራ ችሎታን የሚያሳድግ እና በራስ የመተማመን ስሜትን የሚያጎለብት ነው።

የሙዚቃ ትምህርት የሆኑት እንደ ጊዜ አመልካች ቁጥሮች፣ የድምፅ እና ምት ስርዓት ንባብ እና ሌሎች ተግባራት ከሂሳባዊ ስሌቶች እና ቀመሮች ጋር የተያያዙ ቢሆኑም የሚከተሉት የኖታዎችን የጊዜ ቆይታ የሚያመላክቱ እና በሙዚቃ ቅኝት ግንባታ ወቅት የሚያገለግሉ የድንገተኛ ምልክቶችን ፍለጋ እና ቅኝት ግንባታ የባለአምስት ክብ (circle of fiveth) የሙዚቃ ሂሳባዊ ስሌት ከሒሳብ ትምህርት ተግባር ጋር ያላቸውን ዝምድና መመልከት ይቻላል። ለምሳሌ የሚከተሉትን እንመልከት፡-





ተግባር 5.3

1. ከላይ የቀረበውን ምሳሌ በማየት ክውን ጥበባት እንዴት ከሒሳብ ትምህርት ጋር ዝምድና እንዳላቸው ማብራሪያ ስጡ።
2. የሙዚቃ ትምህርት ከሒሳብ ትምህርትጋር ያለቸው ዝምድናን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።
3. ቀላል ቁጥሮችን ለማስተማር የሚያስችል መዝሙር አዘጋጁ እና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

መ) ክውን ጥበባት ከቋንቋ ትምህርት ጋር ያላቸው ዝምድና

ቋንቋ ለሰው ልጆች ተግባቦት የሚፈጥር እና የባህል ዋነኛ መሳሪያ ነው። በቋንቋ የማይነገር እውቀት፣ ባህል፣ ልማድ፣ ሀይማኖት፣ ፖለቲካ፣ ፍልስፍና ወዘተ የለም። ይህ የሚሆነው ደግሞ ሰዎች በማህበር መኖር ሲችሉ ነው። በመሆኑም ማህበራዊ ተግባቦት ለአንድ ማህበረሰብ እውቀት፣ ባህል፣ ልምድ፣ እምነት እና ሌሎች ክዋኔዎቹ ቋንቋ መሰረታዊ ነገሩ ነው ማለት ነው።

ክውን ጥበባት እንደ ቋንቋ ሆኖ የሚያገለግል የሰዎችን ጥልቅ ስሜት ውበት ባለው መልኩ መግለፅ እና መግባባት የሚያስችል በመሆኑ ከቋንቋ ጋር በእጅጉ ይዛመዳል። ይሁን እንጅ የቋንቋ ትምህርቶችን (የመናገር እና ማዳመጥ) ተግባራትን አሳላጭ በመሆን ደግሞ ወደር የሌለው ጥበብ ነው። በሙዚቃ ፊደላትን፣ ቃላትን፣ አረፍተ ነገርን፣ የቋንቋ ውበትን፣ ሳቅ እና ቁጣን መግለፅ ይቻላል። በመዝሙር እና በድራማ የመናገር፣ የመጻፍ፣ የማዳመጥ ክህሎትን በቀላሉ ማዳበር ይቻላል።

ተግባር 5.4

1. የክውን ጥበባትን በመጠቀም እንዴት የቋንቋ ትምህርትን በቀላሉ ማስተማር እንደሚቻል በምሳሌ በማስደገፍ ማብራሪያ ስጡ።
2. የክውን ጥበባት ከቋንቋ ትምህርቶች ጋር ያላቸውን ዝምድና ምሳሌ በመስጠት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩ።
3. ከክውን ጥበባት መካከል አንዱ መንገድ በመምረጥ እንዴት የቋንቋ ትምህርትን ማስተማር እንደሚቻል የሚያሳይ አንድ የተግባር ስራ አዘጋጅታችሁ በመምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በተግባር ሰርታችሁ አሳዩ።


5.1.2 የዕይታዊ ጥበባት ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ያላቸው ዝምድና

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. የዕይታዊ ጥበባት ከማህበራዊ ሳይንስ ትምህርት ጋር እንዴት ዝምድና እንዳላቸው ማብራሪያ ስጡ።
2. የዕይታዊ ጥበባትን ተጠቅመን የተፈጥሮ ሳይንስን ትምህርት እንዴት ማስተማር እንደሚቻል ምሳሌ በመስጠት ሰፋ ያለ ማብራሪያ ስጡ።
3. የዕይታዊ ጥበባት ከሂሳብ ትምህርት ጋር ምን ዝምድና አላቸው?
4. የዕይታዊ ጥበባት ከቋንቋ ትምህርት ጋር ያላቸዉን ዝምድና አብራሩ።


ሀ የዕይታዊ ጥበባት ከተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርት ጋር ያላቸው ዝምድና

በህብረ-ቀለማት (በስፔክትረም ቀለማት) አፈጣጠር፣ በነገሮች ተፈጥሯዊ እና ሰው ሰራሽ ቅርፅ አፈጣጠር፣ በተፈጥሮዊ ውበት አገላለጽ፣ በቤት አሰራር ዲዛይን አሰራር፣ በቀለማት ውህደት አጸግብሮት እና በመሳሰሉት ነገሮች የዕይታዊ ጥበባትን ከተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርት ጋር ግልጽ የሆነ ዝምድና አለው። ለምሳሌ የሚከተሉትን እንመልከት፦ የስፔክትረም ቀለም የምንላቸው በቅደም ተከተል በፕሪዝም በነጭ ወረቀት ላይ ሲያርፉ ቀይ፣ ብርቱካን፣ ቢጫ፣ አረንጓዴ፣ ሰማያዊ፣ ውሃማ ወይነጠጅ እና ወይነጠጅ ናቸው። በመሆኑም እነዚህ ቀለሞች የተፈጠሩበትን ሁነታ ስንመለከት ዕይታዊ ጥበባት ከተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርት ጋር ያለዉን ትስስር ያሳየናል።



ሥዕል 56 የስፔክትረም ቀለማት አፈጣጠር





ሥዕል 57 የቀለማት አጸግብሮት የሚያሳይ

ተግባር 5.4

1. የዕይታዊ ጥበባትን ተጠቅሞ ተፈጥሮ ሳይንስን እንዴት ማስተማር እንደሚቻል ምሳሌ በመስጠት ሰፋ ያለ ማብራሪያ ስጡ።
2. የዕይታዊ ጥበባት ከተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርት ጋር ያላቸዉን ዝምድና ግለፁ።

ለ) የዕይታዊ ጥበባት ከማህበራዊ ሳይንስ ጋር ያላቸዉ ዝምድና

የዕይታዊ ጥበባት ከማህበራዊ ሳይንስ ትምህርት ጋር በማህበራዊ ጠቀሜታ፣ ባህልን ለመግለፅ፣ ታሪካዊ ቅርሶችን ለመግለፅ ፣ የመልካ ምድር ንድፍ ለማጥናት፣ ታሪክን ከስዕሎች ለመረዳት፣ ከቅርፆች (ሀውልቶች) ታሪክን ወስዶ ለመፃፍ፣ ባህልን ከተለያዩ የእጅ ስራዎች በመውሰድ ለመፃፍ፣ ማህበራዊ ጠቀሜታን ማለትም ማህበራዊ ህይወትን ከማህበረሰቡ ጋር ጠንካራ የሆነ ዝምድና እንዲኖር ለማስተላለፍ ፣ በካርታ ላይ ውሀማ አካላትን በቀለም ለይቶ ለማስቀመጥ(ለማሳየት) እና በተጨማሪም ቅርስን ለመጠበቅ ታሪክን ለትዉልድ ለማስተላለፍ የእይታዊ ጥበባት ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸዉ። ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ታሪካዊ ቅርሶች በመመልከት የዕይታዊ ጥበባት ከማህበራዊ ሳይንስ ጋር ያላቸዉን ዝምድና እና በቀላሉ የማህበራዊ ሳይንስ ይዘቶችን ለማስተማር ያለዉን ፋይዳ ከስዕሉ ተመልከቱ።



ሥዕል 58 የፋሲል ግንብ




ሥዕል 59 የጀጎል ግንብ

ተግባር 5.5

1. የዕይታዊ ጥበባት ከማህበራዊ ሳይንስ ጋር እንዴት እንደሚዛመድ በምሳሌ አስደግፋችሁ አስረዱ።
2. የዕይታዊ ጥበባትን በመጠቀም እንዴት የማህበራዊ ሳይንስ ትምህርትን በቀላሉ ማስተማር እንደሚቻል የሚያሳይ አንድ የተግባር ስራ ሰርታችሁ በመምጣት ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር በማስተያየት ተወያዩ።

ሐ የዕይታዊ ጥበባት ከሂሳብ ትምህርት ጋር ያላቸው ዝምድና

የዕይታዊ ጥበባት ለሂሳብ ትምህርት በመማር ማስተማሩ ላይ ከፍተኛ የሆነ ሚና አለው። ለምሳሌ በስኬል ሥዕሎችን ለማሳነስ እና ለማሳደግ፣ ጠጣር ጀኦሜትሪያዊ ምስሎችን በንድፍ ግልፅ አድርጎ ለማስቀመጥ ፣ በይዘት እና በስፋት የሚገለፁ ጂኦሜትሪክ ምስሎች ለመለየት፣ መሰረታዊ ፎርሞችን በንድፍ በትክክል ለማስቀመጥ፤ ዙሪያ እና ይዘታቸውን ለመግለጽ የዕይታዊ ጥበባት ከሂሳብ ትምህርት ጋር ያለዉን ዝምድና እና እንዴት በቀላሉ የሂሳብ ትምህርት ይዘቶችን በቀላሉ ማስገንዘብ እንደሚቻል ያሳየናል። ምሳል የሚከተሉትን እንመልከት፦



ሥዕል 60 ዕይታዊ ጥበባት ከሂሳብ ትምህርት ጋር ያለውን ዝምድና የሚያሳይ ምስል


ተግባር 5.6

1. ከላይ የተቀመጡት ምስዕሎች በመጠቀም እንዴት ሂሳብን ማስተማር እንደሚቻል አስረዱ።
2. የዕይታዊ ጥበባት እና የሂሳብ ትምህርት ያላቸውን ዝምድና አብራሩ።
3. ከላይ ባያችኋቸው ምሳሌዎች መሰረት የዕይታዊ ጥበባትን በመጠቀም እንዴት የሂሳብን ትምህርት በቀላሉ ማስተማር እንደሚቻል የሚያሳይ አንድ የተግባር ስራ ሰርታችሁ በመምጣት እርስ በእርሳችሁ አስተያየት ተሰጣጡ።


መ) የዕይታዊ ጥበባት ከቋንቋ ትምህርት ጋር ያላቸው ዝምድና

የዕይታዊ ጥበባት ከቋንቋ ትምህርት ጋር ከፍተኛ የሆነ ዝምድና አላቸው። ለምሳሌ፦ በፊደላት አፃፃፍ፣ በዲዛይን አናስሮች እና ሥዕላዊ ድርሰትን መጥቀስ ይቻላል። የዕይታዊ ጥበባት እና የቋንቋ ትምህርት ያላቸዉን ዝምድና እና እንዴት በቀላሉ የቋንቋ ትምህርትን ማስገንዘብ እንደሚቻል የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት፦

1.



2.



ተግባር 5.7


1. የዕይታዊ ጥበባት ከቋንቋ ትምህርት ጋር ስላለዉ ዝምድና ማብራሪያ ስጡ።
2. የቋንቋ ትምህርትን ለማስተማር የሚሆን አንድ ሥዕላዊ መግለጫ ስላችሁ አሳዩ።
3. ከዚህ በታች የተቀመጠውን ሥዕላዊ ድርስት ካነበባችሁ በኋላ ያገኛችሁትን መረጃ በመጻፍ የዕይታዊ ጥበባት ፋይዳን ለመምህራችሁ እና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩ።



4. ከዲዛይን አናስሮች መካከል መስመርን በመጠቀም ድርብ ፊደላትን በተለያዩ የአፃፃፍ ዘዴ በተግባር ሰርታችሁ አሳዩ።

ሠ) የሥነ-ጥበባት ትምህርት ከልዩ ፍላጎት ትምህርት ጋር ያለዉ ዝምድና






ሥዕል 61


5.2 ሥነ-ጥበባትን ከወቅታዊ ጉዳዮች ጋር ማስተሳሰር

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. ሥነ -ጥበባት ከወቅታዊ ጉዳዮች ጋር ያላቸዉን ትስስር ማብራሪያ ስጡ።
2. ተፈጥሯዊ እና ሰው ሰራሽ ወቅታዊ ችግሮችን ከመከላከል አንፃር የሥነ-ጥበባት ትምህርት ምን ጠቀሜታ እንዳለዉ ማብራሪያ ስጡ።
3. ማህበራዊ ንቃተ ህሌና ከመጨመር አንጻር የክዉን እና ዕይታዊ ጥበባት ምን ፋይዳ አላቸው?

ሥነ-ጥበባት ወቅታዊ ጉዳዮችን በቀላሉ ለማህበረሰቡ ለማስተዋወቅ እና የማህበረሰቡን ንቃተ ህሌና ለመጨመር ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ አላቸዉ። ለምሳሌ በሽለላ፣በቀረርቶ፣በሙሾ፣በሎጎ፣በፖስተር፣በድራማ እና በፊልም ስለ ወቅታዊ ጉዳዮች እና ሀገሩን ከጠላት ወራሪ እንዲታደግ የአንድን አካባቢ ማህበረሰብ ብሎም የአንድን ሀገር ህዝብ ንቃተ ህሌና መጨመር እና ማነቃቃት ይቻላል። ለምሳሌ ከዚህ በታች የቀረቡትን የጥበብ ስራዎች በመመልከት ሥነ -ጥበባትን እንዴት ከወቅታዊ ጉዳዮች ጋር ማስተሳሰር እንደሚቻል እና ወቅታዊ ጉዳዮችን በቀላሉ ለማህበረሰቡ ማስገንዘብ እንደሚቻል እንረዳለን።





ሥዕል 62



ሥዕል 63

ተግባር 5.9

1. ከላይ በሥዕል 61 የተቀመጡት ሥዕላዊ መግለጫዎችን በጥሞና በመመልከት ምን እንደተረዳችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፤

2. ከላይ በሥዕል 62 እና 63 የተቀመጡት ሥዕላዊ መግለጫዎችን በጥሞና በመመልከት ምን እንደተረዳችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፤

3. ከላይ የተቀመጡትን ሥዕላዊ መግለጫዎች ምሳሌ በማድረግ ክዉን እና የዕይታዊ ጥበባት በመጠቀም ወቅታዊ ጉዳዮችን የሚገልፅ አንድ የተግባር ስራ ሰርታችሁ አሳዩ።

የምዕራፉ ማጠቃለያ

ሥነ-ጥበባት ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር በተዘዋዋሪም ሆነ በቀጥታ ከፍተኛ የሆነ ዝምድና አላቸው። ዕይታዊ እና ክውናዊ ጥበባትን በመጠቀም ሂሳብን፣ ቋንቋን፣ ተፈጥሮ ሳይንስን፣ ማህበራዊ ሳይንስን እና የመሳሰሉትን የትምህርት አይነቶች በቀላሉ ማስተማር ይቻላል። በመሆኑም የዕይታዊ እና ክውናዊ ጥበባትን በተጨባጭ በተግባር በመስራት የሚፈለገውን የትምህርት ብቃት ለማስጨበጥ ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ አላቸው።

ሥነ- ጥበባት የአንድን ሰው የንግግር ችሎታን፣ በራስ የመተማመን ስሜትን፣ የፈጠራ ችሎታን ለመግለጽ ፤ከሰዎች ጋር በቀላሉ ለመግባባት፣ የማሰብ ችሎታን ለማዳበር፣ ሥነ ምግባር እንዲኖር፣ በጋራ የመስራት ባህልን ለማዳበር፣ የአንድን አካባቢ ታሪክ ለማወቅ፣ የታሪካዊ ሰዎች ታሪክን ለማወቅ ፤ወቅታዊ ጉዳዮችን በቀላሉ ለማህበረሰቡ ግንዛቤ ለማስጨበጥ፣ የሀገር ኢኮኖሚን ለማሳደግ እና ለመሳሰሉት ጉዳዮች ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ አላቸው። ስለዚህ ሌሎችን የትምህርት ዓይነት በቀላሉ እና ግልጽ በሆነ መንገድ ለማስተማር ሥነ-ጥበባት (የዕይታዊ እና ክውናዊ ጥበብ)ከፍተኛ ድርሻ አላቸው።

የምዕራፉ ቼክሊስቶች

ቀጥለው የተቀመጡትን የምዕራፉ ቸክሊስቶች በማንበብ ማሳካት እና አለማሳካታችሁን ገምግሙ

ተ.ቁ	ይዘት	አሳክቻለሁ	አላሳካሁም
1	የዕይታዊ ጥበባት ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ያላቸውን ዝምድና በግልጽ ማወቅ ችያለሁ።		
2	የክውን ጥበባት ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ያላቸውን ትስስር በግልጽ መገንዘብ ችያለሁ።		
3	ሥነ- ጥበባት ለወቅታዊ ጉዳዮች ያላቸው አስተዋጽኦን ተረድቻለሁ።		

4	የክውን እና ዕይታዊ ጥበባትን በመጠቀም የተለያዩ ወቅታዊ ችግሮችን ለቤተሰቦቸ በግልጽ ማስረዳት እችላለሁ።		
5	የክውን እና ዕይታዊ ጥበባት ሌሎች የትምህርት አይነቶችን በቀላሉ ለማስተማር እና ለማስታወስ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳላቸው ተረድቻለሁ።		
6	የክዉን እና የዕይታዊ ጥበባትን ከወቅታዊ ጉዳዮች ጋር ማስተሳሰር ችያለዉ።		
7	ወቅታዊ ጉዳዮች ከሥነ-ጥበባትጋር ያላቸው ዝምድናን በግልጽ አውቃለሁ።		

የማጠቃለያ መልመጃዎች

ትዕዛዝ አንድ፡- ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ

1. ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የትምህርት ዓይነቶችን ከዕይታዊ እና ከክውን ጥበባት ጋር ያላቸውን ዝምድና አስረዱ፡፤

   ሀ) ተፈጥሮ ሳይንስ

   ለ) ማህበራዊ ሳይንስ

   ሐ) ቋንቋ

   መ) ሒሳብ

2. ሥነ-ጥበባት ከወቅታዊ ጉዳዮች ጋር ያላቸውን ዝምድና በሥዕላዊ መግለጫ እና በመዝሙር ሰርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ

3. ሥነ-ጥበባት የወቅታዊ ጉዳዮችን መልክት ለማስተላለፍ ያላቸውን አስተዋጽኦ በምሳሌ አሰደግፋችሁ አብራሩ።

መዳዩ ቃላት

- አናስር፡- የዲዛይን መሰረቶች ወይም አላባዉያን
- መርህ፡- የዲዛይን ህጎች
- ቴክስቸር፡- በሥነ-ስዕል ወይም ኪነ-ቅርፅ ስራ ዉስጥ የሼካራነት እና ልስላሴ ባህሪን የሚገልፅ
- ፍካት፡- በዲዛይን ስራ ዉስጥ ከጥቁረት እስከ ንጣት ያለዉ የቶን ደረጃ
- ቫሊዩ፡- በዲዛይን ስራ ዉስጥ ከጥቁረት እስከ ንጣት ወይም ከንጣት እስከ ጥቁረት ያለዉ የቶን ደረጃ
- ሐሳፊ፡- በዲዛይን ስራ ዉስጥ የነገሮች አንድነት ወይም ስምምነት
- ሞልድ (ቅርፀ አካል)፡- ቅርፅን ለማራባት ጆሶ ወይም ፈሳሽ ነገሮችን የምንሞላበት ጎድጓደዉ ክፍል
- ስፔክትረም፡- ህብረ-ቀለም
- ሥነ-ጥበባት፡- በዉስጡ ሥነ-ስዕልን፣ሙዚቃን፣ቴያትር እና ድራማን አካቶ የያዘ
- ኬሮግራፊ፡- የዉዝዋዜ አሰላለፍ ሥርዓት
- ኖታ፡- የሙዚቃ ምልክት
- ክዉን ጥበባት፡- ሙዚቃን፣ ዉዝዋዜን፣ ቴያትርን እና ፊልምን የያዘ
- ዕይታዊ ጥበባት፡- ቀለም ቅብ፣ ኪነ-ቅርፅ፣ ፎቶ ግራፍ፣ ሥዕል የያዘ
- የቁልፍ የሙዚቃ መሳሪያ፡- የምት እና የክር ባህሪያት የያዘ
- አልቶ፡- የሴት ወፍራም ድምፅ
- ሶፕራኖ፡- የሴት ቀጭን ድምፅ
- ቴነር፡- የወንድ ቀጭን ድምፅ
- ቤዝ፡- የወንድ ወፍራም ድምፅ
- ኢንተርቫል፡- የሙዚቃ ድምፅ ርቀት

ዋቢዎች

ሰይፈ ዘሪሁን:: (2004 ዓ.ም):: *የሥነ-ጥበብ እና የዲዛይን ትምህርት::*

አለማየሁ ወ/ዮኃንስ:: (2002 ዓ.ም):: *የሙዚቃ ትምህርት እና የሙዚቃ መሳሪያዎች አጠናን::*

ጫንያለው ወ/ጊዮርጊስ:: (2006 ዓ.ም):: *መሰረታዊ የተውኔት አጻጻፍ መረሆች* በብሔራዊ ቴያትር የታተመ አዲስ አበባ::

በላይ ግደይ:: (1983 ዓ.ም):: *የኢትዮጵያ ሰልጣኔ* ብርሀን እና ሰላም ማተሚያ ቤት የታተመ::

ሰለሞን ተሾመ:: (2007 ዓ.ም):: *ፎክሎር ምንነቱ እና የትኩረት አቅጣጫ* በፋር ኢስት ትሬዲንግ አሳታሚ ድርጅት የታተመ::

ኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ:: (1995 ዓ.ም):: *የባህላዊ መዚቃ መሳሪያዎች ትምህርት::*

ጌትነት ቦጋለ:: (2010 ዓ.ም):: *የጀንበር እድሜ ሰንቅ* በአቤኔዘር አሳታሚ ድርጅት የታተመ ባህር ዳር::

Minestry of education: (2003 E.C). *Traditional instrument I and II* prepared for 10+3 teacher education deploma programe .

ተስፋየ ለማ:: (2005 ዓ.ም):: የኢትዮጵያ የሙዚቃ ታሪክ ከ1989–1983 ዓ.ም ዋሺንግተን ዲ.ሲ አሜሪካ የታተመ::